# አርነት

# በምርኮ ውስጥ ላሉት

## ከእስልምናና ከዲህሚ ሕይወት በመስቀሉ ነፃ መውጣት

(**ይህ መጽሐፍ** “Liberty to the Captives, Freedom from Islam and Dhimmitude through the Cross” **ከሚለው መጽሐፍ በደራሲው ፈቃድ የተተረጎመ ነው**)

*ለጥርሳቸው ንክሻ ያላደረገን እግዚአብሔር ይባረክ።*

*ነፍሳችን እንደ ወፍ ከአዳኞች ወጥመድ አመለጠች።*

*ወጥመድ ተሰበረ እኛም አመለጥን።*

*ረድኤታችን ሰማይንና ምድርን በሠራ በእግዚአብሔር ስም ነው።*

መዝሙር 124

# ስለ ደራሲው

ማርክ ዱሪ የስነመለኮት ምሑር፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋች እና የአንግሊካን ቤተክርስቲያን መጋቢ ናቸው፡፡ አቻናውያን በመባል ስለሚታወቁ ሕዝቦች ቋንቋ እና ባህል፣ ስለ ክርስቲያን-ሙስሊም ግንኙነት እና ስለ ኃይማኖት ነፃነት በርካታ መጣጥፎችን እና መጽሐፍትን ጽፈዋል፡፡ ከአውስትራልያ ናሽናል ዩኒቨርስቲ እና ከአውስትራልያ የስነመለኮት ኮሌጅ ተመርቀዋል፡፡ በሊድን ዩኒቨርስቲ በተጋባዥ መምህርነት አገልግለዋል፡፡ በስታንፎርድ ዩኒቨርስቲም በማስተማር ያገለገሉ ሲሆን በ1992 ዓ.ም. ደግሞ በአውስትራልያ በሚገኘው አካዳሚ ኦፍ ሂውማኒቲስ ተቋም ከፍተኛ አመራር በመሆን ተመርጠዋል፡፡

# ሌሎች በደራሲው የተደረሱ መጽሐፍት

The Third Choice: Islam, Dhimmitude and Freedom

Deror Books 2010

Which God? Jesus, Holy Spirit, God in Christianity and Islam

ለበለጠ መረጃ

www.markdurie.com የሚለውን ድህረ ገፅ ይጎብኙ

Copyright © July 2014 by Mark Durie የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡ የዚህ ሥራ ማንኛውም ክፍል ያለ አሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ ሊወሰድም ሆነ ሊባዛ አይችልም፡፡

በዚህ የህትመት ሥራ ውስጥ የሚገኙት የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም በኢንተርናሽናል ባይብል ሶሳይቲ ፈቃድ እና ከ1954 ትርጉም (የቀድሞ ትርጉም) በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ፈቃድ ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው፡፡

# ማውጫ

እስልምናን የመተው አስፈላጊነት ..................... 1

ሸሀዳ ................................................... 9

የዲህማ ውል ...........................................27

መሐመድና ውግዘት ...................................41

ኢየሱስ የህማም ሰው ..................................69

መስቀሉ የአርነታችን መንገድ .........................83

ዲህማን እንዴት መካድ ይቻላል? .................. 115

ሸሃዳን እንዴት መካድ እንደምንችል ............. 129

ዋቢ መጻሕፍት/ BIBLIOGRAPHY .............. 151

# ምስጋና

ይህን መጽሐፍ ከዚህ ለማድረስ ርዳታችሁን ለለገሳችሁኝ በሙሉ ፣ ለዚች አነስተኛ መጽሐፍ ጅማሬ በግብረ መልስ፣ በምክር እና በማበረታታት ስላደረጋችሁት ታላቅ አስተዋፅዖ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ ያለ እናንተ እርዳታ ጭራሹንም አትፃፍም ነበር፡፡

በተለይም የሞስክ ኤንድ ሚረክል ቡድን ዓመታትን ስለዘለቀው እርዳታቸው እና ዲህማን የመካጀ ጸሎቶቹን ለመሞከር አውድ ስላፈላለጉልኝ ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ በተለይም በመጨረሻዎቹ ምዕራፎች ውስጥ የሚገኙ ጸሎቶችን በተመለከተ ይህ መጽሐፍ ለክርስቲናዊ አገልግሎት ያለውን አስተዋጽዖ ለማሻሻል ማንኛውንም አስተያየታችሁን በደስታ እቀበላለሁ፡፡

Mark Durie, March 2013

# ማጣቀሻዎችን በተመለከተ

ይሄኛው ቅፅ ሆን ተብሎ አነስተኛ ማመሳከርያዎች እና የግርጌ ማጣቀሻዎች እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ ከምዕራፍ 1-3 ላሉት ርዕሰ ጉዳዮች ጠለቅ ያሉ ማጣቀሻዎች ቢያስፈልግዎ በጸሐፊው ከዚህ በፊት የተጻፈውን The Third Choice : Islam , Dhimmitude and Freedom የተሰኘውን መጽሐፍ ማመሳከር ይችላሉ፡፡

የቁርአን ማጣቀሻዎችን በተመለከተም 9፡29 የሚያመለክተው ሱራ 9 ቁጥር 29ን ነው፡፡ የቁርአን ጥቅሶች የተወሰዱት በነጃሺ አሳታሚ ድርጅት በ2004 ከታተመው የቅዱስ ቁርአን የአማርኛ ትርጉም ነው፡፡

# ምዕራፍ 1

# እስልምናን የመተው አስፈላጊነት

በዚህ ዘመን በዓለም ላይ ለሚገኙ ብዙ ሕዝቦች በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር ቢኖር እስልምናን መተው ነው፡፡ *አርነት በምርኮ ውስጥ ላሉት* የሚለው ይህ መጽሐፍ ይህንን ፍላጎት ለማሟላት በማለም የተዘጋጀ ነው፡፡ ክርስቲያኖች ተፅዕኖ ከሚያሳድረው የእስልምና መንፈስ ነፃ መውጣት ይችሉ ዘንድ የተለያዩ መሳርያዎችን፣ መረጃን እና ጸሎቶችን ያቀርባል፡፡

የዚህ መጽሐፍ ቁልፍ ሐሳብ የእስልምና መንፈሳዊ ኃይል ሸሀዳ እና ዲህማ በመባል በሚታወቁ ሁለት ቃል ኪዳኖች የሚሰራ ነው የሚል ነው፡፡ ሸሀዳ ሙስሊሞችን ዲህማ ደግሞ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎችን በእስልምና ሕግ ለተደነገጉ ነገሮች እንዲገዙ ያደርጋሉ፡፡

ይህ መጽሐፍ የሚከተሉትን ነጥቦች ያብራራል፡

- አንድ ሙስሊም የነበረ ነገር ግን ክርስቶስን ለመከተል የወሰነ ሰው በቃል ኪዳን ከታሰረበት ሸሀዳ እና ከግዴታዎቹ እንዴት ነፃ መውጣት እንደሚችል፡፡
- አንድ ሰው እንደ ክርስቲያን ነፃነቱን መቀዳጀት የሚችለው እና በሸሪአ ህግ በዲህማ በኩል ሙስሊም ባልሆኑ ሰዎች ላይ ከተጫነው አዋራጅ ከሆነው የበታችነት እንዴት መላቀቅ እንደሚችል፡፡

ክርስቲያኖች እነዚህን ነገሮች በመካድ ከሁለቱም ቃልኪዳኖች ተላቀው ተገቢውን ነፃነታቸውን መቀዳጀት ይችላሉ፡፡ ለዚሁ ዓላማ ተብሎ ከእስልምና ተፅዕኖ መላቀቅ የሚያስችሉ ጸሎቶች - የአርነት ስርኣቶች - ተዘጋጅተዋል፡፡

# ሁለቱ ቃል ኪዳኖች

ኢስላም የሚለው የአረብኛ ቃል "ራስን መስጠት" ወይንም "መገዛት" ማለት ነው፡፡ የመሐመድ ኃይማኖት ሁለት መገዛቶችን ለዓለም አቅርቧል፡፡ የመጀመርያው እስልምናን ተቀብሎ የተለወጠ ሰው መገዛት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ሙስሊም ያልሆነ ሰው እስልምናን ሳይቀበል ለእስልምና የበላይነት የሚገዛበት ነው፡፡

- እስልምናን የተቀበለ ሰው ቃል ኪዳን የሙስሊም የእምነት መግለጫ የሆነው ሸሀዳ ነው፡፡ ይህ የአላህን አንድነት፣ የመሐመድን ነቢይነት እና እነዚህ ነጥቦች በውስጣቸው የያዟቸውን ሐሳቦች በተመለከተ የሚደረግ የእምነት መግለጫ ነው፡፡

- *ለእስልምና ፖለቲካዊ የበላይነት ሙስሊም ባልሆነ ሰው የሚደረግ መገዛት ዲህማ* ነው፡፡ ይህ የክርስቲያኖችን እና የሌሎች እስልምናን ያልተቀበሉ ነገር ግን በህጎቹ ለመኖር የተገደዱ ሰዎችን ደረጃ የሚወስን የእስልምና ህግ ተቋም ነው፡፡

ሸሀዳን በመናገር ወይንም ደግሞ ዲህማን በመቀበል የሰው ልጆች እንዲገዙለት የሚጠይቀው የእስልምና ፍላጎት መገታት አለበት፡፡

ብዙ ክርስቲያኖች ክርስቶስን መከተል የፈለገ አንድ ሰው እስልምናን የመካዱ አስፈላጊነት እምብዛም ላይታያቸው ይችላል፡፡ ሙስሊም ሆነው የማያውቁ ክርስቲያኖች በእስልምና የበላይነት መንፈሳዊ ተፅዕኖ ስር እንደሚወድቁ እና የዲህማን ስምምነት ለመቃወም ሙስሊም እንዳለመሆናቸው መጠን እስልምና የሚጭንባቸውን ፍርሃት እና የበታችነት በመቋቋም ግላዊ እርምጃ መውሰድ እንደሚገባቸው ምናልባት ጥቂቶች ያስተውሉ ይሆናል፡፡

*አርነት በምርኮ ውስጥ ላሉት* በነዚህ መንታ የጭቆና ቃል ኪዳኖች (ሸሀዳ እና ዲህማ) በስተጀርባ ያሉትን መርሆች አጠር አድርጎ የሚያቀርብ ሲሆን አንባቢያንም ክርስቶስን፣ የሕይወቱን ኃይል እና ለነፃነታችን በመስቀሉ በኩል የሰጠንን መንፈሳዊ በረከቶች እንዲያስቡ ይጋብዛል፡፡ በመጨረሻም አንባቢያንን ክርስቶስ በነርሱ ፈንታ ያስገኘውን አርነት መቀዳጀት የሚያስችሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆች እና ጸሎቶች ቀርበዋል፡፡

# ሉአላዊነትን ማስተላለፍ

ብዙ የእስልምና የነገረ መለኮት ምሑራን ስለ ሉአላዊነት ብዙ ነገር ይናገራሉ፡ ሉአላዊነት የአላህ ብቻ ነው በሚለውም ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡ ይህንን ሲሉ የሸሪኣ ህግ በሁሉም የፍትህ እና የኃይል መርሆች ላይ የበላይነት ሊኖረው ይገባል ማለታቸው ነው፡፡

የዚህ መጽሐፍ ቁልፍ ነጥብ የክርስቶስ ተከታዮች ሌሎች ዓይነቶችን መንፈሳዊ ሉአላዊነቶች የመካድ መብትና እንዲያውም ግዴታ እንዳለባቸው የሚናገር ነው፡፡

በክርስቲያን መረዳት መሰረት ወደ ክርስቶስ መመለስ ማለት በነፍሳችን ላይ የሚደረጉ ከክርስቶስ ውጪ ያሉትን ሁሉንም መንፈሳዊ የበላይነቶች እውቅና መንፈግ ማለት ነው፡፡ ጳውሎስ ወደ ቆላስይስ በጻፈው መልዕክቱ ላይ ወደ ክርስቶስ እምነት መምጣትን ከአንድ መንግስት ወደ ሌላው መንግስት መሸጋገር እንደሆነ ይገልጻል፡

> እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፥ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን። (ቆላ 1፡13-14)

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሰው መንፈሳዊ ስልት ከአንዱ ወደ ሌላው መንግስት የሚደረግ የዚህ ለውጥ መርህ ነው፡፡ ክርስቲያን አማኞች እንደ ደህንነታቸው አንዱ ክፍል በክርስቶስ አገዛዝ ስር ወደመሆን መጥተዋል፡፡ ስለዚህም “በጨለማው ተፅዕኖ” ስር አይደሉም፡፡ ለአማኞች ከእስልምና እወጃ በተጻራሪ ይህንን የተፈጥሮ መብታቸው የሆነውን አርነት ለመቀዳጀት እና የራሳቸው ለማድረግ ከምን ውስጥ ተለውጠው እንደመጡ እና ወዴት እንደተለወጡ

ሊያውቁት ይገባል፡፡ ይህ መጽሐፍ ለአንባቢያን ይህንን ዕውቀት ይሰጣል እንዲሁም አማኞች ይህንን ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ የሚረዱ መሳርያዎችን ያቀርባል፡፡

# ሰይፍ መልስ ሊሆን አይችልም

የእስልምናን እቅድ ለመቋቋም የሚያስችሉ በርካታ መንገዶች አሉ፡፡ ይህ ፖለቲካዊ እና የመረጃ ልውውጥ፣ ሰብአዊ መብቶችን ማቀንቀን፣ ትምህርት፣ እና እውነትን ለማስተላለፍ መገናኛ ብዙሃንን መጠቀም ጨምሮ የተለያዩ እርምጃዎችን ያካትታል፡፡ ለአንዳንድ ማሕበረሰቦች እና ሃገራት ወታደራዊ ምላሽም አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ ሊኖር ይችላል፡፡

መሐመድ እምነቱን ወደ ዓለም እንዲያሰራጩ ተከታዮቹን ሲልካቸው ሙስሊም ላልሆኑ ሰዎች ሦስት ምርጫዎችን እንዲሰጡ ነበር ያዘዛቸው፡፡ የመጀመርያው ሸሀዳን በመያዝ ሙስሊም መሆን ነው፣ ሌላው በዲህማ ደንብ ፖለቲካዊ እጅ መስጠት ነው፣ ነገር ግን ሌላው ምርጫ ሰይፍ ነበር፡፡ ለሕይወታቸው እንዲዋጉ፣ እንዲገድሉ እና እንዲገደሉ፡፡ ልክ *"ቀቲሉ"* የሚለው የአረብኛ ቃል ይህንን ትግል ለመግለጽ ጥቅም ላይ እንደዋለው ማለት ነው (ቁርአን 9፡29፣ 2፡190፣ 2፡193፣ 2፡217፣ 9፡111 ይመልከቱ)፡፡

ነገር ግን ጂሃድን መቋቋም በሙስሊሞች እጅ መሸነፍን የማስከተሉ እድል እንዳለ ሆኖ መንፈሳዊ አደገኛነትም አለው፡፡ የአሮጌው ዓለም ክርስቲያኖች የእስልምናን ወረራ ለመከላከል በተነሱበት ዘመን (ትግሉ ከአንድ ሚሊንየም ጊዜ በላይ ፈጅቷል) የኢቤሪያን ባሕረ ሰላጤ መልሶ ለማስለቀቅ ስምንት ክፍለ ዘመናትን ፈጅቷል፡፡ ለውጦች ይመጡ የነበሩትም በልምምድ ሲሆን ሁል ጊዜ በጎ ለውጦች

አልነበሩም፡፡ ሳራሰኖች ሮምን ከያዙ ከሰባት ዓመት በኋላ እና አረቦች አንደሉሺያን ከወረሩ እና ከተቆጣጠሩ ከአንድ ክፍለ ዘመን በላይ ከሆነው በኋላ ነበር ጳጳሱ ሊዮን በ853 ዓ.ም. አብያተ ክርስቲያናትንና ከተሞችን ከአረቦች ሲከላከል የሞተ ሰው መንግስተ ሰማያት እንደሚገባ ያወጁት፡፡ ከሦስት ክፍለ ዘመናት በኋላ ደግሞ ክርስትናን በኃይል ለማስፋፋት ሲሉ ሕይወታቸውን የሚያጡ ሰዎች የኃጢአታቸውን ይቅርታ እንደሚቀበሉ ጳጳሱ ጆርጅ ሰባተኛ አወጁ፡፡ ይህ በብዙ ደም ማፍሰስ ወደ አዳዲስ ቦታዎች ከተስፋፋው የእስልምና ስነ መለኮት የተኮረጀ የመስቀል ጦረኞች "የቅዱስ ጦርነት" ዶግማ "የክርስቲያን ጂሃድን" ፈጥሯል፡፡

ዛሬ ክርስቲያኖች "ቅዱስ ጦርነትን" አይሰብኩም ነገር ግን ብዙ የክርስቲያኑ ዓለም ለእስልምና የስነ መለኮት አጀንዳ ምላሽ "በክርስቲያን ጂሃድ" የስህተት አስተምህሮ መያዙ እስልምናን ከመቋቋም በስተጀርባ ስላለው አደጋ ጥሩ ልምድ ተደርጎ መወሰድ አለበት፡፡

የእስልምና የኃይል መሰረት ወታደራዊ ወይንም ፖለቲካዊ አይደለም ነገር ግን መንፈሳዊ ነው፡፡ እስልምና በባሕርያቸው መንፈሳዊ የሆኑትን ነገሮች በሸሪአ ተቋም ውስጥ በሚገኙት በሸሀዳ እና በዲህማ በኩል ይተገብራቸዋል፡፡ ከዚህ የተነሳ እስልምናን ለመቋቋም እና ሰዎችን ነፃ ለማውጣት በዚህ ስፍራ ላይ የተሰጡት መሳርያዎች መንፈሳውያን ናቸው፡፡ ወደ አርነት ለመምጣት የመጽሐፍ ቅዱስን የመስቀል ፅንሰ ሐሳብ በመረዳት በክርስቲያን አማኞች ጥቅም ላይ መዋል እንዲችሉ የተቀናበሩ ናቸው፡፡

# በሰው ኃይል አይደለም

በዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ ከክርስቶስ ልደት በፊት ስድስት ክፍለ ዘመናትን በመቅደም የተሰጠ ከእስክንድር አገዛዝ ዘመን በኋላ ከሚመጡ መንግስታት ውስጥ ስለሚነሳ መሪ የሚናገር አስደናቂ ትንቢታዊ ራዕይ አለ፡

> በመንግሥታቸውም መጨረሻ፥ ኃጢአታቸው በተሞላች ጊዜ፥ እንቈቅልሽን የሚያስተውል ፊተ ጨካኝ ንጉሥ ይነሣል። ኃይሉም ይበረታል፥ ነገር ግን በራሱ ኃይል አይደለም በድንቅም ያጠፋል፥ ያደርግማል፥ ይከናወንማል ኃያላንንና የቅዱሳንን ሕዝብ ያጠፋል። በመታለሉ ተንኰልን በእጁ ያከናውናል በልቡም ይታበያል፥ ታምነውም የሚኖሩትን ብዙዎችን ያጠፋል በአለቆቹም አለቃ ላይ ይቋቋማል **ያለ እጅም ይሰበራል።** (ዳን 8፡23-25)

ይህ መሪ የእስልምናን የበላይነት አስተሳሰብ፣ ስኬቱን፣ ማታለልን መጠቀሙን፣ የሌሎችን ስልጣኔና ኃብት በመጠቀም ኃይሉን ማጠናከሩን፣ በሐሰተኛ የደህንነት ስሜት ውስጥ ያሉትን ማሸነፉን፣ የክርስቲያን እና የአይሁድ ማህበረሰቦችን ማጥፋቱን ከመሳሰሉት የመሐመድ ውርሶች ጋር የሚመሳሰል ባሕርይ አለው፡፡

ይህ ትንቢት ስለመሐመድ እና ከርሱ ግብረ ገባዊ እና መንፈሳዊ ድሽቀት ስለመነጨው ኃይማኖቱ የሚናገር ይሆንን? ይህ ከሆነ በዚህ ንጉስ ላይ ስለሚገኘው ድል የተሰጠው ተስፋ ይህ ድል “በሰው ኃይል” እንደማይገኝ የሚናገር ማስጠንቀቂያ አለው፡፡ ይህንን ኃይል ለማሸነፍ

አርነት በፖለቲካዊ፣ ወታደራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መንገዶች አይገኝም፡፡

ለብዙ ዘመናት ያደረኩት ጥናትና ምርምር እስልምና ሌሎችን የመቆጣጠር መብት እንዳለው ከመናገሩ አኳያ ይህ ማስጠንቀቂ በጣም ትክክል መሆኑን ተገንዝቤአለሁ፡፡ አለኝ የሚለው ኃይል መንፈሳዊ ነው፣ ስለዚህ ውጤታማና ዘላቂ በሆነ መንገድ ለመቋቋም እና ነፃነታችንን ለማስጠበቅ መፍትሄው መንፈሳዊ መንገድ ብቻ ነው፡፡ ሌሎች መንገዶች ምናልባት እስላማዊ ቅየጣን ለመቆጣጠር ይጠቅሙ ይሆናል ነገር ግን የችግሩ ምንጭ ጋር ሊደርሱ አይችሉም፡፡

ከእስልምና አዋራጅ የሆኑ ጥንስሶች እስከወዲያኛው ሊያላቅቅ የሚችለው የክርስቶስ ኃይል እና መስቀሉ ብቻ እንደሆኑ ተረድቼአለሁ፡፡ ከዚያ አመኔታ በመነሳት ነው ይህንን መጽሐፍ ልጽፍ የቻልኩት፡፡ ዓላማውም አማኞች የሰዎችን ነፍስ ለመቆጣጠር ከሚጠቀማቸው ከመንታ ስልቶቹ አምልጠው አርነት እንዲያገኙ ማስታጠቅ ነው፡፡

# የበለጠ ለማወቅ የሚሹ ከሆነ …

ይህ መጽሐፍ ግልፅ እና ቀጥተኛ እንዲሆን የታለመ ነው፡፡ ስለ እስልምና የበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ እና ከዋናዎቹ ምንጮች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን መረጃዎች መረጋገጥ ከፈለጉ ለዚህ ሥራ መሰረት የሆነው ጥናት ቀደም ሲል “The Third Choice: Islam, Dhimmitude and Freedom” በሚል ርዕስ በጻፍኩት መጽሐፌ ውስጥ በስፋትና በጥልቀት ይገኛል፡፡ ያ መጽሐፍ በዚህኛው ውስጥ የተነገሩትን ጉዳዮች በተመለከተ ከዋና ምንጮች የተጠቀሱ ማጣቀሻዎች አሉት፡፡

# ምዕራፍ 2

# ሸሀዳ

## እንዴት ነው ሙስሊም መሆን የሚቻለው?

ኢስላም የሚለው የአረብኛ ቃል መገዛት የሚል ትርጓሜ አለው፡፡ ሙስሊም የሚለው የአረብኛ ቃል የተገዛ የሚል አቻ ትርጓሜ አለው፡፡ ይሄኛው መገዛት ምን ማለት ነው? በቁርአን ላይ ስለ አላህ የተቀመጠው ትልቅ ስዕላዊ መግለጫ ሁሉን የሚገዛ ጌታ፣ በሁሉም ነገር ላይ ሙሉ በሙሉ ስልጣን ያለው የሚል ነው ነው፡፡ ወደ እስልምና መግባት ማለት ለአላህ ለመገዛት መስማማት ማለት ነው፡፡ ይሄም ደግሞ የሚደረገው ሸሀዳን (የእስልምና የእምነት አንቀጽን) በማነብነብ ነው፡፡ ይኸውም ፡-

*አሽሃዱ አነ ላ ኢላሃ ኢላ አላህ*

*ዋ አሽሃዱ አነ መሐመደን ረሱል አላህ*

*“ከአላህ በቀር ምንም አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ መሐመድም የአላህ መልዕክተኛ እንደሆኑ እመሰክራለሁ”* የሚል ነው፡፡

ሸሀዳን ተቀብለህ ለራስህ ብታነበንብ በአጭር ቃል ሙስሊም ሆነሃል ማለት ነው፡፡ እነዚህ ጥቂት ቃላት ብቻ ቢሆኑም አንድምታቸው በጣም ሰፊ ነው፡፡ ሸሀዳን ማነብነብ መሐመድ በሕይወት ዘመንህ ሁሉ ያንተ መሪ ይሆን ዘንድ የቃል ኪዳን አዋጅ ነው፡፡ ሙስሊም መሆን (የተገዛ መሆን) ማለት መሐመድን ለእያንዳንዱ የሕይወት ምዕራፍ መመርያን እንደሚሰጥ የመጨረሻ እና ልዩ የአላህ መልዕክተኛ መቀበል ማለት ነው፡፡ የመሐመድ መመርያዎች የተገኙት ከሁለት ምንጮች ነው፡፡ ሁለቱም በእስልምና የመጽሐፍ ጥቅልል ውስጥ በአንድ ላይ ይገኛሉ፡፡

- **ቁርአን**፡- ለመሐመድ ከአላህ የተገለጠለት መጽሐፍ ነው፡፡
- **ሱና**፡- የመሐመድ ምሳሌዎች ማለትም
- **አስተምህሮቶቹ**፡- ተከታዮቹ እንዲያደርጉት ያስተማራቸው
- **ድርጊቶቹ**፡- መሐመድ ያደረጋቸው ተግባራት

የመሐመድ ምሳሌነቶች ለሙስሊሞች በሁለት ዋና ቅርፆች ተመዝግበው ይገኛሉ፡፡ አንደኛው የሐዲስ ስብስብ ማለትም መሐመድ ያደረጋቸው እና የተናገራቸው በትውፊቶች ተመዝግበው ያሉ ሲሆኑ ሌላው ቅርፅ ሲራዎች የሚባሉት ናቸው፡፡ እነርሱም የመሐመድን የህይወት ታሪክ በቅደም ተከተል አስቀምጠው የያዙ ናቸው፡፡

# የመሐመድ ባህርይ

የመሐመድ ምሳሌነቶች ልንከተላቸው የሚገቡ ናቸውን? የመሐመድ አንዳንድ የሕይወቱ ክፍሎች አዎንታዊ ሲሆኑ ሌሎች የሚደነቁ፣ በጣም አስደሳች እና ፍጹም ማራኪ ናቸው፡፡ በየትኛውም የስነምግባር ደረጃ ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል ስህተት የሆኑ የታሪክ ተከታይ ሁኔታዎችም አሉ፡፡ በሲራዎች እና በሐዲስ አስደንጋጭ የሆኑ ሁነቶችን መመልከት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ያህል ግድያ፣ ስቃይ፣ አስገድዶ የመድፈር ወንጀል እና ሙስሊም ባልሆኑት ላይ ሽብርን ማነሳሳትን ያጠቃልላል፡፡

እነዚህ ጽሑፎች መሐመድ እንደ ግለሰብ ማን እንደነበር እንደ ማስረጃ ሆነው የሚረብሹን ብቻ አይደሉም፡፡ ይኼ ደግሞ  ለሁሉም ሙስሊሞች  እንደምታ አለው፡፡ የመሐመድ ምሳሌዎች በቁርአን መሰረት በአላህ ተገቢ የተደረጉና ሰዎች ሊከተሏቸው የሚገቡ የላቁ ምሳሌዎች ናቸው ስለዚህም በሙስሊሞች እንደ መለክያ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፣ ጥቅም ላይ ሲውሉም ነበር፡፡

ከሁሉም በላይ በሸሀዳ የታሰረ ማንኛውም ግለሰብ እነዚህን የመሐመድ ምሳሌዎች ሊከተላቸው እና ባህርያቶቹን የበለጠ ሊወርሳቸው ግድ ነው፡፡ የዚህ መሰረት በሸሀዳ እወጃ ውስጥ “መሐመድም የአላህ መልዕክተኛ ናቸው” የሚለው ነው፡፡ ይሄንን በንግግር መድገም መሐመድን የህይወትህ መሪ አድርጎ መቀበል ማለት ነው፡፡

በቁርአን ውስጥ መሐመድን ዋና ምሳሌ አድርጎ መከተል ለተከታዮቹ ሁሉ ግዴታ እንደሆነ ተነግሯል፡

> “መልክተኛውን የሚታዘዝ ሰው በእርግጥ አላህን ታዘዘ፡፡ ከትእዛዝም የሸሸ ሰው (አያሳስብህ)፡፡ በእነሱ ላይ ጠባቂ አድርገን አልላክንህምና” (4፡80)

> “አላህንና መልክተኛውን የሚታዘዝም ሰው፣ አላህንም የሚፈራና የሚጠነቀቀው ሰው፤ እነዚያ እነርሱ ፍለጎታቸውን የሚያገኙ ናቸው፡፡” (24፡52)

የመሐመድን ትዕዛዝ እና ምሳሌ መቃወም አለማመን ነው፡፡ ይሄም ደግሞ በቀጣይ ዘመን ወደ ህይወት ውድቀት እና ወደ ገሃነመ እሳት ይመራል፡፡ ይሄም እርግማን በቁርአን በሙስሊሞች ላይ ተደንግጓል፡

> “ቅኑም መንገድ ለርሱ ከተገለጸ በኋላ መልክተኛውን የሚጨቃጨቅና ከምዕመናቹ መንገድ ሌላ የኾነን የሚከተል ሰው (በዚህ ዓለም በተሾመበት ጥመት ላይ እንሾመዋለን) ገሀነምንም እናገባዋለን መመለሻይቱም ከፋች!” (4፡115)

> “አላህ ከከተሞቹ ሰዎች (ሀብት) በመልክኛው ላይ የመለሰው (ሀብት) ከናንተ ውስጥ በሀብታሞቹ መካከል ተዘዋዋሪ እንዳይሆን ለአላህና ለመልክተኛው ለዝምድና ባለቤትም አባት ለሌላቸው ልጆችም ለድኾችም ለመንገደኛም (የሚሰጥ) ነው፤ መልክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት ከርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ፡፡ አላህንም ፍሩ፤ አላህ ቅጣተ ብርቱ ነውና፡፡” (59፡7)

> “ከአላህ የኾነ ማድረስን መልዕክቶቹንም በስተቀር (አልችልም) አላህንና መልክተኛውንም የሚያምጥ ሰው

አርነት በምርኮ ውስጥ ላሉት

ለርሱ የገሀነም እሳት አልለው በውስጧ ዘላለም ዘውታሪዎች ሲሆኑ” (72፡23)

ቁርአን መሐመድን የሚቃወም ማንኛውንም ሰው የመዋጋት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡

“ከነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች እነዚያን በአላህና በመጨረሻው ቀን የማኑትን አላህና መልክተኛው እርም ያደረጉትን እርም የማያደርጉትን እውነተኛውንም ኃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ኾነው ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉዋቸው” (9፡29)

“ጌታህ ወደ መላዕክቱ እኔ (በርዳታዬ) ከናንተ ጋር ነኝና እነዚያን ያመኑትን አጥናኑ፤ በነዚያ በካዱት ልቦች ውስጥ ፍርሃትን በእርግጥ እጥላለሁ ከአንገቶችም በላይ (ራሶችን) ምቱ ከነርሱም የቅርንጫፎችን መለያያ ሁሉ ምቱ ሲል ያወረደውን (አስታውስ) ይህ እነርሱ አላህንና መልክተኛውን ስለተቃወሙ ነው፡፡ አላህንና መልክተኛውንም የሚቃወም ሁሉ አላህ ቅጣቱ ብርቱ ነው፡፡” (8፡12-13)

# ቁርአን፡- የመሐመድ የግል ሰነድ

ነገሮችን የሚረዱ ሙስሊሞች እንደሚያምኑት ከሆነ ቁርአን ፍጹም የሆነ የአላህ መገለጥ ያለበት፣ የሰው ልጆችን በአላህ አማካይነት የሚመራ፣ ለመልክተኛው መሐመድ የወረደ መልዕክት ነው፡፡ መልክተኛውን የምትቀበል ከሆነ መልዕክቱን መቀበል ግድ ነው፡፡ ስለሆነም ሸሀዳ ሙስሊሞችን በቁርአን እንዲያምኑ እና እንዲታዘዙት ያስገድዳል፡፡ ሊሰመርበት የሚገባው ቁልፍ ሀሳብ ቢኖር በቁርአንና

በመሐመድ መካከል ያለው ቅርበት የጀርባ አጥንት እና የሰው አካል ያህል መሆኑ ነው፡፡

ሱና በሰው አካል ሲመሰል ቁርአን ደግሞ በጀርባ አጥንት እንደማለት ነው፡፡ አንዳቸው ያለ አንዳቸው መቆም አይችሉም፡፡ አንደኛውን ያለ አንደኛው መረዳት አይቻልም፡፡

# ኢስላማዊ ሸሪአ፡- ሙስሊም የሚኮንበት መንገድ

የመሐመድን ትምህርት እና ምሳሌነት ለመከተል ሙስሊሞች ቁርአን እና ሱናን መመልከት አለባቸው፡፡ ይሁንና እነዚህ መጽሐፍት ለአብዛኞቹ ሙስሊሞች ውስብስብ ፣ ለመረዳት እና በራሳቸው ለመጠቀም አዳጋች ናቸው፡፡ ቆየት ባሉት የእስልምና ምዕተ ዓመታት የመሐመድን ሱና በሚስጥር መያዝ እና ማደራጀትን በተመለከተ አብዛኞቹ ሙስሊሞች እምነታቸውን ያደረጉት ጥቂት በሆኑ ሊቆች ላይ እንደነበር ለእስልምና የኃይማኖት መሪዎች ግልፅ ሆኖላቸዋል፡፡ ቁርአንንም የሚመሩበት ህግ እንዲሆን በስልት እና ወጥነት ባለው መልኩ እንዲደራጅ አድርገዋል፡፡ ስለሆነም ቁርአን እና የመሐመድን ሱና መሠረት በማድረግ የእስልምና የሕግ አዋቂዎች ከዚህ ያወጡት ሀሳብ ሸሪአ ወይንም እንደ እስላም የሚኖሩበት ሀሳብ ነው፡፡

እስላማዊው ሸሪአ የመሐመድ ሸሪአ ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያቱ ደግሞ መሠረቱ የመሐመድ ትምህርት እና ምሳሌ ስለሆነ ነው፡፡ ይህ የሕግ ሥርዓት አጠቃላይ የህይወትን መንገድ የሚገልጽ ነው፡፡ ያለ ሸሪአ እስልምና የሚባል ነገር የለም፡፡

የመሐመድ ሱና ለሸሪአ ህግ መሠረት በመሆኑ ምክንያት እርሱ ያደረገውን እና በሐዲስና በሲራ የተመዘገበውን እያንዳንዱን ጥቃቅን ነገር ቸል አለማለት አስፈላጊ ነው፡፡ ስለ መሐመድ አለማወቅ ስለ ሸሪአ አለማወቅ ማለት ነው፡፡ ይሄ ማለት ደግሞ በእስልምና ስር የሚኖሩትን ሰዎች ሰብአዊ መብት ያለማወቅ ማለት ነው፡፡ መሐመድ ያደረገውና የሸሪአ ህግም ሙስሊሞችን የሚያዘው በመቶ ሚሊዮኖች በሚቆጠሩ ሙስሊሞችም ሆነ ሙስሊም ባልሆኑ ሰዎች ህይወት ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ የመሐመድ ህይወት እና አሁን ያሉ ሰዎች ግንኙነት ቀጥተኛ ላይሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ሲበዛ የበረታ እና አስፈላጊ ሆኖ ይኖራል፡፡

ስለ ሸሪአ ህግ መታወቅ ያለበት ሌላው ነገር ቢኖር በፓርላማ የፀደቀው እና በህዝብ ተቀባይነት ያገኘው ህግ ሊለወጥ የሚችል ሲሆን የሸሪአ ህግ ግን መለኮታዊ ሥልጣን ያለው ፍጹም እና ሊለወጥ የማይችል መሆኑ ነው፡፡ እንደ ሁኔታው ሊለወጡ የሚችሉ አዳዲስ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ሙስሊም የሸሪአ ሊቃውንት ሸሪአ እንዴት በተግባር መተርጎም እንዳለበት ለመወሰን ምክንያትንና ንጽጽሮችን ይጠቀማሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ለውጦች የዳር ዳር እና ዋናውን የማይነኩ ናቸው፡፡

# የስኬት ተስፋ

እስልምና ትክክለኛውን ምሪት ማግኘትን በተመለከተ የሚያስበው ምንድን ነው? ለአላህ ለሚገዙ እና ምሪቱን ለሚቀበሉ በህይወታቸውና በቀሪው ዘመናቸው ስኬት ታስቦላቸዋል፡፡ ወደ እስልምና መጠራት ማለት ወደ ስኬት መጠራት ማለት ነው፡፡ ይሄም

የስኬት ጥሪ በአዛን ጊዜ ማለትም ለሰላት ጥሪ በሚደረግበት ጊዜ በቀን አምስቴ ይታወጃል፡፡

አላህ ታላቅ ነው! አላህ ታላቅ ነው!
አላህ ታላቅ ነው! አላህ ታላቅ ነው!
ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ
ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ
መሐመድ የአላህ መልዕክተኛ መሆኑን እመሰክራለሁ
መሐመድ የአላህ መልዕክተኛ መሆኑን እመሰክራለሁ
ለማምለክ ኑ! ለማምለክ ኑ!
ወደ ስኬት ኑ! ወደ ስኬት ኑ!
አላህ ታላቅ ነው! አላህ ታላቅ ነው!
አላህ ታላቅ ነው! አላህ ታላቅ ነው!
ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡

የስኬት አስፈላጊነት ዋና ነገር መሆኑን ቁርአን አፅንዖት በመስጠት ይናገራል፡፡ የሰው ልጆችን አሸናፊዎችና የተቀሩት በማለት በሁለት ይከፍላቸዋል፡፡ የአላህን ምሪት በተደጋጋሚ የማይቀበሉትን የከሰሩ በማለት ይጠራቸዋል፡፡

> "ከኢስላም ሌላ ኃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎች ነው፡፡" (3፡85)

> "ብታጋራ ሥራህ በእርግጥ ይታበሳል፤ በእርግጥም ከከሃዲዎቹ ትኾናለህ ማለት ወደ አንተም ወደነዚያም ካንተ በፊት ወደነበሩት በእርግጥ ተወርዷል፡፡" (39፡65)

ስኬትንና ውድቀትን በተመለከተ እስልምና ብዙ ማውራቱ ብዙዎቹ ሙስሊሞች እስልምናን ካልተቀበሉት የተሻሉ እነደሆነ በኃይማኖት ትምህርት ቤቶቻቸው ይማራሉ ማለት ነው፡፡ ኃይማኖታቸውን ያጠበቁ ሙስሊሞች ካላጠበቁት ይልቅ የተሻሉ እንደሆኑ ይነገራቸዋል፡፡

# የተከፈለ ዓለም

በየምዕራፎቹ እንደምንመለከተው ስለ ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆን ስለሌላ እምነት ተከታዮችም ቁርአን ብዙ የሚናገራቸው ነገሮች አሉት፡፡ የእስልምና ህግ ሙዳየ ቃላቶች እንደሚያመለክቱት አራት ዓይነት ሰዎች ይገኛሉ፡፡

1) የመጀመርያና ዋናዎቹ እውነተኛ ሙስሊሞች ናቸው፡፡
2) ግብዞች ተብለው የሚጠሩ ሌሎች ቡድኖች አሉ ከሙስሊሞች ያፈነገጡ ናቸው፡፡
3) ጣዖት አምላኪዎች ከመሐመድ በፊት የበላይነት የነበራቸው ቡድኖች ናቸው፡፡ ጣዖት አምላኪዎች ለሚለው ቃል አቻው “ሙሽሪክ” የሚል ሲሆን ሽሪክ ማድረግ የሚል ትርጓሜ አለው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ማንኛውም ወይንም የትኛውም ነገር አላህን ይመስላል ማለት ነው፡፡
4) የመጽሐፉ ሰዎች የሚባሉት የ “ሙሽሪክ” ንዑስ ቡድን ናቸው፡፡ ምክንያቱም ቁርአን ክርስቲያኖችንና አይሁዶችን ሽሪክ የፈጸሙ ሲል ይከሳቸዋልና፡፡

የመጽሐፉ ሰዎች የሚለው ፅንሰ ሀሳብ ክርስትናና የአይሁድ ኃይማኖት ተመሳሳይነት ያላቸውና ከእስልምና የተገኙ መሆናቸውን

ያመለክታል፡፡ እስልምና የአይሁድና የክርስትና ኃይማኖት መገኛ፣ እናት ኃይማኖት ነው፡፡ እንደ ቁርአን አስተምህሮ ከሆነ ክርስትናና የአይሁድ ኃይማኖት ከመጀመርያው በአንድ አምላክ የሚያምኑ ነበር ማለትም በሌላ አነጋገር ሙስሊም ነበሩ፤ ነገር ግን ቅዱሳት መጽሐፍቶቻቸው ስህተት የገባባቸውና የተለወጠ ስለሆነ መቼም ቢሆን እውነተኛ ሊሆን አይችልም የሚል ዕሳቤ አለው፡፡ ይሄ ማለት ክርስትናና የአይሁድ ኃይማኖት መገኛቸው እስልምና ሆኖ እውነትን ያዛቡ፣ ያጣመሙ ናቸው ተከታዮቻቸውም በስህተት ጎዳና እየነጎዱ ናቸው ብሎ ያስተምራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ክርስቲያኖችና አይሁዶች መሐመድ መጥቶ ቁርአን እስኪወርድለት ድረስ ከጨለማ መላቀቅ አልቻሉም ሲል አስተምህሮቱን ያስቀምጣል፡፡

> "እነዚያ ከመጽሐፉ ባለቤቶች ከአጋሪዎቹም የካዱት ግልጹ አስረጅ እስከመጣላቸው ድረስ (ከነበሩበት ላይ) ተወጋጆች አልነበሩም፡፡" (98፡1)

መሐመድ ለክርስቲያኖችና ለአይሁዶች አለመረዳታቸውን ለማስተካከል የመጣ የአላህ ስጦታ ነበር፤ ስለሆነም መሐመድን የአላህ መልዕክተኛ ቁርአንን ደግሞ የመጨረሻው መገለጥ አድርገው መቀበል እንዳለባቸው ያሳስባል፡፡ (5፡15፣ 57፡28፣ 4፡47)

ቁርአን ስለ ክርስቲያኖችና አይሁዶች አዎንታዊ የሆነ እና አሉታዊ የሆነ አስተያየት አለው፡፡ አዎንታዊ በሆነው ብርሃን ስንመለከት አንዳንድ ክርስቲያኖችና አይሁዶች ታማኞችና እውነተኛ አማኞች ናቸው ሲል ሀሳብ ይሰጣል (3፡113-114)፡፡ ቢሆንም በዚሁ በተመሳሳይ ምዕራፍ እንደምናገኘው የነዚህ ሰዎች እውነተኛነት የሚፈተነው ሃቀኞቹ ሙስሊሞች ወደመሆን በመምጣታቸው ነው (3፡199)፡፡

ምንም እንኳ ክርስቲያኖችና አይሁዶች በአንድ ምድብ ውስጥ ሆነው “የመጽሐፉ ሰዎች” ቢባሉም አይሁዶች በቁርአን ላይ የበለጠ በአሉታዊ ጎናቸው ተገልጸዋል፡፡ እንደ ምሳሌ አድርገን ብንወስድ ቁርአን ሙስሊሞችን ከመውደድ አንፃር ክርስቲያኖች ቀረብ የማለት አዝማምያ ሲያሳድሩ አይሁዶችና ጣዖት አምላኪዎች ግን በሙስሊሞች ላይ ብርቱ የሆነ ጠላትነት አለባቸው ሲል ያስተምራል (5፥82)፡፡ ቢሆንም የቁርአንን የመጨረሻ ፍርድ በምንመለከትበት ጊዜ በተመሳሳይ መልኩ ለክርስቲያኖችም ሆነ ለአይሁዶች አሉታዊ የሆነ አመለካከት አለው፡፡ ተቃውሞ ቁልፍ በሆኑ ስነ መለኮታዊ ንግግሮች ውስጥ የተገለጠ ሲሆን እምነታቸውን በትክክል በሚከተሉ ውስሊሞች የዘወትር ጸሎትም ውስጥ እንዲሁ ተካቶአል፡፡

# የእለት ጸሎቶች

በቁርአን እጅግ የታወቀው ምዕራፍ አል-ፋቲሃ (የመክፈቻ ምዕራፍ) የሚለው ነው፡፡ ይህንን ምዕራፍ በየእለት ጸሎት መደጋገም ግዴታ ነው፡፡ እያንዳንዱ ጸሎት በስግደት ጊዜ የሚደገም ነው፡፡ አንድ በእምነቱ ታማኝ የሆነ ሙስሊም እነዚህን ጸሎቶች በቀን ለ17 ጊዜና በዓመት ከ5,000 ጊዜ በላይ መድገም ይኖርበታል፡፡

አል -ፋቲሐህ ምሪት የሚጠየቅበት ጸሎት ነው፡፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርኅሩህ በጣም አዛኝ በኾነው

ምስጋና ለአላህ ይግባው የዓለማት ጌታ ለሆነው፤

እጅግ በጣም ርኅሩህ በጣም አዛኝ

የፍርዱ ቀን ባለቤት ለኾነው

አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታ እንለምናለን

ቀጥኛውን መንገድ ምራን

የእነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸው

በነሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና

ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ (ምራን በሉ)፡፡

ይህ ሙስሊሞች መንገዳቸው እንዲቀናና አላህ እንዲመራቸው የሚጠይቁበት የጸሎት ጥያቄ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ መመራትን አስመልክቶ ከልብ የሆነ እውነተኛ መልእክት ነው፡፡ ነገር ግን የአላህን ቁጣ የሚቀበሉ ወይንም ከትክክለኛው መንገድ ርቀው በስህተት ጎዳና ያሉት እነማን ናቸው? እጅግ ብዙ ሙስሊሞች በህይወት ዘመናቸው በየእለቱ በሚያደርጉት ጸሎት መቶ ሺህ ጊዜ መጥፎ ስም የሚሰጥዋቸው እነዚህ ሰዎች ማን ይሆኑ ይሆን? መሐመድ የዚህን ምዕራፍ ትርጓሜ እንዲህ ሲል ግልፅ አድርጓል፡፡ "አይሁዶች ቁጣ የሚገባቸው ሲሆኑ ክርስቲያኖች ደግሞ ከዳተኞች ናቸው"፡፡ እያንዳንዱ ሙስሊም በየቀኑ የሚጸልየው ጸሎት በአላህ ቁጣ ክርስቲያኖችና አይሁዶች እንዲወገዱ የሚል ትኩረት ያዘለ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡

# ሙስሊም ያልሆኑት ሊያውቁት የሚገባ ነገረ መለኮታዊ ጥያቄ

ከተከበረ መንፈሳዊ ስርአት በመዘለለ ቁርአንና ሱና የሚከተሉትን ያስተምራሉ

1) **በአላህ ላይ ሽሪክ ማድረግን አጥብቀው የፈጸሙ፣ በመሐመድና በአንድ አምላክ ባለማመናቸው የቀጠሉ ክርስቲያኖችና አይሁዶች ማለትም ወደ እስልምና ያልተለወጡት የሚጠብቃቸው ገሃነም ነው፡፡**

2) **ሙስሊሞች ከሌሎች ህዝቦች የበላይ ናቸው፡፡ የተለዩ ህዝቦች ናቸው፡፡ ሚናቸውም እኩይና ሰናይ የሆኑትን ማስተማር ማለትም የትኛው ነው የሚያስከብረው፣ የተከለከለው፣ አሳፋሪ የሆነው ምንድን ነው የሚሉትን ማስተማር ነው፡፡** (3፡110)

3) **የእስልምና እድል ፈንታ በሌሎች ኃይማኖቶች ላይ የበላይ ሆኑ መግዛት ነው፡፡** (48፡28)

4) **የበላይ የመሆንን ሀሳብ ወደ ስኬት ለማምጣት ሙስሊሞች በክርስቲያኖችና በአይሁዶች ላይ (በመጽሐፉ ሰዎች ላይ) ጦርነትን ይከፍታሉ፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ እስኪሸነፉ፣ ራሳቸውን በትህትና ማዋረድ እስከሚችሉ እና ለሙስሊሙ ማህበረሰብ ግብር መገበር እስከሚችሉ ድረስ ነው፡፡**

> "ከነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች እነዚያን በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምኑትን አላህና መልዕክኛው እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና እውኛውንም ኃይማኖት የማይቀበሉትን፤ እነርሱ የተዋረዱ ኾነው ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጓቸው" (9፡29)

5) **በመጨረሻው ዘመን የአይሁድ እምነትና ክርስትና ይጠፋሉ፡፡ መሐመድ እንዳስተማረው ከሆነ ዒሳ (የሙስሊሞች ኢየሱስ) ወደ ምድር በሚመለስበት ጊዜ**

ክርስትናን ከምድረገጽ ያጠፋል (መስቀልን ይሰብራል፡፡) ክርስቲያኖች ኢስላማዊውን ህግ ታግሰው እስከመጨረሻው እንዲገዙ ያደርጋል፡፡ የሙስሊም ምሑራን ሐዲሱን እንደሚተረጉሙት ከሆነ የሙስሊሞች ነብይ የሆነው ዒሳ ሁሉንም ክርስቲያኖችና የሌሎች እምነት ተከታዮችን በሰይፍ በመጠቀምም ቢሆን ወደ እስልምና እንዲለወጡ ያስገድዳቸዋል፡፡

6) ከላይ ለመግለጽ ከተሞከረው በተጨማሪ አይሁዶችን አስመልክቶ እጅግ ብዙ የተለዩ ነገረ መለኮታዊ አስተሳሰቦች አሉ፡፡ መሐመድ እንዳስተማረው በመጨረሻው ዘመን ድንጋይ ድምጽ በማሰማት ሙስሊሞች አይሁዶችን እንዲገድሉ ይረዳቸዋል፡፡

# የተፈቀደ ማታለል

ኢስላማዊ ሸሪአን አስመልክቶ ችግር ያለበት አንዱ አመለካከት ውሸትና ማታለልን የተመለከተ ነው፡፡ በእስልምና መዋሸት እጅግ ከባድ ኃጢአት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ነገር ግን የመሐመድን ምሳሌ መሰረት በሚያደርጉ የሙስሊም ሊቃውንት ውሸት የሚፈቀድባቸው አንዳንድ ሁኔታዎች እንዳሉ ይታመናል፤

ሙስሊሞች እንዲዋሹ የሚፈለግበትና የሚጠየቁበት በዛ ያሉ የተለዩ ሁኔታዎች አሉ፡፡ በሳሂህ አል ቡኻሪ ውስጥ በሚገኝ አንድ ምዕራፍ ላይ *"በህዝቦች መካከል ሰላምን የሚያሰፍን ውሸታም አይደለም"* ይላል፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ የመሐመድን ምሳሌ በምንመለከትበት ጊዜ ለሙስሊሞች እንዲዋሹ የሚፈቀድበት ሁኔታ ቢኖር ሰዎችን በሚያስታርቁበት ጊዜ ነው፡፡ ምክንያቱም ውጤቱ አዎንታዊ

ስለሚሆን ነው፡፡ የህጋዊ ማታለል ሌላው አውድ ሙስሊሞች ሙስሊም ባልሆኑት ሰዎች አደጋ ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ የሚያደርጉት መዋሸት ነው (3፡28)፡፡ ከዚህ ክፍል የምንወስደው ታቂያ የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ ነው፡፡ ይሄም የሚያመለክተው ሙስሊሞችን ከመታደግ አንፃር ስለሚደረግ ውሸት ነው፡፡

የሙስሊም ምሑራን የደረሱበት ድምዳሜ ቢኖር ሙስሊም ያልሆኑት የፖለቲካውን ስልጣን የበላይነት በሚያገኙበት ጊዜ እራስን ከመጠበቅ አንፃር ወዳጅነትንና መልካምነትን ማሳየት ለሙስሊሞች ጠቀሜታ አለው፡፡ ስለሆነም ጠላቶቻቸውን በልባቸው ይዘው በእምነታቸው መፅናት አለባቸው፡፡ የዚህ አስተምህሮ አንዱ እንድምታ እንደሚያሳየው ታዛቢ ሙስሊሞች የፖለቲካ ስልጣናቸው እየጨመረ በሄደ ቁጥር ሙስሊም ላልሆኑት ህዝቦች የሚኖራቸው የወደጅነት ስሜት እየቀነሰና በእነርሱ ላይ የሚኖራቸውም እምነት ምጸታዊ እየሆነ ይመጣል፡፡

የሸሪኣ ህግ ሙስሊሞችን እንዲዋሹ የሚያበረታታበት ሌሎች ሁኔታዎች በባልና በሚስት መካከል የጋብቻን ጥምረት ለማስቀጠል፣ ክርክሮችን ለመፍታት ጥረት በሚደረግበት ጊዜ፣ እውነቱን መናገር ራስን ለአደጋ ሊያጋልጥ በሚችልበት ሁኔታ ውስጥ፣ አንድ ሰው የግል ሚስጥሩን ሲነግረን እና በጦርነት ወቅት ነው፡፡

በአጠቃላይ ውሸትን በተመለከተ እስልምና የሚያስተምረው "ውጤቱ የተጠቀምክበትን መንገድ ያጸድቃል" በሚል መርህ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ አንዳንድ ምሑራን የተለያዩ ውሸቶችን በተመለከተ ደህና የሆኑ መለያዎችን አስቀምጠዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል ሙሉ በሙሉ ከመዋሸት የተሳሳተን መረጃ መስጠት የተሻለ ነው ብለው ያምናሉ፡፡

# በግብረ ገብነት የተጎዳ ማኅበረሰብ

እንደየሁኔታው የሚለዋወጥ የመዋሸትና እውነትን የመናገር ስነ ምግባር በጣም አውዳሚ ሊሆን ይችላል፡፡ መተማመንን አጥፍቶ ግራ መጋባትን ይፈጥራል፡፡ ሃገራዊና ፖለቲካዊ የሆነውን ባህል ያጠፋል፡፡ ባሎች በተደጋጋሚ ሚስቶቻቸውን የሚያታልሉ ከሆነ በመካከላቸው ያለውን መተማመን ክፉኛ ይሸረሽርና ትዳራቸውን ይጎዳል፡፡ በማኅበረሰብ ደረጃ የሚደረገው ህጋዊው ማታለል አንዳቸው በአንዳቸው ላይ ያለቸውን የመተማመን ህይወት እንዳይቀጥል እንቅፋት ይሆናል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ግጭቶች እንዲቀጥሉና እርቅን ማድረግ አዳጋች እየሆነ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡ አንድ ሰው እስልምናን በሚተውበት ጊዜ ይህንን የመሐመድ ምሳሌነት መከተል እንደሚያቆም የታወቀ ነው፡፡

# እስኪ ስለ ራስህ አስብ

ዕውቀት ከሚደራጅበትና ግልጽ እንዳይሆን ከሚደረግበት አካሄድ የተነሳ በአንዳንድ ርእሰ ጉዳዮች ላይ እስልምና በእርግጥ ምን እንደሚያስተምር ማወቅ አዳጋች ነው፡፡ የእስልምና ዋና ምንጭ ትልቅና ውስብስብ ነው፡፡ የሸሪአ ህግን አስመልክቶ መረጃዎች እንደ ዋና ምንጭ የተቀዱት ከቁርአንና ከነብዩ መሐመድ ፈለግ ነው፡፡ ሂደቱም በክህሎት የደረጀ እንደሆነ ይታሰባል፡፡ አንድ ሰው ስልጠናዎችን ለመውሰድ እረዥም ጊዜ ሊፈጅበት ይችላል፡፡ አብዛኛዎቹ ሙስሊሞች ግን ይሄንን ማድረግ አይችሉም፡፡ ይሄ ማለት ደግሞ ተግባራዊ ከሆነ አመለካከት ስንነሳ እምነትን አስመልክቶ ዓላማቸውን ከማሳካት አንጻር ሙስሊሞች ምሪትን የሚቀበሉት ከምሑራኖቻቸው ነው፡፡ በእርግጥ የእስልምና የህግ አዋቂዎች

እምነትን አስመልክቶ ምክር ለሚያስፈልጋቸው ሙስሊሞች ከነርሱ ይልቅ የኃይማኖት ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች ማናገር የተሻለ እንደሚሆን ያስገነዝባሉ፡፡ የሸሪአ ህግን አስመልክቶ ሙስሊሞች ጥያቄ ቢኖራቸው ህጉን በተመለከተ ተገቢ ዕውቀት ያለውን ሰው መጠየቅ ይኖርባቸዋል፡፡

የእስልምና ኃይማኖት ዕውቀት ሁሉን ነገር በግልጽ ከማስቀመጥ አንፃር ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር የተለየ አመለካከት ያለው ነው፡፡ በእስልምና አንዳንድ ነገሮች መገለጽ የለባቸውም ከተባለ ወይንም ደግሞ እነዚህ ነገሮች ኢስላምን መልካም ባልሆነ ብርሃን የሚገልጹ ከሆነ ለውይይት እንዲቀርቡ አይደረግም፡፡ ስለ እስልምና ያለው መረጃ ለማወቅ አስፈላጊ ነው ወይንስ አይደለም በሚል ጥያቄ ላይ ተመስርቶ እንደየሁኔታው ግልጽ ይደረጋል፡፡

ይህ ማለት ግን አሁን ያሉት ሙስሊሞችም ሆኑ ቀድሞ የነበሩት ስለ ቁርአንም ሆነ ስለ መሐመድ ፈለግ ምንም ዓይነት ግልጽ አስተሳሰብ እንዲያገኙ መብቱ የላቸውም ማለት አይደለም፡፡

አሁን ያለንበት ዘመን ከመቼውም ዘመን ይልቅ የመጀመሪያ የሆኑ ማሳረጃዎችን ማግኘት የሚቻልበት ሁኔታ ስላለ ክርስቲያኖች፣ አይሁዶች፣ እግዚአብሔር የለሾችም ሆኑ ሙስሊሞች የሚያውቁትን ነገር ለሌሎች ለማሳወቅ ማንኛውንም አጋጣሚ ሊጠቀሙ ይገባል፡፡

# ምዕራፍ 3

# የዲህማ ውል

እንደ ጎርጎሳውያኑ የዘመን አቆጣጠር በ2006 ዓ.ም የሮማው ካቶሊክ ጳጳስ የነበሩት ቤኒዲክት በብዙዎች ዘንድ የታወቀላቸወን የረጌንስበርግ ገለፃ አድርገው ነበር፡፡ የንግግራቸውንም ሀሳብ የወሰዱት ንጉስ ማኑኤል ሁለተኛ የተባሉት የመሐመድን በሰይፍ የታጀበ እምነትን የማሰራጫ ስብከት ትእዛዝ በተመለከተ የተናገሩትን በመጥቀስ ነበር፡፡

የጳጳሱ መልዕክት በዓለም ዙርያ ከሚኖሩ ሙስሊሞች ዘንድ ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞ አስነስቶ ነበር፡፡ አንድ ትኩረትን የሳበ ምላሽ የተሰጠው ግን የሳውዲ አረቢያው የእስልምና ህግጋትን የማስረዳት ስልጣን በነበራቸው ሼከ አብዱላዚዝ አል ሼክ ነበር፡፡ በወቅቱ ርዕሰ ጉዳዩን አስመልክቶ በነበረው ጋዜጣዊ መግለጫ “እስልምና ኃይልን በመጠቀም የተጀመረ ኃይማኖት አይደለም” ብለዋል፡፡ የሙግት ሀሳባቸውንም ሲያጠናክሩ “በዚህ ምክንያት እስልምናን መክሰስ ስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም በእምነት ጉዳይ አረመኔ መሆን የሚቻለው በሦስተኛ ምርጫ ነው፡፡ የመጀመርያው ምርጫ ሰላማዊ

ነው፡፡ ሁለኛተው ሰይፍ ማንሳት ነው፡፡” ሦስተኛውን እንዲህ ሲሉ ነበር ያስቀመጡት “እጅ እንዲሰጡ ማድረግና ቀረጥ ማስከፈል ከዚያም በቀዬአቸው ለመኖር ፈቃደኛ ይሆናሉ፡፡ ይሄንንም የሚያደርጉት ኃይማኖታቸው በሙስሊሞች የበላይ ጠባቂነት ስር መሆኑን ስለሚያጤኑ ነው”

የእስልምና ህግ አዋቂው ከመሐመድ ምሳሌ በመነሳት ያነበቡትን እንዲህ ሲሉ ያስቀምጣሉ “ቁርአንንና የመሐመድን ፈለግ ያነበበ ሁሉ አንድ የሚረዳው እውነት አለ” የህግ አዋቂው ለማመላከት የሞከሩት ሦስቱ ምርጫዎች እነዚህ ነበሩ፡፡

1) ወደ እስልምና መለወጥ
2) ሰይፍ (መግደል ወይም መገደል)
3) ለእስልምና ኃይል እጅ መስጠት

የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምርጫዎች ወደ መሐመድ የሚወስዱ ናቸው፡፡ እርሱም እንዲህ ነበር ያለው

> አላህ ትእዛዝን ሰጥቶኛል፡፡ ትእዛዙም ሰዎች ሁሉ ከአላህ በቀር ሊመለክ የሚገባው ሌላ ነገር እንደሌለ እስኪመሰክሩ ድረስ እንደዚሁም መሐመድ የአላህ መልዕክተኛ መሆኑን እስኪመሰክሩ ድረስ መዋጋት ነው፡፡ ይሄንን ማድረግ ከቻሉ እራሳቸውንም ንብረታቸውንም ከኔ ማዳን ይችላሉ፡፡

ነገር ግን ይህ አባባል እስልምናን ወይንም ሰይፍ ከመምረጥ፣ እጅ ከመስጠት እና ጀዝያን ከመክፈል በተጨማሪ መሐመድ በሰጠው ሌላ አማራጭ ተሻሽሏል፡፡

> በአላህ ስምና አላህ በሚፈቅደው መንገድ ተዋጉዋቸው በአላህ በማያምኑት ላይ ቅዱስ ጦርነት ክፈቱባቸው፡፡ መድበለ አማልክት የሚያመልኩትን ጠላቶቻችሁን ስታገኙአቸው ወደ ሦስቱም ዓይነቶች ግብዣ ጋብዙዋቸው፡፡ እነርሱ ከነዚህ መካከል ለአንዱ ምላሽን ቢሰጡ እናንተም በመቀበል ክፉ ከማድረግ ተቆጠቡ፡፡ እስልምናን እንዲቀበሉ ጋብዟቸው፡፡ ምላሽን የሚሰጧችሁ ከሆነ ተቀበሏቸው፣ እነርሱንም ከመዋጋት ተቆጠቡ... እስልምናን ለመቀበል እምቢ ካሉ ጅዚያን ጠይቋቸው፡፡ ለመክፈል ከተስማሙ ተቀበሏቸውና እጃችሁን ከነርሱ ላይ ሰብስቡ፡፡ ግብሩን የማይከፍሉ ከሆነ የአላህን እርዳታ በመፈለግ ተዋጓቸው፡፡

ሦስተኛውን ምርጫ አስመልክቶ ዋና ሙፍቲ ደርሼበታለሁ የሚሉት "እውነታ" እንደሚያሳየው የቁርአንና የመሐመድን ፈለግ በተመለከተ ታላላቅ የእስልምና ተንታኞች ትርጓሜዎች እንደሚገልጹት ከሆነ ሙስሊም ያልሆኑት ሰዎች እንኳን በታሪክ ውስጥ በሸሪአ ህግ የተገዙበት ጊዜ ነበር፡፡

ኢስላማዊ ለሆነው አገዛዝ እጃቸውን የሰጡ ማኅበረሰቦች አስገዳጅ በሆነ የቃል ኪዳን ውል የዲህማን ውል እንደተቀበሉ ይቆጠራሉ፡፡ በዚህ ውል መሰረት ሙስሊም ያልሆኑት ማኅበረሰቦች እጃቸውን በመስጠት የሚገቡት ግዳጅ ያለበት ቃልኪዳን በዝቅተኝነት የተሸነፉ ከመሆናቸውም በተጨማሪም አመታዊ ግብር ለሙስሊሞች እንዲከፍሉ ይገደዳሉ፡፡ እንደዚሁም ሙስሊም ያልሆኑት ድል ከመደረጋቸው በፊት የነበራቸውን እምነት እንዲከተሉ ይፈቀድላቸዋል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የሚያልፉ ሙስሊም ያልሆኑ ህዝቦች በግዳጅ የተጨቆኑ ይባላሉ፡፡

ይህ የማስገደድ ሥርአት ቁርአንን መሰረት ያደረጉ ሁለት መሰረታዊ ፖለቲካዊ መርህ ያላቸው መግለጫዎች አሏቸው፡፡

4) እስልምና በሌሎች ኃይማኖቶች ላይ ድልን መቀዳጀት አለበት (48፡28)

5) እኩይና ሰናይ የሆነውን አስተምህሮ በተመለከተ ሙስሊሞች በኃይል የበላይ በመሆን ሊቆጣጠሩት ይገባል፡፡ (3፡110)

# የጂዝያ አከፋፈል ስርአት

የእስልምና ህግ - የሸሪአ ህግ የዲህማ ውል እስልምናን ያልተቀበሉትን ሰዎች ሙስሊሞች ባይተውአቸው ኖሮ መሞት የሚገባቸው እንደሆኑ ይቆጥራቸዋል፡፡ ቀድሞ ከእስልምና በፊት የነበረውን አስተሳሰብ በምንመለከትበት ጊዜ ሰዎችን ድል ማድረግ ከቻልክ እና እንዲኖሩ ብትፈቅድላቸው የአንተ ባለ እዳዎች ሆነው ይቀጥላሉ የሚል አንደምታ ነበረው፡፡ በዚህም ምክንያት ተገደው የሚከፈለውን አመታዊው የቀረጥ ሥርአት እንዲከፍሉ የሚደረጉት በእስልምና መንግስት ስር ያሉ አዋቂ ወንዶች ናቸው፡፡

እንደ የእስልምና መዝገበ ቃላት አዘጋጆች ግላዬ ከሆነ ጂዝያ ማለት፡

> ...በእስልምና መንግስት አስተዳደር ስር ያሉ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች የስምምነት ውሉ እንዲጸድቅ ይስማማሉ (በማስገደድ የሚደረግ ውል)፡፡ ይሄ ደግሞ ጥበቃን ያረጋግጥላቸዋል፡፡ እንደዚህ የሚደረግላቸውም እንደ ካሳ ስለሚቆጠርላቸው ነው፡፡ (ሌን የአረቢኛ- እንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት)

አርነት በምርኮ ውስጥ ላሉት

በ19ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ አልጄሪያዊ ተንታኝ አት-ፋይሽ ይሄንን መርህ በማብራሪያ መፅሐፋቸው የአት ተውባህ 9፡ 29ን ሀሳብ እንደገለጹት

> “እንደዚህ ተብሎ ነበር፡ (ጂዝያ) ለደማቸው እርካታ የሚሰጥ ነው፡፡ እገሌ ላለመገደሉ የሚገባውን ሂሳብ ከፍሏል ይባላል፡፡ ዓላማውም የመግደልና ባሪያ የማድረግ ሥራቸውን ለማካካስ ነው፡፡ ይሄ የተደረገው ከሙስሊሞች ጥቅም አንፃር ነው፡፡”

ወይንም ዊሊያም ኢቶን ከአንድ ክፍለ ዘመን ቀደም ብሎ አጭርና የተሟላ ማብራሪያ በሚሰጠው *“የቱርክ ግዛት አሰሳ”* በተሰኘ (በ1979 በታተመ) መጽሐፋቸው እንደተናገሩት ፡

> “ቋሚ የሆነውን ቀረጥ (ጂዝያ) በሚከፍሉበት ወቅት ለክርስቲያን ተገዢዎች የተሰጠው ስያሜ በራሱ የሚያመለክተው የተከፈለው ገንዘብ በዚያ ዓመት ጭንቅላታቸው ከአንገታቸው ሳይለያይ እንዲሄዱ ስለተፈቀደላቸው የከፈሉት ማካካሻ እንደሆነ ነው፡፡”

ሦስተኛው ምርጫ የአመታዊው ጂዝያ የአከፋፈል ሥርአት ከበድ ያለ ትዕምርታዊ መልዕክት የተገለጸበት መንገድ ነው፡፡ ዲህሚ የሆኑ ወንዶች ይሄንን ሥርአት እስከ አሁኗ ሰአት ድረስ በመላው የእስልምና ሀገራት ሁሉ እንዲተገብሩ ይጠየቃሉ፡፡ አንገታቸው ላይ አንዴ ወይንም ሁለት ጊዜ እንዲመቱ ይደረጋል፡፡ በገመድ አንገት ላይ የመታሰር ሥርአትም ይደረጋል፡፡ ይሄ የሚያመለክተው ያ ሰው በእድሜ ዘመኑ ሁሉ ቀረጥ ለመክፈል ራሱን ማስገዛቱን ነው፡፡ ሥርአቱ የጂዝያ ክፍያን በተመለከተ የተደነገገ የሞት

ቅጣትን በይቅርታ ያልፋል፡፡ ሦስተኛው ምርጫ ይሄንን የሰዎችን መሰዋት አስመልክቶ ደርዘን የሆኑ ማጣቀሻዎችን ያቀርባል፡፡ ይሄም ደግሞ ከሞሮኮ እስከ ቡካራ ከ 9ኛው -20ኛው ክፍለ ዘመን ኢስላማዊና ኢስላማዊ ካልሆኑ ምንጮች የተወሰደ ነው፡፡ ይሄኛው ሥርአት በአንዳንድ የእስልምና አገራት ማለትም የመንና አፍጋኒስታን አይሁዶች ወደ አገራቸው እስከተመለሱበት በ1940ዎቹ መጨረሻና በ1950ዎቹ መጀመሪያ ቀጥሏል፡፡ በቅርብ ጊዜ ባሉት ዓመታት ወደ ድሮው አካሄድ ለመመለስ ብዙ ጥሪዎች እየተደረጉ ናቸው፡፡

ሙስሊም ያልሆኑትን ማንነት በተመለከተ ማንነታቸው የሚወሰነው ድል ባደረጓቸው ሙስሊሞች እጅ ስር ይሆናል ማለት ነው፡፡ የእስልምና ተንታኞች እነዚህ ሰዎች የማመስገንና በትህትና ዝቅ የማለትን አመለካከትን ከራሳቸው ጋር ሊያዋህዱት ይገባል በሚለው እሳቤ ወጣ ያለ አቋም አላቸው፡፡

አብዛኛዎቹ የሸሪአ ህጎች የተቀረጹት ሙስሊም ያልሆኑት በበታችነት እንዲሸማቀቁና አደጋ የተጋረጠባቸው መሆኑን እንዲያውቁ በሚያስገነዝብ መልኩ ነው፡፡ እንደምሳሌ አድርገን ብንወስድ

- በዲህሚ የጭቆና በደል ውስጥ ያሉት በሸሪአ ፍርድ ቤት ተቀባይነት የላቸውም፡፡ ይሄ ደግሞ በሁሉም አቅጣጫ አደጋ ላይ መሆናቸውን ጠቋሚ ነው፡፡
- በዲህሚ የጭቆና አሰራር ስር ያሉት ቤታቸውን ከሙስሊሞች በላይ ከፍ አድርገው እንዲሰሩ አይፈቀድላቸውም፡፡
- በዲህሚ የጭቆና አገዛዝ ስር ያሉት ፈረስ እንዲጋልቡና እራሳቸውን ከሙስሊሞች በላይ ከፍ አድርገው እንዲሄዱ አልተፈቀደላቸውም፡፡

አርነት በምርኮ ውስጥ ላሉት

- በዲህሚ ባርነት ውስጥ ያሉት እራሳቸውን ከሙስሊሞች ጥቃት እንዲከላከሉ አልተፈቀደላቸውም፡፡ ይሄ ደግሞ ከሙስሊሞች ለሚሰነዘርባቸው ማንኛውም ዓይነት ጥቃት ተጋላጭ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡
- ማንኛውም ኃይማኖትን የሚያሳዩ ምልክቶች እንዲያስተዋውቁ አይፈቀድላቸውም፡፡
- በእስልምና ላይ የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ትችት አይፈቀድም፡፡
- በዲህሚ ጭቆና ውስጥ ያሉት ለየት ያለ አለባበስ መልበስ አለባቸው፡፡ የቀለም አመራረጣቸው ኢስላማዊ ቃና እንዲኖረው ይጠበቃል፡፡
- ሙስሊም ያልሆኑትን ዝቅ ብለው እንዲገዙ የሚያስገድዱና ከሙስሊሞቹ የሚለዩ ብዙ ህጎች ተደንግገዋል፡፡

እነዚህ ህጎች በማኅበራዊና ህጋዊ አገላለፆች "አናሳዎች" ናቸው የሚል አንድምታ ይሰጣሉ (9፡29)፡፡

የዲህሚ ሥርአት ሙስሊም ያልሆኑትን ማኅበረሰቦች የበላይነት ለመቀነስ የተቀረጸ አካሄድ ነው፡፡ በ18ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩት ሞሮኮዋዊው ተንታኝ ኢብን አቢጃ እንደ ገለጹት ዓላማው ምድራዊ ያልሆነ ምንባብ፣ የተተረጎመና ለመጀመሪያ ጊዜ ሦስተኛው ምርጫ ተብሎ የታተመና ነፍስን የሚገድል ነው፡፡

የዲህማ ውልን አስመልክቶ ታዋቂ ምሳሌ የሚሆነው የዑመር ቃልኪዳን በመባል የሚታወቀው ክርስቲያኖች ይሄ ቅጣት በራሳቸው ላይ እንዲሆን የሚለምኑበት አካሄድ ነው፡፡

> እነዚህ ለደህንነታችን ስንል በራሳችንና የኛን እምነት በሚከተሉ ሰዎች ላይ የደነገግናቸው አኳሆኖች ናቸው፡፡ ለናንተ ጥቅም ስንል በራሳችን ላይ የደነገግናቸውን እነዚህን ደንቦች ጥሰን ብንገኝ የኛ ዲህማ ተሰብሯል ማለት ነው እናም በማይታዘዙ እና በአመጸኞች ሕዝቦች ላይ እንድታደርጓቸው የተፈቀዱትን ነገሮች ሁሉ በኛ ላይ ልታደርጉ ትችላላችሁ፡፡

በኢብን ቁዳማም ተመሳሳይ የሆነ ነጥብ ቀርቧል፡፡ የዲህማ ውሉን በተመለከተ የዲህማ ውሉ ሳይጠበቅ ቢቀር ዲህሚው ንብረቱንና ሕይወቱን ያጣል፡፡

> በከለላ ውስጥ ያለ፣ ነገር ግን የከለላ ስምምነቱን ደንብ የጣሰ ሰው በግዳጅ የሚከፍለውን ቀረጥ (ጂዝያ) ባይከፍል ወይንም ለማኅበረሰቡ ህግ መገዛትን ባይወድ ራሱን እና ንብረቱን ሕገወጥ ያደርጋል (ሐላል - በሙስሊሞች ለመገደል ወይንም ለመያዝ ራሱን በነፃ ያቀርባል)፡፡

በቅጣት ምክንያት ራስን የመሰዋት ድንጋጌ ባለበት ስርአት የጂዝያ ክፍያ እንደ "የደም ውል" ወይንም "የደም ቃልኪዳን" ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ተሳታፊዎችም በራሳቸው ላይ ሞትን የሚቀሰቅሱና የመሞቻ መንደጋቸውንም የሚጠርጉ ናቸው፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ የገቡትን ውል መጠበቅ በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ነው፡፡

እንደዚህ ዓይነቱ ቃል ኪዳን ለምዕተ ዓመታት ሚስጥራዊ በሆኑ ማኅበረሰቦችና በጥንቆላ ቡድኖች ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ሰዎች እንዲገዙና እንዲታዘዙ የስነልቦናና መንፈሳዊ ኃይልን ተጠቅሞ እንቅስቃሴያቸውን በማሰር የበላይነትን የማግኛ መንገድ ነው፡፡

የጂዝያ ስርአት ምስሌያዊ በሆነ መልኩ የዲህሚን ፈቃድ ይጠይቃል፡፡ እንደዚህም ሲባል የዲህሚን ህግ የሚተላለፍ የሚከፍለውን የቅጣት ካሳ የሚያሳይ ነው፡፡ ማለትም በእድሜ ዘመን ሁሉ የሚደረግ ቅጣት ነው፡፡ ይህ ማለት እራስን መርገም ማለት ነው፡፡ ሂደቱም "ከገባሁት ኪዳን አንዱን ብሰብር ጭንቅላቴን(ራሴን) የመቁረጥ ሙሉ መብት አለህ" እንደማለት ነው፡፡ ስለሆነም አንድ ሰው የዲህሚን ህግ ቢተላለፍ በራሱ ላይ የሞት ቅጣት እንደወሰነ ይቆጠራል፡፡

ሦስተኛውን ምርጫ በተመለከተ የዲህሚ ማኅበረሰቦች በነሱ ላይ የሚታወጅባቸውን ጂሃድ እስከ ምን ድረስ እንደሚታገሱ አያሌ ምሳሌዎች አሉ፡፡ ሰዎቹ የዲህሚን ህግ ይጥሳሉ ወይንም እውነታውን ይገነዘባሉ፡፡ የአብዛኛዎቹን የዲህሚ ማኅበረሰብ ታሪክ በምንመለከትበት ጊዜ እጅግ አሰቃቂ የሆኑ ታሪካዊ ድርጊቶች እንደተከናወኑ መመልከት እንችላለን፡፡ ለምሳሌ ያህል ጭፍጨፋ፣ አስገድዶ መድፈር እና ንብረትን መዝረፍ የተደረገባቸው ሲሆን ሙስሊም ባለመሆናቸው ብቻ ወንጀል ተፈጽሞባቸው በዝቅተኛነትና በመንፈሳዊ ቀንበር ውስጥ ገብተውና ስነልቦናቸው ተጎድቶ በኅብረተሰቡ ውስጥ እንዲመላለሱ ተደርጓል፡፡

# ዲህማዊነት

ዲህማዊነት (ዲህሚቲውድ) የሚለው ሀሳብ አጠቃላይ ሁኔታው የዲህማ ቃልኪዳን የሚያስከትላቸውን አጠቃላይ አኳኋኖች ይገልጻል፡፡ ጾታዊነትና ዘረኝነትን መግለጽ እንደሚቻለው ዲህማዊነትን በህጋዊና ማህበራዊ መዋቅር ብቻ መግለጽ አይበቃም ነገር ግን በበታችነት ስነ ልቦና እና የተጨቆነ ማህበረሰብ ነገን ለማየት

ካለው ፍላጎት የተነሳ ራሱን ዝቅ አድርጎ ለማገልገል ባለው ፍቃደኝነትም ጭምር ነው፡፡

የመካከለኛው ዘመን ታዋቂው አይሁዳዊ ሊቅ ሜሞንዲስ "ባናምንበትም አዋቂውንም ወጣቱንም ተቀብለናል የትህትናን ህይወት ራሳችንን አለማምደናል" ሲል ሀሳቡን ያስቀምጣል፡፡ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ይኖር የነበረው ጆቫኒ ሲቪልጂክ የተባለ ሰው እንደገለጸው የቱርኮችንና የአልባኒያ ሙስሊሞችን ገዢነትና የኃይል ጥቃትን መፍራት ለትውልድ እየተላለፈ መምጣት በባልካን አካባቢ ለሚኖሩ ክርስቲያኖች የስነልቦና ተፅዕኖ ነበረው፡

> የበታችነት ስሜት የሚሰማቸው፣ ባርያ ተብለው ስም የተሰጣቸው ፤ ዋና ስራቸውም በጌታቸው ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት፣ በፊቱ ዝቅ ማለትና እርሱን ማስደሰት ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች አፋቸው የሚዘጋ ፣ ሚስጥረኞች፣ ጮሌዎች፣ በሌሎች ላይ እምነት መጣል የማይችሉ ግብዞችና የማምለጫ መንገድ የሚቀይሱ ናቸው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ በሰላም ለመኖርና የሚደርስባቸውን ኃይለኛ ቅጣት ለማስወገድ ነው፡፡ ቀጥተኛ የሆነው ጭቆናና በኃይል ማጥቃት በሁሉም ክርስቲያኖች ዘንድ በሚባል መልኩ የፍርሃትና የጭንቀት ስሜት እንዲሰማቸው ትልቅ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ ጆቫኒ አያይዘው እንደሚናገሩት በሜቄዶኒያ በነበርኩ ጊዜ ሰዎች "በህልማችን እንኳን ሳይቀር ቱርካውያንና አልባናዊያን ሲያባርሩን እናልማለን" ብለው ሲናገሩ ሰምቻለሁ፡፡

በዲህሚ ህግ ሙስሊም ያልሆኑት በዝቅተኝነት ስሜት ውስጥ ሲገቡ ሙስሊም የሆኑት ደግሞ የበላይ እንደሆኑ ይታሰባል፡፡ ሙስሊሞቹ ቸርነትን የሚያደርጉ እንደሆኑ ተደርጎም ይቆጠራል፡፡ ቀድሞ ሙስሊም የነበሩና ወደ ክርስትና የተለወጡ ኢራናዊ ሰው ይህንን አስመልክቶ እንዲህ ነበር ያሉት "አሁንም ክርስትና የሚታየው የበታች የሆኑ ሰዎች ኃይማኖት እንደሆነ ነው፡፡ እስልምና የጌቶችና የገዢዎች ኃይማኖት ነው፡፡ ክርስትና የባሪያዎች ኃይማኖት ነው"፡፡

እስልምናን ያልተቀበሉትን መጨቆን የሚለው ንጽረተ ዓለም ሙስሊም ያልሆኑትን የበታች የሚያደርግ ጎጂ ልማድ ነው፡፡ ሙስሊሞች ተፎካካሪ ለመሆን የሚማሩበት ሁኔታ ካልተፈጠረ ራሳቸውን ይጎዳሉ፡፡ ይሄም ደግሞ መሰረታዊ ችግር ነው፡፡ በኃይማኖት ሰበብ ሀብትን የመቆጣጠር አካሄድና ጭቆናዊ አገዛዝ ሙስሊሞችን ሀሰት ወደ ሆነ የበላይነት ስሜት ላይ እንዲታመኑ ከማድረጉም በተጨማሪ ኋላ ላይ እያደከማቸው ይሄዳል፡፡ የሚያመጣውም ጥፋት እነርሱ ስለ ራሳቸውና ስለ ዓለም የሚኖራቸው መረዳት የተዛባ እንዲሆን ማድረጉ ነው፡፡

# በምዕራቡ ዓለም ያለ ጭቆና

በሦስተኛው ምርጫ ላይ ከተደነገጉት ነጥቦች አንደኛው ምንድነው? ብለን የጠየቅን እንደሆነ የአመለካከት መዛባትን ጠብቆ የሚያስኬድ ሂደት ነው፡፡ የምዕራቡ ዓለም ህዝቦች የጭቆና አገዛዝን አስመልክቶ ያላቸው ንፅረተ ዓለም እየጨመረ እንደመጣ መመልከት ይቻላል፡፡ ይሄ ደግሞ የተገለጠበትን ሁኔታ እንደ ምሳሌ አድርገን ብንወስድ በምዕራቡ ዓለም የሚኖሩ መሪዎች እስልምናን ሲያሞጋግሱ ማየት የተለመደ መሆኑ ነው፡፡ ይሄ ብቻም ሳይሆን የሰላም ኃይማኖት

እንደሆነም ያውጃሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩም ለእስልምና ያላቸውን ምስጋናም ይገላጻሉ፡፡ ይሄንን ሀሳብ እንደ ማስረጃ ለማቅረብ እንደ ጎርጎሮሳውያኑ አቆጣጠር በ2009 ዓ.ም. የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ በካይሮ ባደረጉት ንግግር "የስልጣኔ ባለውለታው እስልምና ነው" ሲሉ ተደምጠዋል፡፡

በዲህሚ የአገዛዝ ጭቆና ስር ያለ ሰው የሚሰማው ስሜት ቢኖር ድል ላደረጉት ሰዎች ህይወቱን አሳልፎ መስጠት እንዳለበት ነው፡፡ እንግዲህ ከዚህ የጭቆና አገዛዝ ጋር የተያያዘው ስልጣኔ የእስልምናን ባለውለታነት አመላካች ነው ተብሎ ታምኗል፡፡

የዚህ የጭቆና አገዛዝ ንጽረተ ዓለም የተገለጠበት ሌላው መልኩ ደግሞ በማያቋርጥ ሁኔታ ታሪካዊና ስነመለኮታዊ አካሄድን የሚክዱበት መንገድ ነው፡፡ ክህደቱ ደግሞ አስተማሪ የሆኑ መረጃዎችን የሚደመስስና ፖለቲካዊ ንግግር ያለው ነው፡፡

በምዕራቡ ዓለም ያለ የጭቆና አገዛዝ አዲስ የሚባል ክስተት አይደለም፡፡ በአውሮፓ ያሉትን አብዛኛዎቹን አገራት ስንመለከት ጂሃድ ታውጆባቸው ሲሰቃዩ መኖራቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ እንደ ፈረንሳይ፣ ጣሊያን፣ ስፔይን፣ አየርላንድ እና እንግሊዝ ያሉ አገራት ህገ ወጥ የጂሃድ ጥቃት ሰላባዎች መሆናቸው እየታየ ነው፡፡

ምንም እንኳ የጂሃድን ሽብር መፍራት ለአውሮፓውያን አዲስ ክስተት ባይሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየጨመረ ለመጣው የጂሃድ ሽብር ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳበረከተ ያለጥርጥር የሚታመነው በምዕራቡ ዓለም ያለው እስልምናን ባልተቀበሉት ላይ የተጣለው የጭቆና አካሄድ ነው፡፡

# ኃይማኖታዊ ስደትና የዲህማ መመለስ

በ19ኛውና በ20ኛው ምዕተ ዓመታት የተለያዩ የአውሮፓ ኃይላት የሙስሊሙን ዓለም ዝቅ ለማድረግና ጨቁኖ የመግዛት ስርአታቸውንም ለማጥፋት ያላሰለሰ ጥረት አድርገዋል፡፡ ቢሆንም ተፅዕኖ ማድረግ፣ ዝቅ አድርጎ ማየትና የኃይማኖት አድሎ ማድረግ ሙስሊሞች በሚበዙበት አገራት እየጨመረ መቷል፡፡

በፓኪስታን፣ በኢራቅ፣ እንደዚሁም በግብፅ በክርስቲያኖች ላይ እየደረሰ ያለውን አደጋ አይተው እንዳላዩ ሆነው ማለፋቸው ይሄ የጭቆና አካሄድ ከእለት ወደ እለት እያደገ እንዲመጣና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፅዕኖ እንዲያሳድር ምክንያት ሆኗል፡፡

# ምዕራፍ 4

# መሐመድና ውግዘት

መሐመድ የእስልምና አካል የተመሰተረበት መሰረት ነው፡፡ ይሄ ምዕራፍ ደግሞ የመሐመድን ግለ ታሪክ አስመልክቶ አጠቃላይ የሆኑ ገጽታዎችን ለመቃኘት ይሞክራል፡፡ ይሄም ደግሞ ሰዎችን በማስገደድ ኃይማኖቱን እንዲቀበሉ ያደረገበትንና የእስልምና መርሆዎችን ያካተተ ነው፡፡

## የአስቸጋሪው ነገር ጅማሮ

መሐመድ የተወለደው በ570 ዓ.ም የአረብ ጎሳ ከሆኑት ቤተሰቦቹ በመካ ነው፡፡ አባቱ አብደላ ቢን አብድ ሙታሊብ የሞተው መሐመድ ከመወለዱ በፊት ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ በጨቅላነት ጊዜው ሌሎች ቤተሰቦች እንዲያሳድጉት ተላልፎ ተሰጠ፡፡ የስድስት ዓመት ህፃን ሳለም እናቱ በሞት ተለየች፡፡ ከዚህም የተነሳ አያቱ እርሱን የማሳደጉን ኃላፊነት ወሰዱ፡፡ አሳዛኙ ነገር አያቱም የስምንት ዓመት ልጅ ሳለ

የሞትን ጽዋ ተጎነጩ፡፡ በመሆኑም መሐመድ ከአባቱ ወንድም ከአቡ ጧሊብ ጋር እንዲያድግ ተደረገ፡፡ የአጎቱንም ግመሎችና በጎች እንዲጠብቅ ሀላፊነት ተሰጠው፡፡ የቱንም ያህል ሌሎቹ የመሐመድ አጎቶች ሀብታም ቢሆኑም እሱን መርዳት ግን አልቻሉም ነበር፡፡

ቁርአን በቅጽል ስሙ አቡ ላሀብ (የነበልባል አባት) ብሎ ስለሚጠራው የመሐመድ አጎት በመሐመድ ላይ ስለነበረው ንቀትና ጥላቻ መጠነኛ ሀሳብ አለው፡፡

> የአቡ ለሀብ ሁለት እጆች ከሰሩ (ጠፉ፤ እርሱ) ከሰረም፡፡
>
> ከርሱ ገንዘቡና ያም ያፈራው ሁሉ ምንም
> አልጠቀመውም፡፡
>
> የመንቀልቀል ባለቤት የኾነችን እሳት
>
> በእርግጥ ይገባል፡፡
>
> ሚስቱም (ትገባለች)፤ እንጨት ተሸካሚ ስትኾን
>
> በአንገትዋ ላይ ከጭረት የኾነ ገመድ
>
> ያለባት ስትኾን፡፡ (111፡1-5)

## ያለ እቻ ጋብቻ

ከድጃ የጋብቻን ጥያቄ ባቀረበችለት ጊዜ መሐመድ የሃያ-አምስት ዓመት ወጣት ነበር፡፡ በአስራ አምስት ዓመት ትበልጠውም ነበር፡፡ አባቷም ጋብቻውን ይቃወም ይሆናል የሚል ስጋት ነበራት፡፡ ስለሆነም አባቷ መጠጥ ጠጥቶ በነበረበት ወቅት ከመሐመድ ጋር ተጋባች፡፡ አባቷም ወደ ማስተዋል ሲመጣ የተደረገውን ስለተረዳ ተበሳጨ፡፡ በአረብ ባህል ባል ለሚስት ጥሎሽ እንዲሰጥ

ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን በወቅቱ ከድጃ ኃይለኛና ኃብታም ስለነበረች ይሄ ስርአት አልተከበረም ነበር፡፡

የመሐመድ ግለ ታሪክ ጸሐፊ የነበረው ኢብን ኢስሃቅ ከድጃን “የክብርና የሀብት ሴት” በማለት ነበር የገለጻት፡፡ ድኻ የነበረውንም መሐመድ መቀበል ችላ ነበር፡፡ ከድጃ ከመሐመድ በፊት ሁለት ጊዜ አግብታ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ ጋብቻን አስመልክቶ ከነበረው መረዳት የተቃረነ ነበር፡፡ በሁለቱ መካከል የነበረውን ስምምነት በተመለከተ ግጭት የነበረበት ነበር፡፡

## ወላጅን በሞት መነጠቅ

ከድጃና መሐመድ ስድስት ልጆች ነበሯቸው (አንዳንድ መረጃዎች ሰባት እንደነበሩ ይጠቅሳሉ)፡፡ መሐመድ አስቀድሞ ሦስት ወንዶች ልጆች ነበሩት ነገር ግን ገና በጨቅላነታቸው ነበር የሞቱት ይሄ ደግሞ በመሐመድ የቤተሰብ ህይወት አሳዛኝ ነገር መሆኑ አልቀረም፡፡

## የቤተሰብ ህይወትን አስመልክቶ የነበረ አሳማሚ ልምምድ

በአጠቃላይ ለመደምደም ያህል የመሐመድ የቤተሰቡን ሁኔታ በምንመለከትበት ጊዜ እጅግ ብዙ የሚያሳምሙና የሚጎዱ ሁኔታዎችን ማሳለፍ ችሎ ነበር፡፡ ወላጅ አልባ መሆን፣ አያትንም በሞት ማጣት፣ በድህነት ውስጥ ማለፍ፣ የባለቤቱ አባት ጠጪ መሆን፣ ሀይለኛ በሆኑት ዘመዶች ይደረግበት የነበረው ጥላቻ ከብዙ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ አጎቱ አቡ-ጧሊብ ያደረገለት እርዳታ እና ባለቤቱ ከድጃ እሱን ለጋብቻ በመምረጥዋ ከድህነት ለመላቀቅ ችሎ ነበር፡፡

# አዲስ ኃይማኖት ተመሰረተ

መሐመድ የአርባ ዓመት ጎልማሳ በነበረ ጊዜ የመንፈስ ጉብኝት ልምምድ እንዳገኘው ይናገራል (እሱ እንደሚለው ከሆነ ጂብሪል የተባለ መልአክ ሲሆን) በመጽሐፍ ቅዱስ ገብርኤል ተብሎ የተጠቀሰው እንደ ማለት ነው፡፡

## ራስን አለመቀበል

በዚህ የመንፈስ ጉብኝት የመሐመድ መንፈስ ክፉኛ ተረብሾ ነበር፡፡ ተቆጣጥሮት በነበረውም መንፈስ ተደምሞ ነበር፡፡ እራሱንም ለመግደል ጥረት አድርጎ ነበር፡፡ ይሄንን አስመልክቶ እንዲህ ብሎ ነበር፡

> "ወደ ተራራ ጫፍ ላይ እወጣለሁ፣ እራሴንም ወደ ታች ወርውሬ እገድላለሁ፣ ከዚያም እረፍት አገኛለሁ፡፡"

በዚህ ወቅት ባለቤቱ ከድጃ ከደረሰበት ጭንቀት አፅናናችው ክርስቲያን ወደ ነበረውና ዋራቃ ወደተባለው የአጎቷ ልጅ ቤትም ወሰደቸው፡፡ እርሱም ያበደ ሰው ሳይሆን ነብይ መሆኑን አሳወቃቸው፡፡

ከዚህ በኋላ ለመሐመድ የተገለጠለት ነገር በመቆሙ ምክንያት እንደገና ራሱን ማጥፋት ፈልጎ ነበር፡፡ በተደጋጋሚ ራሱን ከተራራ ላይ ጥሎ ለመሞት ሙከራ እያደረገ ሳለ አንድ ቀን ጂብሪል ተገልጦ " መሐመድ ሆይ! አንተ በእርግጥም እውነተኛ የአላህ መልዕክተኛ ነህ" አለው፡፡ መሐመድ የተጭበረበረና የተተወ ስለመሰለው እጅግ

ፈራ፡፡ ቀድሞ በነበሩት ሱራዎች አላህ መሐመድን እንደማይጥለው አስረግጦለታል፡፡

> ጌታህ አላሰናበተህም፤ አልጠላህምም፡፡ መጨረሻይቱም (ዓለም) ከመጀመሪያይቱ ይልቅ ላንተ በላጭ ናት፡፡ ጌታህም ወደ ፊት (ብዙን ስጦታ) በእርግጥ ይሰጥሃል፤ ትደሰታለህም፡፡ የቲም ኾነህ አላገኘህምና አላስጠጋህምን? (አስጠግቶሀል)፡፡ (93፡3-6)

የእስልምናው ማኅበረሰብ በመጀመሪያ ቀስ በቀስ ነበር ያደገው በመጀመሪያ ወደ እስልምና የተለወጠችው ከድጃ ነበረች፡፡ በመቀጠለም የአጎቱ ልጅ የነበረው እና በመሐመድ ቤት ይኖር የነበረው ወጣቱ አሊ ነበር፡፡ ከዚያም ብዙ ድሆች፣ ባሪያዎች ወይንም ከባርነት ነፃ የወጡ ሰዎችም ተከታዮቹ ሆኑ፡፡

# የመሐመድ የራሱ ጎሳ

በመጀመሪያዎቹ አካባቢዎች ይሄ አዲሱ ኃይማኖት በተከታዮቹ ዘንድ በሚስጥር ተይዞ ነበር፡፡ ነገር ግን ከሦስት ዓመት በኋላ መሐመድ ከአላህ ዘንድ በአደባባይ ግለጠው የሚል ቃል መጣለት፡፡ ይሄንንም የቤተሰብ ጉባኤ በማዘጋጀት ዘመዶቹ እስልምናን እንዲቀበሉ ጥሪ አደረገላቸው፡፡ የቁረይሽ ነገድ የሆኑት የሃገሩ ሰዎች በመጀመርያ የመሐመድን ንግግር ለመስማት ዝንባሌ አሳይተው ነበር፡፡ ይህ ግን አማልክቶቻቸውን መቃወም እስካልጀመረበት ጊዜ ድረስ ብቻ ነበር የዘለቀው፡፡ ከዚህ በኋላ ኢብን ኢስሃቅ እንደዘገበው ሙስሊሞች “የተናቁ አናሳዎች” ሆነው ነበር፡፡ ውጥረቱ ከፍተኛ ሆኖ ነበር፡፡ በሁለቱም በኩል ውጤቱ መጥፎ ሆኖ ነበር፡ ተቃውሞው እየተጠናከረ ሄደ፡፡

የመሐመድ አጎት አቡ ጧሊብ ከተቃዋሚዎች ጥቃት ከለላ ሆነው፡፡ መካ የነበሩትም ወደ አጎቱ ዘንድ መጥተው “አቡ ጧሊብ ሆይ የአባትህ ወንድም ልጅ አማልክቶቻችንን አረገሚል፡፡ ኃይማኖታችንንም ተሳድቧል፡፡ በሕይወት አካሄዳችንም ተሳልቋል፡፡ አንድም እንድታስቆመው ይገባል፡፡ አሊያም ጉዳት እንድናደርስበት ልትፈቅድልን ይገባል፡፡” ሲሉ ነገሩት አቡ ጧሊብ ግን በሀሳባቸው አልተስማማም፡፡

የመሐመድን አዲስ ኃይማኖት ያልተቀበሉት አረቦች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋም በመመስረት በመሐመድ ነገድ ላይ አድማ መቱ፡፡ ይሄም ደግሞ ምንም ዓይነት ጋብቻ ከነርሱ ጋር ላለመጋባትና የንግድ ልውውጥን አለማድረግን የሚያጠቃልል ነው፡፡

ይሄ ስድብና አደገኛ ሁኔታ መሐመድ በቅርብ ዘመዱም ተደርጎበታል፡፡ በራሱ ላይ ቆሻሻ ደፍቶበታል፡፡ ሶላት በሚያደርግበት ጊዜም የእንስሳ አንጀትም ወርውሮበታል፡፡ ስደቱ እየተጠናከረ ሲሄድ ሰማንያ -ሦስት ሙስሊም ወንዶች ከነቤተሰቦቻቸው የክርስቲያን አገር ወደ ሆነችው ኢትዮጵያ ተሰደዋል፡፡ በዚያም መጠለያ የተሰጣቸው ሲሆን ጥበቃም ተደርጎላቸዋል፡፡

## ራስን መጠራጠር

አንድ ወቅት መሐመድ ከ*ቁራይሾች* ከደረሰበት ተፅዕኖ አንፃር አሃዳዊ አምላክን ከማምለክ መወላወል ውስጥ ገብቶ ነበር፡፡ መሐመድ አማልክቶቻቸውን የሚያመልክ ከሆነ እነሱም አላህን እንደሚያመልኩ ጥያቄ አቅርበውለት ነበር፡፡ ነገር ግን በሱረቱ አል-ካፊሩን 109፡6 መሰረት “ለናንተ ኃይማኖታችሁ አለላችሁ፤ ለኔም ኃይማኖቴ አለኝ”

ሲል ሀሳባቸውን ተቃወመ፡፡ ነገር ግን በአልጠባሪ ዘገባ መሰረት መሐመድ ራሱን ተጠራጥሯል፡፡ የሰይጣን ጥቅሶች በመባል የሚታወቀው አን ነጅም ምዕ 53 ተገልጦለታል፡፡ ይሄም ደግሞ በመካውያን ዘንድ የሚመለኩት አማልክት ማለትም አል-ላት፣ አል-ዑዛ እና መናት የተሰኙት፡ "ምልጃቸው ተቀባይነት ያለው የተከበሩ *ግሃረኒቅ* (በራሪዎች) ናቸው" የሚል ነበር፡፡ አረማውያን የነበሩት ቁራይሾች ይሄንን በሰሙ ጊዜ እጅግ ተደስተው ከሙስሊሞቹ ጋር ማምለክ ጀመሩ፡፡ እንደዛም ሆኖ ጂብሪል የተባለው መልአክ መሐመድን ገሰጸው፡፡ እናም መሐመድ ያ ጥቅስ እንዲወገድ አደረገ፡፡ በዚህም ምክንያት ቁረይሾቹ የበለጠውኑ ጠላቶች ሆኑበት፡፡

ከዚህም በኋላ መሐመድ ቁርአን 22፡52 ላይ የሚገኘው "ከመልክተኛና ከነቢይም ከአንተ በፊት አንድንም አላክንም ባነበበና (ዝም ባለ) ጊዜ ፡- ሰይጣን በንባቡ ላይ (ማጥመሚያን ቃል) የሚጥል ቢሆን እንጅ፤ ወዲያውም አላህ ሰይጣን የሚጥለውን ያስወግዳል፤ ከዚያም አላህ አንቀጾቹን ያጠናክራል፤ አላህም አዋቂ ጥበበኛ ነው" የሚለው ቃል ተገለጠለት ፡፡ ይሄም ከሱ በፊት የነበሩት ነቢያት ብዙዎችን እንደሳቱ አመላካች ነበር፡፡ እዚህ ጋር የምንመለከተው እንግዲህ መሐመድ አሳፋሪ ሊሆን የሚችለውን ክስተት በመለወጥ ራሱን ከፍ ከፍ ለማድረግ እንደተጠቀመበት ነው፡፡

ውስጡን በጣም የጎዳው እርሱ አጭበርባሪ እንደሆነ የሚቀርበበት ክስ እና ቀልድ በበዛበት ጊዜ መሐመድ ስነ ምግባሩ ጥሩ እንደሆነ እና የተሳሳተ ሰው ሳይሆን ታማኝ ሰው እንደሆነ የሚገልጽ መገለትን ከአላህ ዘንድ ተቀበለ፡

ሱረቱ አል-ቀለም 68፡1-4 "በብርእ እምላለሁ በዚያም (መልአኮች) በሚጽፉት፡፡ አንተ በጌታህ ጸጋ የተጎናጸፍክ ስትሆን ዕብድ አይደለህም፡፡ ላንተም (ከጌታህ) የማይቋረጥ ዋጋ በእርግጥ አልለህ፡፡ አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ፡፡" (53፡ 1-3)

"በኮከብ እምላለሁ በወደቀ (በገባ) ጊዜ ፡፡ ነቢያችሁ (ሙሐመድ) አልተሳሳተም፤ አልጠመመም ፡፡ ከልብ ወለድም አይናገርም፡፡" (53፡1-3)

እጅግ በዛ ያሉ ትውፊቶች እንደዘገቡት ከሆነ መሐመድ የራሱ ዘር፣ ጎሳ፣ ነገድና ቤተሰብ የበላይ እንደሆነ ያምን ነበር፡፡ እንደዚሁም የማይመስል መደምደምያ እስኪመስል ድረስ ዘሮቹ ከአዳም ዘሮች ሁሉ የተለዩ እርሱም ከተለየ ጎሳ (ሀሺማውያን) የተለየ ሰው እንደሆነ ተናግሯል፡፡ "እኔ በመንፈሴም በዘሬም ከእናንተ የተመረጥኩ ነኝ ስለሆነም ማንም ሰው አረቦችን ቢወድድ እኔን ከወደደ በኋላ በእኔ በኩል እነሱን ይወዳል" ሲል ተናግሯል፡፡

## ተቀባይነት ያጣባቸው ተጨማሪ አጋጣሚዎች

ለመሐመድ ነገሮች በመልካም ሁኔታ አልሄዱለትም ነበር፡፡ በአንድ ዓመት ውስጥ ባለቤቱን ከድጃን እና አጎቱን አቡ ጧሊብን በሞት አጥቷል፡፡ ይሄ ደግሞ ቀላል የማይባል አስደንጋጭ ኩነት ነበር፡፡ የእነሱ እርዳታና ጥበቃ ባይኖር ኖሮ *ቁራይሾች* የበለጠ በእርሱ ላይ ጠላት ለመሆን ይደፋፈሩ ነበር፡፡

የአረቡ ማኅበረሰብ ግንባር ፈጥሮ የመረዳዳትና የመመካከር መሰረት ነበረው፡፡ የደህንነት ጥበቃ የሚፈለግበት አንዱ መንገድ ያ ሰው

ከአንተ የተሻለ ጠንካራ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ለመሐመድና ለተከታዮቹ አደገኛ ነገሮች እየጨመሩ ከመምጣታቸው የተነሳ እንደዚሁም በራሱ ጎሳዎች ተቀባይነትን በማጣቱ ከሌሎች ዘንድ ትድግና መፈለግን ምርጫው አድርጎ ነበር፡፡ መሳቂያና መሳለቂያም ሆኖ ነበር፡፡ ከታኢፍም በአመጽ ተባርሮ ነበር፡፡

የቱንም ያህል ሁኔታዎች ለመሐመድ መልካም ባይሆኑም በስተመጨረሻ እርሱን ሊታደጉ የሚችሉ ማኅበረሰቦችን ማግኘት ችሎ ነበር፡፡ እነዚህም ብዙ አይሁዶች በሚኖሩባት በመካ የሚኖሩ አረቦች ናቸው፡፡

# አዲስ ተባባሪዎችና ከመካ ሽሽት

በመካ በሚደረገው አመታዊ ትርኢት ላይ ከመዲና የሆኑ በቡድን የተደራጁ ጎብኚዎች ለመሐመድ ያላቸውን ታማኝነትና ታዛዥነት ለመግለጽ ቃል ኪዳን በመግባት እሱ ላስተማረው የአንድ አምላክ መልእክት ለመኖር ተስማምተዋል፡፡

በቃልኪዳኑ የመጀመርያ ጊዜ ለመዋጋት የተደረገ ምንም ዓይነት ራስን መስጠት አልነበረም፡፡ በቀጣዩ ዓመት በነበረ ትርኢት ግን ከመዲና የሆኑ በዛ ያሉ ቡድኖች መሐመድ ለፈለገው ጥበቃ ቃል ኪዳን ገብተዋል፡፡ አንሳር ወይም “ረዳት” በመባል የሚታወቁት የመዲና ሰዎች ሐዋርያቸውን ሙሉ በሙሉ እንዲታዘዙ ይሄንን የማያደርጉት ግን ተገድለው እንዲቀበሩ የሚል ትእዛዝ አስተላልፎ ነበር፡፡

ከዚህ ውሳኔ በኋላ ሙስሊሞች የተረጋጋ የፖለቲካ ክበብ ለመመስረት ወደ መዲና መሰደድ ችለው ነበር፡፡ መሐመድ

በመስኮት ሾልኮ ወደ መዲና ለማምለጥ የመጨረሻው ሰው ነበር፡፡ መዲና በደረሱ ጊዜ መሐመድ መልክቱን ያለምንም እንቅፋት እና በሚገባቸው ሁኔታ በማቅረቡ ብዙ አረቦች ወደ እስልምና ተለውጠዋል፡፡ በዚያን ጊዜ መሐመድ የሃምሳ ሁለት ዓመት ጎልማሳ ነበር፡፡

መካ በቆየባቸው ጊዜያቶች መሐመድ በራሱ ቤተሰቦች እና ጎሳዎች ተቀባይነትን ያጣ ሰው ነበር፡፡ ጥቂት ለየት ያሉ የተዋረዱ ድሆች በእርሱ አምነዋል፡፡ ሆኖም አብዛኛዎቹ ተሳልቀውበታል፣ አስፈራርተውታል፣ አዋርደውታል በተቀሩት ሁሉ ጉዳት እንዲደርስበት ተደርጓል፡፡

መሐመድ ለመጀመሪያ ጊዜ በራሱ እርግጠኛ አልነበረም፡፡ በነብያዊ ጥሪው ላይ ፍርሃት ነበረው፡፡ አንድ ወቅት የቁራይሾችን አማልክት የተቀበለ መስሎ ነበር፡፡ ሆኖም ግን በስተመጨረሻ የቱንም ያህል ተቃውሞ ቢኖርበትም መሐመድ ቁርጠኛ በሆነ ሁኔታ በመንቀሳቀስ ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ለርሱ የሰጡ ተከታዮችን ማፍራት ችሎ ነበር፡፡

# ተቀባይነትን ማጣት እና የመካ መገለጥ

## *ሰላማዊ ምስክርነት?*

ብዙ ጸሐፍት እንደሚናገሩት መሐመድ በመካ የቆየባቸው አስር ዓመታት ሰላማዊ ነበሩ፡፡ ይሄ አባባል በአንድ ጎኑ እውነት ነው፡፡ ነገር ግን በቁርአን የመካ ምዕራፎች ላይ የቱንም ያህል አካላዊ ጉዳት የታዘዘም ባይሆንም እነዚህ ቀደምት መገለጦች የመሐመድን ጎረቤቶች አስፈሪ በሆኑ ንግግሮች በሚቀጥለው ህይወት ለተቃዋሚዎች

አርነት በምርኮ ውስጥ ላሉት

የተዘጋጀውን አሳቃቂ ቅጣት በመግለጽ ማስፈራራታቸው አልቀረም፡፡

በቁርአን ውስጥ የሚገኙት የመካ ፍርዳዊ ጥቅሶች ዓላማ በቁራይሽ አረቦች ተቃውሞ በተጻራሪ መሐመድን መደገፍ ነበር፡፡ ለምሳሌ ያህል ብንወስድ መሐመድ በሙስሊሞች ላይ የሚስቁ የከፋ ቅጣት እንደሚያገኛቸው ተናግሯል፡፡ በገነት የሚኖሩ ሙስሊም አማኞች በምቾት ውስጥ ሆነው ወይን እየጠጡ ሲደሰቱ ሙስሊም ያልሆኑት ደግሞ በእሳት ውስጥ እየተጠበሱ ሲቃጠሉ ወደ ታች እያዩ ይስቁባቸዋል፡፡ (83፡29-36)

ይሄ የፍርድ መልእክት በመካዎች ዘንድ ያለምንም ጥርጥር የግጭት እሳት እንዲቆሰቆስ አድርጓል፡፡ ጣዖታትን የሚያመልኩ ሰዎች የሰሙትን ነገር ሊወዱት አልቻሉም፡፡

## አስቀድሞ ማስጠንቀቅ በመካ

መሐመድ የዘላለም ፍርድን ብቻም አልነበረም የሰበከው፡፡ ኢብን ኢስሃቅ እንደዘገበው ከሆነ አስቀድሞ በመካውያን ዘመን መሐመድ ጣዖታውያኑን ለመግደል ሐሳብ እንደነበረው አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ነበር፡፡ "እናንተ *ቁራይሾች* ትሰሙኛላችሁን? ህይወቴን በእጁ ላይ ባደረገው እናንተን ጭፍጨፋን አመጣባችኋለሁ፡፡"

መሐመድ ወደ መዲና ከመሸሹ በፊት በቡድን የተደራጁ ቁራይሾች ወደ እርሱ መጥተው ፊት ለፊት በመጋፈጥ እርሱን የማይቀበሉትን እንደሚገድል ተናግሯል ሲሉ ከሰሱት "መሐመድን የማትከተሉት ከሆነ ትሰዋላችሁ፡፡ ከሞት ከተነሳችሁም በኋላ በእሳት ባህር ውስጥ

ትቃጠላላችሁ” ብለሃል ሲሉ ነበር የከሰሱት “መሐመድም እውነት ነው ብያለው ደግሞም ትክክል ነኝ” ሲል ምላሽ ሰጥቷል፡፡

በሙስሊሞች ላይ በመዲና ከደረሰው ጠንካራ ተቀባይነትን ማጣት የተነሳ መለኮታዊ ምሪትን በማግኘት በጠላቶቻቸው ላይ ጦርነትን ለማወጅ ተገደው ነበር፡፡

## አሸናፊዎችና ተሸናፊዎች

ስኬትን፣ ማሸነፍንና መሸነፍን የሚያሳይ ቋንቋን አስመልክቶ ኢስላማዊው ፅንሰ ሐሳብ በመጀመርያ የተገለጸው መሐመድ በመካ በቆየባቸው አስራ ሦስት ዓመታት አጋማሽ ላይ እንደነበር በቁርአን ቁጥሮች ላይ እንደ ጭብጥ ሆኖ ቀርቧል፡፡ በእነዚህ ጊዜያቶች በሙሴና በግብፃውያን ጣዖታት ማካከል የተደረገውን ግጭት በአሸናፊና በተሸናፊ መካከል እንደነበር በተደጋጋሚ ለማጣቀሻነት ተጠቅሞበታል፡፡ (20፡64፤69፤ 26፡40-44፤ 29፡39)

በመጨረሻዎቹ የመካ ጊዜያት መሐመድ ስኬትን አስመልክቶ የተጠቀመባቸው ቃላቶች በእርሱና በተቀናቃኞቹ መካከል የነበረውን ትግል የሚያሳዩ ነበሩ፡፡ በአስረኛው ሱራ ወደ መዲና የተደረገው ስደት ከመጀመሩ በፊት መሐመድ የአላህን መገለጥ የማይቀበሉትን ተሸናፊዎች ናቸው ሲል አውጇል፡፡ (10፡95)

## የመሐመድ ‘ፊትና’ ንጽረተ ዓለም

መከራ፣ ስደት፣ ፈተናን የሚያመለክተው ፊትና የተሰኘው የአረብኛ ቃል መሐመድ ወደ ወታደራዊ መሪነት ቀስ በቀስ እንዴት እንደተሸጋገረ ለማወቅ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ ስርወ ቃሉ የመጣው

"ከሆነ ነገር መመለስ፣ መፈተን፣ ማግለል፣ ለችግር መዳረግ" የሚሉ ትርጉሞች ካሉት ፋታና ከሚል ቃል ነው፡፡ መሰረታዊ ትርጓሜውም ብረትን በእሳት ውስጥ በማሳለፍ ብረትነቱን ማረጋገጥ የሚለውን ሊወክል ይችላል፡፡ ፊትና ፈተና ወይም መከራን በአዎንታዊና በአሉታዊ መልኩ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህም ስቃይንም የሚያጠቃልል ነው፡፡

ፊትና የቀደሙት የሙስሊም ማኅበረሰብ አባላት ሙስሊም ካልሆኑት ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ቁልፍ የሆነ የስነ መለኮት ፅንሰ ሐሳብ ሆኖ ነበር፡፡ መሐመድ ቁራይሾች ፊትናን ማለትም፤ ስድብን፣ ስም ማጥፋትን፣ ስቃይን፣ ማግለልን፣ የኢኮኖሚ ተፅዕኖ ማድረግን እና ሌሎች ተፅዕኖዎችን በመጠቀም ከእስልምና ለመሸሽ ሞክረዋል፣ ሌሎችንም ከእስልምና አደናቅፈዋል የሚል ክስ አቅርቦባቸው ነበር፡፡ መዋጋትን አስመልክቶ በመጀመርያ የተገለጠው ቁጥር ግልጽ እንደሚያደርገው የመዋጋትና መግደል አጠቃላይ ዓላማው ፊትናን ለማስወገድ ነው፡፡

> እነዚህንም የሚጋደሉዋችሁን (ከሓዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሉ፤ ወሰንንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና፡፡
>
> ባገኛችኋቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው፤ ከአወጧችሁም ስፍራ አውጥዋቸው ፤ መከራም ከመግደል ይበልጥ የበረታች ናት፤ በተከበረው መስጊድም ዘንድ በርሱ ውስጥ እስከሚጋደሉዋችሁ ድረስ አትጋደሉዋቸው፤ ቢጋደሉዋችሁም ግደሉዋቸው፤ የከሀዲዎች ቅጣት እንደዚህ ነው፡፡ ቢከለከሉም አላህ መሀሪ አዛኝ ነው፡፡

> ሁከት እስከማይገኝና ኃይማኖት ለአላህ ብቻ እስከሚሆን ድረስ ተጋደሉዋቸው፤ ቢከለክሉም ወሰንን ማለፍ በበዳዮች ላይ እንጂ የለም (ወሰን አትለፉባቸው)፡፡ (2፡190-193)

የሙስሊሞች ፊትና "መከራም ከመግደል ይበልጥ የበረታች ናት" ተብሎ መነገሩ አስፈላጊ ነጥብ ነው፡፡ በተቀደሰው ወር (የአረብ ጎሳ ልማድ ውጊያን በሚከለክልበት ወር) በመካ ነጋዴዎች ላይ ጥቃት ከተፈጸመ በኋላ ተመሳሳይ የሆነ ቃል ተገልጧል (2፡217)፡፡ የከሃዲዎችን ደም ማፍሰስ ሙስሊም ከኃይማኖቱ እንዲያፈነግጥ ከማድረግ ያነሰ ነገር መሆኑ ተመልክቷል፡፡

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ያለ ሌላኛው ወሳኝ ነገር "ምንም ዓይነት ፊትና እስከማይኖር ድረስ ተዋጓቸው" የሚለው ነው፡፡ ይህም በመዲና በሁለኛተው ዓመት ላይ ከበድር ጦርነት በኋላ ተደግሟል (8፡39)፡፡

እነዚህ ሁለት ሁለት ጊዜ የተገለጡት የፊትና ሐረጎች ሰዎች ወደ እስልምና እንዳይገቡ የሚከለክል ምንም ዓይነት እንቅፋት ባለበት ጊዜ ወይንም ደግሞ ሙስሊሞች እምነታቸውን እንዲክዱ የሚያደርግ ነገር በተፈጠረበት ጊዜ ላይ ጂሃድ የተፈቀደ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ሰዎችን መዋጋት እና መግደል ምናልባት የትኛውንም ያህል አሳዛኝ ቢሆንም እስልምናን መናቅ ወይንም እንቅፋት መሆን ከዚያ ይከፋል፡፡

አብዛኞቹ ሙስሊም ምሑራን ፊትና የአለማመንን መኖር ጭምር ያጠቃልላል ስለሚሉ ይህ ሐረግ "አለማመን ከመግደል ይከፋል" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡

በንደዚህ ዓይነት መንገድ የምንረዳው ከሆነ እንግዲህ "ፊትናከመግደል ይከፋል" የሚለው ሐረግ ሙስሊሞችን ቢተናኮሉም ባይተናኮሉም የመሐመድን መልዕክት የተቃወሙ ከሃዲዎችን ሁሉ ለመግደል ዋስትና ይሰጣል ማለት ነው፡፡ የታላቁን ሀተታ ሰጪ የኢብን ከቲርን ንግግር ለመጠቀም ያህል ለከሃዲዎች "አለማመንን መፈጸም" ከነርሱ መገደል ይልቅ የባሰ ክፋት ነው፡፡ ይህ አለማመንን በማስወገድ እስልምናን በተቀሩት አካባቢዎች ላይ የበላይ ለማድረግ ጦርነትን መጠቀምን ያጸድቃል (2፡193፣ 8፡39)፡፡

## ሙስሊም ላልሆኑት ያለው እንደምታ

ሙስሊም ያልሆኑትን አለመቀበል የሚለው ኢስላማዊ ህግ የመነጨው ከመሐመድ ስሜታዊ ንጽረተ ዓለም እና ተቀባይነት ማጣትን አስመልክቶ ካለው ምላሽ ነው፡፡ በመጀመርያ መሐመድ ጠላትነቱ ከራሱ ጎሳ የሆኑ ጣዖታት አምላኪ አረቦች እንደሆኑ ትኩረት አድርጎ ነበር፡፡ እነዚህ ጣዖታውያን የሆኑ አረቦች በእስልምና አስተምህሮ ላይ ከነበራቸው መጥፎ አመለካከት የተነሳ ተገቢውን ምላሽ መስጠት እንደሚያስፈልግ መሐመድ ያምን ነበር፡፡ መሐመድ የመጽሐፉ ሰዎች ከሚላቸውም ተመሳሳይ ውግዘት ደርሶበት ነበር፡፡ እስልምናን እንደመቃወማቸው መጠን እንዲጨቆኑ እና እንደ የበታች እንዲቆጠሩ ወንጀለኞች ናቸው የሚል ታርጋ ተለጥፎባቸዋል፡፡

## በሌሎች የመወገዝ ተቃውሞዎች

የመሐመድን የነብያዊነት ታሪክ በምንመለከትበት ጊዜ ተቀባይነት ስለማጣት የተሰጡ የተለያየ ደረጃ ያላቸውን ምላሾች ማጤን እንችላለን፡፡ በመጀመርያዎቹ ጊዜያቶች እንደምንመለከተው

ከነበረበት ጠንካራ ውግዘት የተነሳ ራሱን የማጥፋት አስተሳሰብ፣ አጋንንት እንደተቆጣጠረው አድርጎ መፍራትና ተስፋ የመቁረጥ ሁኔታ ነበር፡፡

ተቀባይነት የማጣትን ፍርሃት ለማሸነፍ ራስን የማፅደቅያ ምላሾችም ነበሩ፡፡ እነዚህም የሚያጠቃልሉት አላህ ጠላቶቹን በሲዖል ይቀጣል የሚለውን ጨምሮ አንዳንድ አሳፋሪ አጋጣሚዎችን ለመሸፈን ሁሉም ነብያቶች አንድ ወቅት በሰይጣን ተታለዋል የሚለውን የሚመስሉ ነገሮችን መናገር፣ የመሐመድን መገለጦች የተከተሉ ሰዎች በዚህም ሆነ በወዲያኛው ዓለም አሸናፊዎች እንደሚሆኑ አላህ መናገሩን የሚገልጹ ጥቅሶችን መናገር የመሳሰሉ ነገሮች ይጠቀሳሉ፡፡

በመጨረሻም የጠብአጫሪነት ምላሾች እየጎሉ መጡ፡፡ የዚህም ውጤት ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎችን በመዋጋት እና በማሸነፍ ፊትናን ለማስወገድ ለሚያስችለው የጂሃድ አስተምህሮ መፈጠር ምክንያት ሆነ፡፡

## ተገቢ ቅጣት

የመሐመድ በመዲና ያለው ወታደራዊ ጥንካሬ እያደገ ሲሄድ ድል እየተቀዳጀ መሄድ ጀመረ፡፡ ድል ያደረጋቸውን ጠላቶቹን የሚይዝበት መንገድ ለመዋጋት ስላነሳሳው ጉዳይ የሚለው ነገር አለው፡፡ ለዚህ ጥሩ ማስረጃ የሚሆነው ቀደም ሲል በመሐመድ ላይ የግመል ፋንድያ እና አንጀት ስለወረወረበት ኡቅባ ስለተባለው ሰው የሚነገረው ነው፡፡ ኡቅባ በድር በሚባል ጦርነት ተማርኮ መሐመድን እንዲህ ሲል ተማፀነው "መሐመድ ሆይ ልጆቼን ማን ይጠብቃቸዋል?" መሐመድም "ሲዖል" ካለ በኋላ ገደለው፡፡ ከበድር ጦርነት በኋላ የተገደሉ መካውያን አስከሬን በጉድጓድ ውስጥ ተጥሎ ነበር፡፡

መሐመድም የመካ ሟቾች ላይ ለመሳለቅ በእኩለ ሌሊት ወደ ጉድጓዱ ሄዶ ነበር፡፡

እንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ የሚያሳየው መሐመድ እርሱን ያወገዙትን ሁሉ ተገቢውን ቅጣት በመስጠት የሚበቀል መሆኑን ነው፡፡ ይሄንን ደግሞ እስከ ህይወቱ ፍፃሜ ድረስ ሲያደርገው ኖሯል፡፡

## የመካ ድል መደረግ

መሐመድን የተቃወሙ ሁሉ ሁልጊዜ ስማቸው በሚገደሉት ሰዎች ተርታ መመደቡ የታወቀ ነበር፡፡ መሐመድ መካን ድል ባደረገ ጊዜ ሰዎችን መግደል ማበረታታት እንዲቆም አድርጎ ነበር፡፡ እንደዛም ሆኖ እንዲገደሉ ትእዛዝ የወጣባቸው ሰዎች ነበሩ፡፡ ሦስቱ ወደ ኋላ የተመለሱ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ሁለቱ መሐመድን በመካ የተሳደቡ ነበሩ፡፡ ከሦስቱ አንዷ ሴት ነበረች፡፡ ሌሎች ሁለት ሴቶች ደግሞ ስለ መሐመድ ምጸታዊ ግጥምን በመግጠማቸው ምክንያት ነበር፡፡

በመካ የተገዳዮች ስም ዝርዝር መኖሩ የሚያመላክተው መሐመድን የሚቃወሙ ሰዎች የነበሩ መሆናቸውን ነው፡፡ የመሐመድን አስተምህሮ በመቃወማቸው ምክንያት ለስቃይ የተዳረጉ አርአያ የሚሆኑ ሰዎች ነበሩ፡፡ እነዚህ ሰዎች ደግሞ እስልምናን ጥሎ መውጣት እንደሚቻል ያሳዩ ሰዎች ነበሩ፡፡ መሐመድን የተሳደቡም ሆነ በእርሱ የተሳለቁ አደገኛ ሁኔታ ያጋጥማቸው ነበር፡፡ ምክንያቱም የሌሎችን እምነት የመሸርሸር አቅም ስለነበራቸው ነው፡፡

# የሁዳይቢያህ ስምምነት

መካ ድል ከመደረጓ በፊት ወደ መካ እንደሚጓዝ ራዕይ አይቶ ነበር፡፡ በወቅቱ ይሄ ሊሆን የሚችል አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ሙስሊሞች ከመካውያን ጋር ጦርነት ለመግጠም በዝግጅት ላይ የነበሩበት ወቅት ነበርና፡፡ ራዕዩን ካየ በኋላ መሐመድ ጉዞ ሊያደርግ የሚችልበትን ስምምነት ተደራደረ፡፡ የስምምነቱን ውል ያደረጉት ደግሞ ለአስር ዓመት ነበር፡፡ ከስምምነቶቹ መካከል አንደኛው መሐመድ ያለመካውያን ጠባቂዎች ፈቃድ በማንኛውም ጊዜ ከእርሱ ጋር ካሉት ጋር ወደ መካ መጓዝ እንደሚችል የሚያሳይ ነበር፡፡ ይሄ ደግሞ የሚያጠቃልለው በዚያን ጊዜ ባርያዎች ተብለው የሚጠሩትንና ሴቶችንም ነው፡፡ ስምምነቱ ሁለቱም ወገኖች በነፃነት መጓዝ የሚችሉበትን ሁኔታ ያገናዘበ ነበር፡፡

አስገራሚው ነገር መሐመድ የገባውን የስምምነት ውል መጠበቅ አለመቻሉ ነው፡፡ ለዚህም ደግሞ ምክንያቱ ሰዎች ከመካ ወደ እርሱ ሲመጡ ባርያ በማድረግ ሴቶቹንም ሚስቶቹ በማድረጉ በተጨማሪም የአላህ ስልጣን ነው በማለት ስደተኞቹን ለመልቀቅ ፈቃደኛ አለመሆኑ ነበር፡፡ የመጀመርያው ጉዳይ ወንድሟ ሊመልሳት የመጣ ኡም ኩልትም የተባለች ሴት ጉዳይ ነበር፡፡ ነገር ግን ኢብን ኢስሃቅ እንዳስቀመጠው "አላህ ከልክሏል" በማለት መሐመድ ሀሳቡን ተቃውሟል፡፡

ሱራ 60 ለሙስሊሞች የሚመክረው ነገር ቢኖር ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎችን ወዳጅ አድርገው እንዳይወስዱ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሙስሊም መካውያንን በምስጢር ቢወዳጅ ክህደት እንደተደረገ ይቆጠር ነበር፡፡ ሙስሊም ያልሆኑት በማንኛው ምክንያት ሙስሊሞችን ከእምነታቸው እንዲያፈገፍጉ ምክንያት ናቸው ተብሎ ይታመን ነበር፡፡ ሱራ 60

እንዲህ ከሚለው የሁዳይቢያህ ስምምነት ጋር ይጋጫል፡ “እርስበርሳችን ምንም ዓይነት ጠላትነት አናሳይም፡፡ በምስጢር የምናደርገው የተለየ ነገርም አይኖረንም፡፡” ይሁንና ሙስሊሞቹ በመካውያን ላይ ጥቃትን ከፍተው ድል ካደረጉ በኋላ ስምምነቱን ያፈረሱት ቁራይሾች እንደነበሩ ማስረጃ ሆኖ ቀርቦ ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ከጣዖታት አምላኪዎች ጋር ምንም ዓይነት ስምምነት እንዳይደረግ አላህ አወጀ፡፡

9፡3-5 “አላህ ከአጋሪዎቹ ንጹህ ነው...” “አጋሪዎቹን በአገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሉዋቸው”

እንደዚህ ዓይነት ክስተቶች የሚያመለክቱት መሐመድ የማያምኑትን ሰዎች ሙስሊሞች ከእምነታቸው እንዲያፈነግጡ ከሚያደርጉት ወገን በመፈረጅ እነርሱ እስልምናን እስካለተቀበሉ ድረስ ከነርሱ ጋር ጤናማ የሆነ ግንኙነት እንዳይኖር ማድረጉን ነው፡፡

# አይሁዶችን መታገል

በመዲናና በቃይባር ከሚኖሩ አይሁዶች ጋር መሐመድ የነበረውን ግንኘነት በተመለከተ “ የመጽሐፉ ሰዎች”ን ገና ከመሰረቱ አስገድዶ ቃል ኪዳን የማስገባት ውልን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነበር፡፡

## አይሁዶችን በተመለከተ መሐመድ በመጀመርያ የነበረው አመለካከት

በመካው ዘመን ከነበሩ ከአይሁዶች ጋር መሐመድ የነበረውን ግንኙነት በተመለከተ በብዙ አይሁዳዊ ነብያት መስመር ውስጥ በመግባት

እርሱም ነብይ እንደሆነ ይናገር ነበር፡፡ በመካ እና በመጀመርያው ወር በመዲና የተገለጠውን ሱራ በምንመለከትበት ጊዜ በአንፃራዊነት ስለ አይሁዶች በጥቂቱ የተገለፁ ማጣቀሻዎች ነበሩ፡፡ ቁርአን በመካ ይኖሩ የነበሩትን አይሁዶች በመጥቀስ በሚናገርበት ጊዜ አንዳንዶቹ እስልምናን ያልተቀበሉ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ የመሐመድን መልዕክት እንደ በረከት አድርገው የተቀበሉትን ያመለክታል፡፡ (98፡ 1-8)

መሐመድ በመካ በነበረው ቆይታ ከአንዳንድ ክርስቲያኖች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ሞክሮ ነበር ግንኙነቱም አበረታች ነበር፡፡ ክርስቲያን የነበረው የከድጃ የአጎት ልጅ ዋራቃ መሐመድን እንደ ነብይ ተቀብሎት ነበር፡፡ እንደዚሁም በመካ የሚኖሩ የአቢሲኒያ ክርስቲያኖች ከእርሱ ጋር የመገናኘት እድል ስለገጠማቸው በእርሱ አምነው ነበር፡፡ ምናልባትም አይሁዶች የመሐመድን ማንነት በመለየት "ከአላህ የተላከ ግልፅ ምልክት" አድርገው እንደሚቀበሉትና ለመልዕክቱ አዎንታዊ ምላሽ እንደሚኖራቸው ተስፋ አድርጎ ነበር፡፡ ሱራ 98ን በምንመለከትበት ጊዜ መሐመድ አስተምህሮቱ ከአይሁዶች ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ተናግሯል፡፡ ይሄ ደግሞ ጸሎት መጸለይና ለድሆች መስጠትን ያካትታል (98፡5)፡፡ በአይሁዶች ልማድ እንደሚደረገው በጸሎት ጊዜ በሶርያ አቅጣጫ ወዳለችው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲዞሩ ተከታዮቹን አዟቸዋል፡፡ ኢስላማዊ ትውፊቶች እንደመዘገቡት ከሆነ መሐመድ መዲና ሲደርስ ከአይሁዳውያን ጋር ቃልኪዳን ተገባብቶ ነበር፡፡ ቃል ኪዳኑም አይሁዶችም ሆኑ ሙስሊሞች የራሳቸው ኃይማኖት ያላቸው ሲሆን አይሁዶች ለሙስሊሞች ታማኝነትን እንዲያሳዩ ትእዛዝ የታዘዘበት ነበር፡፡

## *በመዲና የደረሰ ተቃውሞ*

*በመዲና ለሚኖሩ የአይሁድ ማኅበረሰብ አባላት መሐመድ መልዕክቱን ማድረስ በጀመረ ጊዜ በፍጹም ያልጠበቀው ተቃውሞ ገጥሞት ነበር፡፡ ኢስላማዊ ትውፊቶች እንደሚናገሩት ከሆነ ተቃውሞው የቅናት ባህሪ አለው ይላሉ፡፡ አንዳንዶቹ የመሐመድ መገለጦች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማጠቀሻዎች አሉት፡፡ የአይሁድ መምህራን እነዚህን ጽሑፎች ስለመቃወማቸው ምንም ጥርጥር የለም፡፡ ከመሐመድ አተረጓጎም ጋር እንደሚቃረኑም ሳያመላክቱ አልቀረም፡፡ የሙስሊሞች ነብይ የሆነው (መሐመድ) የአይሁድ መምህራንን ጥያቄ ችግር ፈጣሪ እንደሆኑና ቁርአን ከሰማይ የወረደዉ ወደ እርሱ እንደሆነ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ በተደጋጋሚ መሐመድን ጥያቄ በመጠየቅ ሰዎች በሚገዳደሩት ጊዜ ሁኔታውን የሚጠቀምበት ሰዎች እርሱን እንዲቀበሉ በማድረግ ነው ለዚህም እማኝ የሚያደርገው ቁርአንን ነው፡፡*

*የመሐመድ ቀለል ያለው ስልት ምንድን ነበር? ካልን አይሁዶች አታላዮች መሆናቸውን ማረጋገጥ ነበር፡፡ ለዚህም ደግሞ ተስማሚ የሆነ ጥቅስን ከቁርአን ይጠቅስ ነበር፡፡* 936፡76፣ 2፡77)

*ከአላህ ዘንድ የመጣው ሌላው ምላሽ ደግሞ አይሁዳውያን ሆን ብለውና አስበውበት ቅዱሳት መጽሐፍቶቻቸውን ውሸት እንዲቀላቀልባቸው አድርገዋል የሚል ነው፡፡* (2፡75)

*በአይሁዳውያን መምህራንና በመሐመድ መሀከል የተደረገው ውይይት በኢስላማዊ ትውፊቶች ተተርጉሟል፡፡ ይሄም ደግሞ እንደ እውነተኛ ንግግር አልያም ለመሐመድ እሳቤ ምክንያታዊ ምላሾች እንደተሰጠ*

ተቆጥሮ ሳይሆን እንደ ፊትና (እስልምናንና የሙስሊሞችን እምነት እንደማጥፋት ተቆጥሮ) ነው፡፡

# የተቃዋሚዎች ጥላቻን የተሞላ ስነመለኮት

መሐመድ ከአይሁዶች ጋር የተለዋወጣቸው አደናቃፊ ንግግሮች የሚያመላክቱት ለአይሁዶች የነበረው ጥላቻ ምን ያህል እያደገ የመጣ እንደነበር ነው፡፡ ከላይ በተገለጹት ጥቅሶች ለመግለጽ እንደተሞከረው አንዳንድ አይሁዶች እስልምናን በመቀበላቸው ምክንያት ቁርአን እስልምናን ከተቀበሉት ከጥቂቶቹ በስተቀር ሁሉም አይሁዶች የተረገሙ እንደሆኑ አውጇል፡፡ (4፡ 46)

ቁርአን እንደሚለው ከሆነ ባለፉት ጊዜያት አንዳንድ አይሁዶች በኃጢአታቸው ምክንያት ወደ ዝንጀሮነትና አሳማነት ተቀይረዋል (7፡ 166)፡፡ አላህ እንደዚሁ የነብያት ገዳዮች ብሏቸዋል (7፡166፣ 5፡60፣ 2፡56)፡፡

አላህ ቃል ኪዳንን ከሰበሩ ከአይሁዳውያን ጋር የነበረውን የባለቤትነት ግንኙነት አንስቷል (5፡70)፡፡ ይሄም የሆነበት ምክንያት ልባቸውን ስላደነደኑ ነው፡፡ ሙስሊሞች ሁሉጊዜ (ከጥቂቶች በስተቀር) ከሀዲዎች እንደሆኑ ያምናሉ፡፡ ቃል ኪዳናቸውን ስላፈረሱ አሁዶች ከሳሪዎች ተብለዋል (2፡ 27)፡፡

ወደ መዲና ከመምጣቱ በፊት የመሐመድ መገለጥ እንዳመላከተው አይሁዳዊነት ጠቀሜታ ነበረው (2፡62) ነገር ግን ይህ በ3፡85 ላይ ባለው ሀሳብ ተሽሯል፡፡ መሐመድ ወደ መዲና የመጣበት ምክንያት የአይሁዶችን ስህተት ለማረም መልዕክተኛ ሆኖ ነው (5፡115)፡፡

አርነት በምርኮ ውስጥ ላሉት

በሱራ 5፡115 መሰረት መሐመድ እንደደመደመው የተላከበት ቀዳማይ ዓላማ አይሁዳዊነትን ለመሻር፣ እስልምናን የመጨረሻው ኃይማኖት ለማድረግና ቁርአንን የመጨረሻው መገለጥ ሆኖ እንዲቀርም ጭምር ነው፡፡ ይሄንን መገለጥ የሚቃወሙ ሁሉ ከሳሪዎች ናቸው፡፡ ይሄ ደግሞ ለአይሁዳውያኖችም ሆነ ለክርስቲያኖች መቼም ቢሆን የጥንት ኃይማኖታቸውን እንከተል ቢሉ ተቀባይነትን የሚያገኝ አይደለም፡፡ ለመሐመድ እውቅና በመስጠት እስልምናን መቀበል የግድ ነው፡፡

## ወደ ብጥብጥ የተሻገረ ተቀባይነትን ማጣት

በመዲና አይሁዶችን ለማስፈራራት ብሎም ለማጥፋት መሐመድ ዘመቻ አዘጋጀ፡፡ በበድር በሚኖሩ ጣዖት አምላኪዎች ላይ በተቀዳጀው ድል ስለተደፋፈረ *ቀይኑቃ* በሚባል ቦታ ላይ ወደሚኖሩ የአይሁድ ጎሳዎች ዘንድ በመሄድ በአላህ የበቀል ቁጣ አስፈራራቸው፡፡ ከዚያም ሰበብ ፈልጎ የቀይኑቃን አይሁዶች በመክበብ ከመዲና አባረራቸው፡፡

በመቀጠልም መሐመድ አይሁዶችን አደጋ ውስጥ የሚጥልና እንዲገደሉ የሚያደርግ ዓላማን ሰንቆ ተነሳ፡፡ ለተከታዮቹም “በኃይላችሁ ስር የወደቀን ማንኛውንም አይሁዳዊ ግደሉ” ሲል ትእዛዝን አስተላለፈ፡፡ “ለአይሁዶቹም እስልምናን ተቀበሉ ደህንነትም ይሆንላችኋል” ሲል አወጀ፡፡

በመሐመድ የመረዳት ዕውቀት ውስጥም ታላቅ የአቅጣጫ ለውጥ ተደረገ፡፡ ሙስሊም ያልሆኑት መኖር የሚችሉትና ንብረታቸው ሊጠበቅ የሚችለው እስልምናና ሙስሊሞችን መርዳት ከቻሉና ሲያከብሯቸው ብቻ እንደሆነም ደነገገ፡፡ ከዚህ ውጭ ያለው ግን *ፊትና* ስለሆነ የሀሰት እነርሱን ለመዋጋት የመነሻ ሰበብ ሆናል፡፡

ሙሐመድ ከአይሁዶች ጋር የነበረውን ጉዳይ ገና አልጨረሰም፡፡ በኑ ናዲር የተባሉት ጎሳዎች በርሱ ትኩረት ውስጥ ለመግባት ቀጣዮቹ ነበሩ፡፡ ሁሉም የናዲር ጎሳ አባላት ቃል ኪዳናቸውን በማፍረስ ተከሰው ጥቃት ደረሰባቸው፡፡ ከረጅም ጊዜ ከበባ በኋላ ንብረታቸውን ለሙስሊሞች እንደ ምርኮ በመተው ከመዲና ተባረሩ፡፡

ከዚህ በኋላ መሐመድ በስተ መጨረሻ የቀረውን የአይሁዶች ጎሳ ቁራይዛዎችን ከበበ፡፡ ከመልአኩ ጅብሪል የመጣ ትእዛዝን መሰረት ባደረገ መልኩ መሆኑ ነው፡፡ አይሁዳውያንም ያለምንም ምክንያት እጃቸውን እንደሰጡ ወንዶቻቸውን መዲና በሚገኘው የገበያ ስፍራ አንገታቸው እንዲቀላ ተደረገ፡፡ እነዚህም ከስድስት መቶ እስከ ዘጠኝ መቶ እንደሚደርሱ ይገመታል፡፡ ሴቶችንና ልጆችንም ለሙስሊሞቹ ባርያዎች እንዲሆኑ ተደረገ፡፡

መሐመድ በአረብ ምድር ከሚኖሩ አይሁዶች ጋር ያለውን ነገር ሁሉ አልጨረሰም ነበር፡፡ በመዲና የሚኖሩትን ካጠፋ በኋላ ቃይባር ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሰ፡፡ የቃይባር ዘመቻ የተጀመረው ምላሽን በሚጠይቁ ሁለት ምርጫዎችን ነበር፡፡ እነርሱም ወደ እስልምና መለወጥ አልያም መሞት የሚሉ ነበሩ፡፡ እንደዛም ሆኖ ሙስሊሞች በቃይባር አይሁዶችን ባሸነፉ ጊዜ ሦስተኛ ምርጫ እንደ መደራደርያ ሆኖ ገባ፡፡ ከሚሆነው ነገር የተነሳ እጅ በመስጠት በቃይባር የሚኖሩ አይሁዳውያን የመጀመርያዎቹ የዲህሚ ህግ ተገዢዎች ሆኑ፡፡

መሐመድ ከአይሁዶች ጋር የነበረውን ግንኙነት አስመልክቶ ለማቅረብ የተሞከረውን ሀሳብ እዚህ ላይ ብንቋጨው የተሻለ ነው፡፡ አንድ ልንገነዘበው የሚገባ ነገር ቢኖር ቁርአን አይሁዶችንና ክርስቲያኖችን “የመጽሐፉ ሰዎች” በማለት በአንድ ጎራ ይመድባቸዋል፡፡ የመሐመድ ህይወትና ቁርአን ለክርስቲያኖች እና ለአይሁዶች እንደ

"የመጽሐፉ ሰዎች" የሰጡት ቦታ በየዘመናቱ የሚኖሩ አሁዶች እና ክርስቲያኖች ለሚታዩበት መንገድ እንደ ሞዴል ሆኖ እንደሚያገለግል ግልጽ ነው፡፡

# "ተጠቂዎች ነን"

የመሐመድ መርሐ ግብር እንደ ዋና ነገር አፅንዖት በመስጠት ይናገር የነበረው የሙስሊሞችን ተጠቂዎች መሆን ነበር፡፡ የስነመለኮታዊ አቋምን በቀጣይነት ለማስቀጠል ድል ማድረግ ማለት ነፃ መውጣት እንደ ማለት ይቆጠርም ነበር፡፡ በሙስሊሞች ላይ ይደረግ የነበረው "መጠነ ሰፊ ቅጣት" ጠላቶቻቸው የህሊና ቅጣት እንዲደርስባቸው ያደረገም ነበር፡፡ እንደ መለኮታዊ ድንጋጌ ከሆነ የሙስሊሞች ስቃይ "ከመገደል ይልቅ የከፋ" ስለሆነ እያንዳንዱ ሙስሊም ከጠላቶቹ ለሚሰነዘርባቸው ጥቃት ምንም ዓይነት የከፋ ምላሽ መስጠት እንደ ግዴታ ይቆጠራል፡፡ ሙስሊሞች ተጠቂዎች በሆኑ መጠን የእምነት አቅጣጫው ገፅታ የሚያመላክተው የእስልምናን አስተምህሮ አስፈላጊነት ነው፡፡

በቁርአን እና በመሐመድ ሱና ላይ የተመሰረተው ይህ ስነ መለኮታዊ አስተሳሰብ ነው ብዙ ጊዜ ሙስሊሞች የነርሱ ተጠቂነት እነርሱ ካጠቋቸው ሰዎች ጉዳት ይልቅ እጅግ የከፋ መሆኑን ደጋግመው እንዲናገሩ የሚያደርጋቸው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ የአልጄርያ የኃይማኖታዊ ፖለቲካ ፕሮፌሰር በሆኑት በፕሮፌሰር አህመድ ቢን መሐመድ ተንጸባርቋል፡፡ ከዶክተር ዋፋ ሱልጣን ጋር በአልጀዚራ ቲቪ ላይ በተደረገ ክርክር በዶክተር ዋፋ ንግግር በመቆጣት እንዲህ ብሎ ጮኸ፡

> ተጠቂዎቹ እኛ ነን! ... በኛ (በሙስሊሞች) መካከል በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ንጹህ ሰዎች አሉ ነገር ግን በናንተ መካከል ያሉት በአስራዎች፣ በመቶዎች ወይንም በሺዎች ቢቆጠሩ ነው፡፡

ይህ የመጨቆን አስተሳሰብ እስከዚህ ዘመን ድረስ በብዙ የሙስሊም ማህበረሰቦች መካከል እንደ ወረርሺኝ በመሰራጨት ለራሳቸው ስራ ኃላፊነት የመውሰድ አቅማቸውን አዳክሞታል፡፡

# ሌሎችን የሚያወግዘው መሐመድ

የመሐመድን ሌሎችን ያለመቀበል ታሪክ ቅኝት እዚህ ላይ መጠቅለሉ የተሻለ ይሆናል፡፡ ሌሎቹን በመግፋቱና ተበቃይነቱ በጠላቶቹ ላይ ስኬትን እንዲቀዳጅ አድርጎታል፡፡

እንደተመለከትነው የሙስሊሞች ነቢይ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ ተቀባይነት ማጣትን አስተናግዷል፡፡ በቤተሰቡ መካከል፣ በመካ ከነበረው ከራሱ ማህበረሰብ እና በመዲና ከነበሩት አይሁዶች ዘንድ ተቃውሞ ገጥሞታል፡፡ ምላሹን በምንመለከትበት ጊዜ መሐመድ ራሱን የመቀበል ችግር ነበረበት፡፡ በመቀጠልም ለራሱ እውቅና መስጠት ውስጥ ገባ፡፡ ከዚያም ወደ ጸብ አጫሪነት ተሸጋገረ፡፡ ያለ ወላጅ ያደገው መሐመድ ወላጅ አልባ ልጆችን አበዛ፡፡ አጋንንቶች እንዳደሩበት በማሰብ እራሱን ከመጠራጠሩ የተነሳ ህይወቱን የማጥፋት ሙከራ ያደርግ የነበረው ሰው ሌሎችን የማይቀበል እና የራሱን እምነት በሌሎች ላይ በኃይል በመጫን የሌሎችን ኃማኖት ለማጥፋት በወታደራዊ ኃይል የሚጠቀም ቀንደኛ ሰው ሆነ፡፡ በመሐመድ ስሜታዊ ንፅረተዓለም ሙስሊም ያልሆኑትን ማሸነፍና ማዋረድ ተከታዮቹን “ይፈውሳቸዋል” ብሎ ያምን ነበር፡፡ ይህ ፈውስ

አርነት በምርኮ ውስጥ ላሉት

"የኢስላማዊ ሰላም" የሚመጣውና አሸናፊ መሆን የሚቻለው በጦርነት ነው፡፡ ይሄ እውነት ደግሞ በቁርአን ውስጥ ተረጋግጧል፡፡ (9፡14-15)

በመጀመርያ መሐመድና ተከታዮቹ በመካ በሚኖሩ የመድበለ አማልክት አምላኪዎች ዘንድ ስደት ደርሶባቸዋል፡፡ ነገር ግን በመዲና የተጠናከረ ኃይል እንዳለው በተረዳ ጊዜ ነብያዊ አገልግሎቱን ያልተቀበሉትን የመድበለ አማልክት አምላኪዎቹንም፣ የአይሁዶቹንም ሆነ የክርስቲያኖቹን አቅም ማዳከም በመጀመሩ ዝምታን መምረጥና መገዛትን እንደ መፍትሔ ወስደውት ነበር፡፡

መሐመድ ሐሳባዊና ወታደራዊ መርሐ ግብር በመመስረት እርሱንና የኅብረተሰቡን እምነት በማንኛውም አገላለጽ ያልተቀበሉትን ስልታዊ በሆነ መንገድ ለማስወገድ ተንቀሳቅሷል፡፡ እንደ መሐመድ አባባል ከሆነ የመርሐ ግብሩ መሳካት ነብያዊ አገልግሎቱን የሚያረጋግጥና ነፃ አውጪ መሆኑን አመላካች ነው፡፡

የመሐመድ ነብያዊ አገልግሎት እንዴት እያደገ እንደሄደ ቁርአን ያሳያል፡፡ ይሄ ደግሞ በመሐመድ ግላዊ ጠንካራ ማስረጃዎች የተገለጠ ነው፡፡ እርሱን ያልተቀበሉትን የመግፋት፣ ጠላትነትና ጸብ አጫሪነቱ እያደገ መሄድ ችሏል፡፡ ሙስሊም ባልሆኑት ላይ የሚጫኑት ባህርያቶች ማለትም ዝምታ፣ የህሊና ክስና ዝቅ ዝቅ ማለት መሰረታቸው መሐመድ ራሱ ተቀባይነትን ከማጣቱ የተነሳ የመጡ ናቸው፡፡ የመሐመድ ሀይለኛነት፣ ከፍተኛ ጫናና ሌሎችን አለመቀበል የሚደርስባቸው "ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ አምናለሁ፡፡ በመሐመድም ነብይነት" የሚለውን ለመቀበል እምቢ የሚሉት ሁሉ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ 5

# ኢየሱስ የህማም ሰው

## የህማም ሰው

የኢየሱስ ህይወት ከመሐመድ የሚያንስ አይደለም፡፡ በመገፋትና ተቀባይነትን በማጣት የተሞላ ነው፡፡ የተደመደመው ደግሞ በመስቀል ነው፡፡ መሐመድ ለደረሰበት ስደት የሰጠው ምላሽ ቢኖር ተገቢ የሆነን ቅጣት በጠላቶቹ ላይ መፈጸም ነበር፡፡ የክርስቶስ ምላሽ ደግሞ ከዚህ ፍጹም የተለየ ነው፡፡

ልክ እንደ መሐመድ የኢየሱስ የቤተሰብ ሁኔታ ስንመለከተ በአመለካከት የተራራቁ ነበሩ፡፡ በወላጆቹ ህጋዊ ጋብቻ ባለመወለዱም ከህብረተሰቡ እንዲገለልም ተደርጎ ነበር (ማቴ 1፡18-25)፡፡ የተወለደው ውርደት በሚመስል ሁኔታ ውስጥ ነው (ሉቃ 2፡7)፡፡ ከውልደቱ በኋላ ሄሮድስ ሊገድለው ፈልጎ ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ መሸሸጊያ ፍለጋ ወደ ግብፅ ሸሸ (ማቴ 2፡13-18)፡፡

## ኢየሱስ ጥያቄ ቀረበበት

ኢየሱስ በ30 ዓመቱ አካባቢ የማስተማር አገልግሎቱን በጀመረ ጊዜ፤ ትልቅ የሆነ ተቃውሞ በህይወቱ አጋጥሞት ነበር፡፡ መሐመድ እንደተጠየቀው ሁሉ የአይሁዳውያን የኃይማኖት መሪዎች ያለውን ስልጣን ዝቅ ለማድረግና በጥያቄ ለመሞገት ጥረት አድርገው ነበር፡፡

> "...ኢየሱስ ከዚህ ከወጣ በኋላ፣ ጸሐፊትና ፈሪሳውያን ክፉኛ ይቃወሙትና በጥያቄም ያዋክቡት ጀመር ከአፉ በሚወጣውም ቃል ሊያጠምዱት ያደቡ ነበር"፡፡ ሉቃ 11፡53-54

ጥያቄዎቹም በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረጉ ነበሩ

- ኢየሱስ ለምንድን ነው በሰንበት የሚፈውሰው? ይሄ ጥያቄ የተጠየቀው የሰንበትን ህግ ሽሯል የሚለውን ለማሳየት ነው፡፡ (ማር 3፡2፤ ማቴ 12፡10)፤
- በምን ስልጣን ነው ነገሮችን የሚያደርገው? (ማር 11፡28፤ ማቴ 21፡23፤ ሉቃ 20፡2)፤
- ለሰው ሚስቱን መፍታት ህጋዊነት ነውን? ( ማር 10፡2፤ ማቴ 19፡3)
- ለቄሳር ግብርን መክፈል ተገቢ ነውን? ( ማር 12:15፤ ማቴ 22፡17፤ ሉቃ 20፡22)፤
- ታላቂቱ ትእዛዝ የትኛዋ ነችን? (ማቴ 22፡36)
- መሲሁ የማን ልጅ ነው? (ማቴ22፡42)
- ስለ ኢየሱስ አባትነት (ዮሐ 8፡19)

- ስለ ትንሳኤ ሙታን (ማቴ 22፡ 23-28፤ ሉቃ 20፡ 27-33)፤
- ምልክትን ስለማድረግ መጠየቅ (ማር 8፡11፤ ማቴ 12፡38፤ 16፡1)
- ከነዚህም በተጨማሪ ኢየሱስ ክስ ቀርቦበት ነበር
- በአጋንንት ተይዟል፡፡ "በአጋንንት ኃይል አጋንንንትን ያስወጣል፡፡ (ማር 3፡22፤ ማቴ 12፡24፤ዮሐ 8፡52፤ ዮሐ 10፡20)፤
- ሰንበትን የማይጠብቁ ደቀመዛሙርት አሉት (ማቴ 12፡2)፤ ወይንም የማንጻት ስርአት (ማር 7፡2፤ ማቴ 15፡ 1-2 ፤ ሉቃ 11፡38)፤ እና
- ተቀባይነት የሌለው ምስክርነት መስጠት (ዮሐ 8፡13)

## አውጋዦቹ

የኢየሱስን ህይወትና አስተምህሮ በምንመለከትበት ጊዜ ከብዙ ግለሰቦችና ቡድኖች ውግዘት ደርሶበተ ነበር፡፡

- ንጉስ ሄሮድስ ገና ህፃን ሳለ ሊገድለው ሙከራ አድርጎ ነበር፡፡ (ማቴ2፡16)
- በናዝሬት የሚኖሩ የራሱ ሰዎች ስሜቱን ጎድተውታል፡፡ (ማር 6፡3፤ ማቴ 13፡ 53፡58)፤ ከገደል ላይ ጥለውት ሊገድሉት ጥረት አድርገዋል፡፡ (ሉቃ 4፡ 28-30)
- የገዛ ቤተሰቡ አባላት አዕምሮውን አጥቷል በማለት ከሰውታል፡፡ (ማር 3፡21)
- ብዙ ተከታዮቹ በምድረበዳ ጥለውት ሄደዋል፡፡ (ዮሐ 6፡60)

- ሕዝቡ በድንጋይ ሊወግሩት ሞክረዋል፡፡ (ዮሐ 10፡31).
- የኃይማኖት መሪዎች ሊገድሉት ተማክረዋል፡፡(ዮሐ 11፡50)
- በውስጥ ካሉት መካከል በይሁዳ ተከድቷል፡፡ (ማር 14፡43፣ ማቴ 26 14-16፣ ሉቃ 22፡ 1-6፣
- ዮሐ 18፡2-3)
- አዕማድ ደቀመዝሙሩ በነበረው ጴጥሮስ ሦስት ጊዜ ተከድቷል፡፡ (ማር 14፡ 66-72፣ ማቴ 26፡ 69-75፣ ሉቃ 22፡54-62፣ ዮሐ 18)
- በመስቀል ላይ እንዲሞት የተደረገው ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበባት በኢየሩሳሌም ነበር፡፡ ይሄ የሆነው ደግሞ ከጥቂት ቀናት በፊት እንደ መሲህ በደስታ በተቀበሉበት ከተማ ውስጥ ነበር፡፡ (ማር 15፡12-15፣ ሉቃ 23፡ 18-23፣ ዮሐ 19፡15).
- በጥፊ ተመትቷል፣ ተፍተውበታል፣ የኃይማኖት መሪዎችም ተሳልቀውበታል፡፡ (ማር 14፡65፣ ማቴ 26፡ 67-68)
- በሮማውያን ወታደሮች ጸያፍ ስድብና መሳለቅ ደርሶበታል፡፡ (ማር 15፡16-20፣ ማቴ 27፡27-31፣ ሉቃ 22፡63-65፣ ሉቃ23፡11)
- በአይሁዳውያንና በሮማውያን ልዩ ፍርድ ቤቶች የሀሰት ክስ ቀርቦበታል፡፡ የሞት ፍርድም ተፈርዶበታል፡፡( ማር 14፡53-65፣ ማቴ 26፡ 57-67፣ ዮሐ 18፡ 28)
- ሮማውያን ከፍተኛ ወንጀል የሰሩ ሰዎችን በሚገድሉበት የመስቀል ሞት እንዲሞት ተደርጓል፡፡ ይሄ ደግሞ እንደ እርግማን መቆጠሩ አይሁዶች ትኩረት ሰጥተው እንዲከታተሉት አድርጓል፡፡ (ዘዳ 21፡33)

- በሁለት ወንጀለኞች መካከል ተሰቀለ፡፡ የደረሰበትን ስቃይ በመስቀል ላይ ታግሶ ሳለ አብዝቶ ተነቀፈ፡፡(ማር 15፡ 21-32፣ ማቴ 27፡32-44፣ ሉቃ 23፡32-36፣ የዮሐ 19 ፡23-30)

## *ተቀባይነትን ስላጣበት ሁኔታ የኢየሱስ ምላሽ*

እነዚህን ሁሉ ውግዘቶች በምንመለከትበት ጊዜ ኢየሱስ ሲቆጣና በአመጽ ሲመልስ አናይም፡፡ መበቀልንም አልፈለገም፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከመሰቀሉ በፊት በእርሱ ላይ ለሚቀርቡ ክሶች መልስ ከመስጠት ተቆጥቦ ነበር፡፡ (ማቴ 27፡14) ይሄንን ሐሳብ ቤተክርስቲያን ስለ መሲሁ የተነገረ ትንቢት ፍፃሜ እንደሆነ ታስተምራለች፡፡

> ተጨነቀ ተሰቃየም፣ ነገር ግን አፉን አልከፈተም፣ እንደ ጠቦትም ለዕርድ ተነዳ በሸላቾች ፊት ዝም እንደሚል በግ፣ አፉን አልከፈተም፤ (ኢሳ 53፡7)

አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስ ማን እንደሆነ ስለራሱ እንዲናገር በተጠየቀ ጊዜ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ዝምታን ይመርጥ ነበር፡፡ ይልቁንም መልሶ ጥያቄ የሚጠይቃቸው ጊዜ ነበር (ማቴ 21፡24፣ 22፡15)፡፡ የቱንም ያህል ሰዎች ከእርሱ ጋር ጦርነትን መግጠም ቢፈልጉም አይጨቃጨቅም ነበር፡፡

> በእርሱም ደስ የሚለኝ ምርጤ ይህ ነው፤ መንፈሴን በእርሱ ላይ አደርጋለሁ፤ ድምፁን በመንገድ ላይ በኀይል አያሰማም የተቀጠቀጠ ሸምበቆ አይሰብርም የሚጤስም የጥዋፍ ክር አያጠፋም፤ ፍትህን በታማኝነት ያመጣል ፍትህን በምድር እስኪያመጣ ድረስ፤ አይደክምም፤ ተስፋም አይቆርጥም፤

ደሴቶች በህጉ ይታመናሉ፡፡ (ማቴ 12፡19-20፣ ከኢሳ 42፡1-4 የተወሰደ)

ሰዎች ኢየሱስን በድንጋይ መውገር ወይም መግደል በፈለጉ ጊዜ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ዞር ይል ነበር፡፡ (ሉቃ 4፡30) ወደ መስቀል ሞት ሲሄድ ግን በዓላማና አስቦበት ነበር፡፡

እነዚህ ምላሽ የሚያሻቸው ነጥቦች ኢየሱስን በውግዘት ልምምድ ውስጥ እንዲያልፍ ፈተና ሆነውበት ነበር፡፡ ፈተናውንም አሸነፈ፡፡ ለተደረገበትም ውግዘት አልተሸነፈም፡፡ የዕብራውያኑ ጸሐፊ ምላሹን እንዲህ አድርጎ አስቀምጦታል፡

> በድካማችን የማይራራልን ሊቀ ካህናት የለንምና፤ ነገር ግን እንደ እኛ በማንኛውም ነገር የተፈተነ ሊቀ ካህናት አለን ይሁን እንጂ ምንም ኀጢአት አልሰራም፡፡ እንግዲህ ምህረትን እንድንቀበልና እንድናገኝ፣ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቀርብ (ዕብ 4፡15-16)

በወንጌላት ላይ ስለ ኢየሱስ ተገልፆ የምናየው ሐሳብ የሚያመለክተው በታላቅ ጥበቃና እረፍት ውስጥ ያለ፤ በእርሱ ላይ የተነሱትን የማጥፋት ፍላጎት እንዳልነበረው ያሳያል፡፡ ኢየሱስ ለነበረበት ውግዝና ምላሽ አለመስጠት ብቻ ሳይሆን ደቀመዛሙርቱም በሚወገዙበት ጊዜ ሊኖራቸው ስለሚገባ ምላሽ ስነመለኮታዊ ማዕቀፍ አሳይቷቸዋል፡፡ ቁልፍ የሆኑት ስነመለኮታዊ ጉዳዮች ከዚህ በታች ተገልጸዋል፡፡

# የኢየሱስ የውግዘት ስነ መለኮት

## ውግዘትን መቀበል

ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር መሲህ ውግዘት እንዲደርስበት መሆኑ አግባብ ያለው ነገር መሆኑን ግልፅ አድርጎ ተናግሯል፡፡ የእግዚአብሔር ሐሳብ የተወገዙትን እንደ ቁልፍ ድንጋይ አድርጎ ህንጻው እንዲገነባና ጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

> ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ (ማር 12፣ 11 ከመዝ 118፣ 22-23 የተወሰደ) በማቴ 21፣ 42 ላይም ይገኛል፡፡

ኢየሱስ እንደ ተወገዘ፣ እንደ ተሰቃየ ባርያ መሆኑን ኢሳይያስ ትንቢታዊ መልዕክት ተናግሯል፡፡ በእርሱ ስቃይ አህዛብ ሁሉ ሰላምና የኃጢአት ስርየትን ያገኛሉ፡፡

> በሰዎች የተናቀና የተጠላ፣ የህማም ሰውና ስቃይ
>
> ያልተለየው ነበር፡፡ ሰዎች ፊታቸውን እንደሚያዞሩበት ዐይነት፣ የተናቀ ነበር፣ እኛም አላከበርነውም፡፡ በእርግጥ እርሱ ደዌያችንን ወሰደ ሕመማችንንም ተሸከመ እኛ ግን በእግዚአብሔር እንደተመታ እንደተቀሰፈ፣ እንደተሰቃየም ቆጠርነው፣ ነገር ግን ስለ መተላለፋችን ተወጋ ስለበደላችንም ደቀቀ፤ በእርሱ ላይ የወደቀ ቅጣት ለእኛ ሰላም አመጣልን፣ በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን (ኢሳ 53፣ 3-5)

የዚህ ዕቅድ ማእከላዊ ሀሳቡ መስቀል ነው፡፡ ኢየሱስ በተደጋጋሚ ወደ ሞት እንደሚሄድ የሚያመላክት ነው፡፡

> ከዚያም የሰው ልጅ ብዙ መከራ እንደሚቀበል፣ በሽማግሌዎች፣ በካህናት አለቆችና በጸሐፍት እንደሚናቅ፣ እንደሚገደል፣ ከሦስት ቀንም በኋላ እንደሚነሳ ያስተምራቸው ጀመር፡፡ እነርሱም ይህን በግልጽ ነገራቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ኢየሱስን ለብቻው ወስዶ ይገስጸው ጀመር፡፡ (ማር 8፡31-32 እንደዚሁም ማር 10፡32-34፣ ማቴ 16፡21፣ 20፡17-19፣ 26፡2፣ ሉቃ 18፡31፣ ዮሐ 12፡23)

## አመጽን አለመቀበል

ኢየሱስ ግቡን ከማሳካት አንጻር በግልጽና በተደጋጋሚ ኃይል መጠቀምን አውግዟል፡፡ በመስቀል ላይ ሆኖ እንኳን በዚህ አቋሙ ጸንቶ ነበር፡፡ ኢየሱስም እንዲህ አለው “ ሰይፍን የሚመዝዙ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉ”፡፡ ማቴ 26፡-52 ኢየሱስ ወደ መስቀል እየሄደ ሳለ ኃይልን መጠቀምን በፈቃዱ ተወ ይሄንንም ያደረገው የመጣበትን ተልዕኮ ለመወጣት ነው፡፡ ይሄውም የሞትን ዋጋ እስከመክፈል ድረስ ነው፡፡

> “ኢየሱስም፣ የእኔ መንግስት ከዚህ ዓለም አይደለም፤ ቢሆንም ኖሮ አይሁድ እንዳይዙኝ ሎሌዎቼ በተከላከሉልኝ ነበር፣ አሁን ግን መንግስቴ ከዚህ አይደለም አለው”፡፡ ዮሃ 18፡-36

"ሰይፍ" የሚመጣበት ጊዜ እንዳለ አመላካች ነገር በወንጌል ላይ ተጠቅሶ እናያለን፡፡ ይሄንንም የምናገኘው ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ወደፊት ሊያገኛት የሚችለውን መከራ ለማሳየት ነው፡፡

"እኔ የመጣሁት ሰላምን በምድር ለማስፈን አይምሰላችሁ፡ ሰይፍን እንጂ" ማቴ 10፡-34

የቱንም ያህል ይሄኛው ጥቅስ ኢየሱስ አመጽን እንደሚፈቅድ ተደርጎ እንደማስረጃ ሲቀርብ ብናይም እውነታው ግን ክርስቲያኖች በክርስቶስ ባላቸው እምነት የተነሳ ቤተሰቦቻቸው በሚያገሏቸው ጊዜ ሊፈጠር የሚችለውን መከፋፈል ለማሳየት ነው፡፡

በሉቃስ ወንጌል ላይ ተመሳሳይ የሆነው ምንባብ ሰይፍ በሚለው ቃል ምትክ መከፋፈል የሚል ቃል ተጠቅሶ እናገኛለን ሉቃስ 12፡-51፡፡ ስለሆነም በዚህ ክፍል ላይ ሰይፍ የሚለው ቃል እንደምሳሌ ሆኖ የሚያመለክተው መከፋፈልን፣ የአንድ ቤተሰብ አባላት ከሌሎች የቤተሰብ አባላት መለያየትን ነው፡፡ ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚታሰበው ሌላኛው አተረጓጎም ደግሞ " ሰይፍ" የሚለው የክርስቲያኖችን ስደት ይወክላል የሚል ነው፡፡ ማለትም ሰይፉ የሚነሳው በክርስቲያኖች ላይ ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ምስክርነታቸው ነው፡፡

የኢየሱስ የኃይል አካሄድን አለመቀበሉ መሲሁ ሲመጣ ያደርገዋል ተብሎ ከሚጠበቀው አስተሳሰብ የተቃረነ ነበር፡፡ ይሄውም ህዝቡን ይታደጋቸዋል የሚለው ነው፡፡ የሚታደጋቸው ደግሞ ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ አንደዚሁም መንፈሳዊ ከሆነ ሁኔታ ነው ተብሎ ይታመን ነበር፡፡ ኢየሱስ ደግሞ ወታደራዊ የሆነውን አካሄድ ተቃውሞታል፡፡

መንግስቱ ፖለቲካዊ፣ የዚህ ዓለምም አለመሆኗንም ግልጽ አድርጎላቸዋል፡፡

ሰዎች የቄሳር የሆነውን ለቄሳር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር የግድ መስጠት እንዳለባቸውም አስተምሯቸዋል፡፡ (ማቴ 22፡-21) የእግዚአብሔር መንግስት በአንድ ስፍራ ተወስናለች የሚለውን አተያይ አስተባብሏል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የምትገኘው በሰዎች መካከል ሰለሆነ ነው(ሉቃ 17፡21)፡፡ በእግዚአብሔር መንግስት የተሻለውን ቦታ የሚይዘው ማነው? የሚል ጥያቄ ይዘው ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስን የሞገቱበት ምክንያት የእግዚአብሔር መንግስት እነርሱ በሚቀመጡበት ስፍራ የምትገኝ ነች ብለው አምነው ስለነበር ነው፡፡ ኢየሱስ ድግሞ የእግዚአብሔር መንግስት እነርሱ እንደተለማመዱት እንደ ፖለቲካ መንግስት ሰዎች ሰዎችን ጌታ ሆነው የሚገዙባት አለመሆኗን አሳይቷቸዋል፡፡ ፊተኛ ለመሆን ኋለኛ መሆን እንደሚኖር አስተምሯል፡፡ (ማቴ 20፡- 16፣27) የኢየሱስ ተከታዮች መገልገልን ሳይሆን ማገልገልን መፈለግ አለባቸው፡፡ (ማር 10፡- 43፣ ማቴ 10፡- 27)

የጥንቷ ቤተክርስቲያን የኢየሱስን አስተምህሮ ከልቧ ተቀብላው ነበር፡፡ እንደ ምሳሌ ያህል በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ከተከለከሉ የስራ ዘርፎች መካከል አንዱ ውትድርና ነበር፡፡ ክርስቲያን ወታደር የሚሆን ከሆን ከመግደል ይታቀብ ነበር፡፡

## ጠላትህን ውደድ

ሌላውን አለመቀበልና ማውገዝ ጠብ ያለበት ምላሽ ከሌላኛው ወገን እንዲነሳ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ ኢየሱስ መቼም ቢሆን ክፉ ያደረጉብንን ሰዎች መቅጣት ተቀባይነት አለው አላለም፡፡ ይልቁንም

ክፉ ለሚያደርጉባችሁ በክፉ ፈንታ መልካም አድርጉ ብሏል፡፡ (ማቴ 5፡- 38-42) በሌላው ላይ መፍረድ ስህተት ነው፡፡ (ማቴ 7፡- 1-5) ጠላታችንን መጥላት ሳይሆን መውደድ አለብን፡፡ (ማቴ 5፡-43) የዋሆች ምድርን ይወርሳሉ፡፡ (ማቴ 5፡-5) የሚያስተራርቁ ብጹአን ናቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና፡፡ (ማቴ 5፡- 9)

እነዚህ አስተምህሮቶች ደቀመዛሙርት ሰምተው እንዲረሱአቸው የሚገቡ ተራ ቃላት አልነበሩም፡፡ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት መልዕክቶቻቸው በአዲስ ኪዳን ተመዝግቦ የተቀመጠ ሲሆን በታላቅ መከራና ተቃውሞም ጊዜ ጭምር በእነዚህ መርሆዎች ተመርተዋል፡፡

> እስከዚህ ሰዓት ድረስ እንራባለን፣ እንጠማለን፣ እንራቆታለን፣ እንጎሰማለን፣ እንከራተታለን፣ በገዛ እጃችን እየሠራን እንደክማለን፤ ሲሰድቡን እንመርቃለን፣ ሲያሳድዱን እንታገሳለን፣ክፉ ሲናገሩን እንማልዳለን እስከ አሁን ድረስ የዓለም ጥራጊ የሁሉም ጉድፍ ሆነናል፡፡ (1ቆሮ 4፡-11-13፣ 1ጴጥ 3፡-10፣ ቲቶ 3፡-1-2 ሮሜ 12፡- 14-21)

ሐዋርያት በአማኞች ፊት የኢየሱስን ምሳሌ ይዘው ተመላልሰዋል፡፡ (1ጴጥ 2፡-21-25) ጠላትህን ውደድ የሚለው በማቴ 5 የተጠቀሰው ክፍል የጥንቷ ቤተክርስቲያን በተደጋጋሚ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመውሰድ በጽሑፎቻቸው ይጠቀሙባቸው ነበር፡፡

## ስደትን ለመቀበል የተዘጋጀህ ሁን

ኢየሱስ ለተከታዮቹ ያስተማረው ስደት የማይቀር መሆኑን ነው፡፡ መመታት፣ መጠላት፣ መሰደድና ለሞት ታልፎ መሰጠት

እንደሚያጋጥማቸው ነግሯቸዋል፡፡ (ማር 13፡ 9-13፤ ሉክ 21፡12-19፤ ማቴ 10፡ 17-23)

ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን በሚያሰለጥናቸው ጊዜ የተቀበሉትን መልዕክት ለሌሎች እንዴት ማድረስ እንዳለባቸው መመርያ ሰጥቷቸዋል፡፡ በዚህም ደግሞ የመገፋትን ህይወት ይለማመዳሉ፡፡ በተቃራኒው ደግሞ የመሐመድን አስተምህሮቶች በምንመለከትበት ጊዜ ሙስሊሞች ለሚደርስባቸው ማንኛውም ስቃይ የኃይል ጥቃት ሰውን በማረድም ጭምር ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታታቸዋል፡፡

ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ያስተማራቸው በቀላሉ “ የእግራችሁን ትቢያ አራግፋችሁ ሂዱ” የሚል ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ለተቃዋሚዎቻቸው አንዳችም ክፉ ምላሽ ሳይሰጡ እንዲሄዱ ነበር ያስተማራቸው፡፡ (ማር 6፡11፤ ማቴ 10፡14) “ወደ ቤትም ስትገቡ ሰላምታ ስጡ ቤቱም የሚገባው ቢሆን ሰላማችሁ ይድረስለት፤ ባይገባው ግን ሰላማችሁ ይመለስላችሁ”፡፡

ይሄንን አስተምህሮ ደግሞ ኢየሱስ ምሳሌ በመሆን አሳይቷል፡፡ ወደ ሳምራውያን መንደር በመጣ ጊዜ ሊቀበሉት ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ በዚህ ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ከሰማይ እሳት አውርዶ እንድትበላቸው እንዲያደርግ ጠየቁት፡፡ ኢየሱስ ግን ገሰፃቸውና እልፍ ብሎ ሄደ፡፡ (ሉቃ 9፡54-56)

ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ያስተማራቸው ነገር ቢኖር ስደት ሲያጋጥማቸው ወደሌላ ከተማ እንዲሸሹ የሚያስገነዝብ ነበር፡፡ (ማቴ 10፡23) በሚሰደዱ ጊዜ ምን መናገር እንዳለባቸው መንፈስ ቅዱስ ስለሚያሳያቸው አንዳች መጨነቅ የለባቸውም፡፡ (ማር 10፡ 19-20፤

ሉቃ 12፡11-12፣ 21፡14-15) እንዲፈሩም አይገባም፡፡ (ማር 10፡31፣ ማቴ 10፡26)

ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ለየት ያለ አስተምህሮ ቢኖር ተከታዮቹ በሚሰደዱበት ጊዜ የግድ መደሰት እንዳለባቸው ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ከነብያቶቹ ጋር እነርሱም የታወቁ ስለሆኑ ነው፡፡

> "ሰዎች ስለ ሰው ልጅ ሲጠሉአችሁ ሲለዩአችሁም ሲነቅፉአችሁም ስማችሁንም እንደ ክፉ ሲያወጡ ብፁዓን ናችሁ፡፡ እነሆ ዋጋችሁ በሰማይ ታላቅ ነውና በዚያን ቀን ደስ ይበላችሁ ዝለሉም አባቶቻቸው ነቢያትን እንዲህ ያደርጉባቸው ነበርና" (ሉቃ 6፡22-23፣ ማቴ 5፡11-12)

ይሄ መልዕክት የጥንቷ ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ ከነበራት መሰጠት የተነሳ ሙሉ በሙሉ በፍርሃት ውስጥ ስለማለፏ በርካታ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡

> "ነገር ግን ስለ ጽድቅ እንኳን መከራን ብትቀበሉ ብጹአን ናችሁ" (1ጴጥ 3፡14፣ 1ቆሮ 1፡5፣ ፊሊ 2፡ 17-18፣ 1ጴጥ 4፡ 12-14)፡፡

ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ከስደት ባሻገር የዘላለምን ህይወት ወደፊት እንደሚቀበሉ ተስፋ ሰጥቷቸዋል፡፡የተሻለው ነገር ወደ ፊት የሚሆን ነው የተስፋ ቃል ለመውረስ ደግሞ በህይወት ታማኝ ሆኖ መቀጠል ይገባል (ማር 10፡29-30፣ ማር 13፡13)፡፡

# ምዕራፍ 6

# መስቀሉ የአርነታችን መንገድ

## መሐመድ ለመስቀል የነበረው ጥላቻ

በመንፈሳዊው ዓለም በመኖራችን ምክንያት መሐመድ መስቀልን መጥላቱ የተገባ አልነበረም፡፡ በትውፊቶች የተዘገበውን አልዋቂዲ እንደሚናገረው ከሆነ፤ መሐመድ ሰው ቤት ሲገባ የመስቀል ምስል ያለበትን ማንኛውንም ነገር ካገኘ ማጥፋት ይቀናው ነበር[1]፡፡

መሐመድ ለመስቀል ያለው ጥላቻ ሥር ከመስደዱ የተነሳ ኢየሱስ ወደ ምድር በሚመለስበት ጊዜ የሙስሊሞች ነብይ በመሆን መስቀልን ከምድረ ገፅ ያጠፋል፡፡ ክርስትናንም ያስወግዳል ብሏል፡፡

አቡ ሁራሪያ እንደዘገበው፡ የአላህ ሐዋርያ እንዲህ
ብሏል፡፡ “ነፍሴበእርሱ እጅ በተያዘችው እምላለሁ

1 W.Muir, The life of Muhammad. Volume3, p.61, note 47

በእርግጥም (ኢየሱስ) የማርያም ልጅ በመካከላችሁ ይወርዳል፡፡ ለሰው ልጆችም በፍትህ ይፈርዳል፡፡ ይሄንን የሚያደርገው ደግሞ እንደ ገዢ ሆኖ ነው፡፡ መስቀልን ይሰብራል፡፡ አሳማንም ይገድላል፡፡ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎችም ቀረጥ እንዳይከፍሉ ያደርጋል፡፡ (ሳኢህ አልቡኻሪ የነቢያቶች ታሪክ ያለበት መጽሐፍ 4፡60፡ 3448)

በሌላ መልኩ ኢየሱስ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ "ሦስተኛው ምርጫ" ይጠፋል፡፡ ስለሆነም ክርስቲያኖች የግድ ወደ እስልምና ይቀየራሉ፡፡ ይሄንን ማድረግ ካልቻሉ ግን ይገደላሉ፡፡

አሁን አሁን መሐመድ ለመስቀል ያለውን ጥላቻ የሚጋሩ እጅግ ብዙ ሙስሊሞችን ማግኘት ይቻላል፡፡

- እንደ ጎርጎርዮሳውያን አቆጣጠር በ1998 ዓ.ም የገና በአል ከመከበሩ ከሁለት ቀን በፊት በፓኪስታን ፌይሳላባድ በምትገኝ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የተንጠለጠለ መስቀል በሙስሊሞች መሪ እንዲወርድ ተደርጓል[2]፡፡
- እንደ ጎርጎርዮሳውያን አቆጣጠር በወርሀ የካቲት 18/ 2004 ዓ.ም በአልባንያ በምትገኝ የቅዱስ አንድሪው ቤተክርስቲያን በፎቶግራፍ የተደራጀን ማስረጃ አቅርበዋል፡፡ እንደ የፎቶግራፍ ማስረጃው ከሆነ በጣራው ላይ የተንጠለጠለን መስቀል አውርደው ሰባብረዋል[3]፡፡ በኮሶቮ አቅራብያ

---

[2] Annual Report on International Relegious Freedom for 1999. US State Department <http//www.thepersecution.org/used/us99irf.html>

[3] ERP-KLM Info Service. Newsletter 17/3/ 2005. <http:// www.Kosovo. Net/news/ archive/2005/ March_17/1. Html>

በሚገኙ የክርስቲያኖች የመቀበርያ ስፍራዎች በመሄድ መስቀሎችን በመነቃቀል አመጽ እንዲነሳ አድርገዋል[4]፡፡

- እንደ ጎርጎርዮሳውያን አቆጣጠር በሚያዝያ 2007 ዓ.ም በባግዳድ ማለትም ክርስቲያኖች በሰፈሩበት አል- ዳዎራ በሚባል ስፍራ የሙስሊም አማጽያኖች ክርስቲያኖችን በቤተክርስቲያናቸው ሕንጻ ላይ የተንጠለጠሉትን በእይታ ውስጥ ያሉ መስቀሎችን እንዲያስወግዱ መመርያ ሰጥተዋል፡፡ ይህ ደግሞ ሊሆን የቻለው የሙስሊሞች ህግ (ፈትዋ) የክርስቲያኖችን የመስቀል ምልክት መጠቀም በጥብቅ ስለሚከለክል ነው[5]፡፡
- በ2007 ዓ.ም ሀማስ ጋዛን በተቆጣጠረ ጊዜ መስቀልን የማጥፋት አመጽ አድርጓል፡፡ ጋዛ በሚገኝ የካቶሊኮች የሴቶች ገዳምና ትምህርት ቤት ጭንብል የለበሱ ወንዶች በመገኘት አካባቢውን በማመሰቃቀል፣ ዘረፋ ያካሄዱ ሲሆን ትኩረት ያደረጉትም መስቀልን ማጥፋት ላይ ነበር፡፡ በጋዛ የሚኖር የአይን እማኝ የሆነ ክርስቲያን እንደዘገበው ከሆነ በጋዛ ውስጥ ተሰሚነት ካላቸው ሰዎች አንደኛው የስቅለት ስእል ያለበትን መስቀል ከአንገቱ ጀምሮ በመቆራረጥ "ይሄ አልተፈቀደም" ሲል እኩይ የሆነውን ድርጊት ፈጽሟል[6]፡፡

---

4 Jared Israel, " Eradication of an ancient culture… The destruction of the Churches of Kosovo'.<http:// emperors clothes.com list.htm>.
5 Extrimists threaten Church in Baghdad'. Zenit News Service. 19 April 2007. <http://www.zenit.org/article/19414?I=english>
6 Fears in PA : Gaza May turn into Taliban-style Emirate. MEMRI Special Dispatch Series 1633, Palestinian Authority / Jihad & Terriorism Studies Project, June 26, 2007. <http:// memri.org/ bin/articles.cgi? page= archives& Area=sd&ID= SP 163307> This is cited from AL-Quds AL- Arabi (London), June 20, 2007.

- በጥቅምት 29/ 2007 ዓ.ም በዕለተ ሰኞ በማሌዥያውያን ፓርላማ ውስጥ የፓርላማ አባል የሆነ ጡሀን ሰይድ ሁድ ኢድሮስ የተባለ የፓርላማ አባል ኃይማኖታዊ የሆኑ በቤትክርስቲያኖች ትምህርት ቤቶች ፊትለፊት የሚሰቀሉ ምልክቶችን በተመለከተ "ለኃይማኖቴ፣ ለብሔሬ፣ እንደዚሁም ለሀገሬ ሀላፊነት እንደሚሰማው ሰው …እነዚህ መስቀሎች ድምጥማጣቸው መጥፋት አለበት ብዬ አምናለሁ" ሲል ቁጭቱን በአደባባይ ተናግሯል[7]፡፡
- በህዳር 2004 ዓ.ም እንግሊዝ አገር የሚገኝ ቤልማርሽ የተሰኘ እስር ቤት በ1.6 ሚሊዮን ፓውንድ መስጊድ የማሰራት እቅድ እንዳለው ሪፖርት አድርጓል፡፡ ተቋሙ የተለያዩ ቤተ እምነቶች ለሆኑት ክርስቲያኖች ጸሎት ቤት አስገንብቶ ጥቅም ላይ እንዲውሉ እያደረገ የሚገኝ ሲሆን ከሙስሊሞቹ ጋር በእስር ቤት የሚገኝ አንዱ የዚህን መስጊድ መሰራት ተቃውሟል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ አንዳንዶቹ በሽብር ፈጣሪነት ተፈርጀው የታሰሩ ስላሉበት ነው፡፡ እነዚህ አክራሪዎች ሙስሊሞች በሚጸልዩበት ጊዜ እነዚህ የጸሎት ቤቶች መስቀላቸውን እንዳይታይ በጨርቅ መሸፈን አለባቸው ሲሉ በብርቱ ተቃውሟቸውን አሰምተዋል[8]፡፡

---

[7] The Hansard record of the Third Meething of the fourth Session of Eleventh Parliament (Dewan Rakyat) of Malasia, on Monday, 29 October 2007, PP. 143-44http://www.parlimen.gov.my/hidex/pdf/DR-29102007.pdf.

[8] Reported by Justin Penrose, writhing in the Sunday Mirror of November 7.2004. Daniel Pipes offered a critique of this dission in his ' Londonistan Follies' blog http://www.danielpipes.org/blog /298.

አርነት በምርኮ ውስጥ ላሉት

- በእንግሊዝ ሌላ መስቀልን የሚያጥላላ አንድ ድርጊት ተከስቶ ነበር፡፡ የለንደን ባቡር ተቆጣጣሪ የሆነው መሐመድ አዛዊ የእንግሊዝን ዘውድ በደንብ ልብሱ ላይ ማድረጉ በፍጹም እንዳልተስማማው በብሶትና በንዴት ተናግሯል፡፡ እንደ ምክንያት አድርጎ ያቀረበው ደግሞ አነስ ያለና አምስት ሚሊ ሜትር የምትሆን መስቀል ስላለበት ነው፡፡ የሰራተኞችን ጉዳይ ወደ ሚከታተለው የከተማው ልዩ ፍርድ ቤት በመቅረብ በከተማው የፖሊስ ተቋም ላይ ያለውን ተቃውሞ አሰምቷል፡፡ እንደ አገላለጹ ከሆነ "ይሄ የዘር መድልዎ ነው" ሲል ተደምጧል፡፡ ክሱ ተቀባይነት ባያገኝም ከኃይማኖት አንፃር ዘውዱን ለማድረግ ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች ያለማድረግ ፈቃድ እንዲሰጣቸው የፖሊስ ባለስልጣኑ ውሳኔውን አስተላልፏል፡፡

የቀድሞው የካንተርበሪ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ጆርጅ ኬሪ እንደ ጎርጎሮሳውያኑ አቆጣጠር በ1995 ዓ.ም ሳውዲ አረቢያ ደረታቸው ላይ ያንጠለጠሉትን መስቀል እንዲያስወግዱ በኃይል ተጠይቀዋል፡፡ ዴቪድ ስኪድሞር ኤጲስቆጶስ በተሰኘ የዜና አገልግሎት እንደዘገበው ከሆነ፡

> ኬሪ ከግብጽ ተነስተው ወደ ሱዳን እየበረሩ ሳለ ሳውዲ አረቢያ እንዲያርፉ አስገዳጅ ሁኔታ አጋጥሟቸው ነበር፡፡ የቀይባህር ጠረፋማ ከተማ በሆነችው ጅዳ ሲቃረቡ ኬሪ ማንኛውንም ኃይማኖታዊ ምልክቶች ማለትም አንገታቸው ላይ ያጠለቁትን ቁስ መሆናቸውን የሚያሳየውን ዘለበትና

በደረታቸው ላይ ያንጠለጠሉትን መስቀል እንዲያስወግዱ ተነግሯቸዋል[9]፡፡

የቱንም ያህል መስቀል በሙስሊሞች ዘንድ የተወገዘም ቢሆን በክርስቲያኖች ዘንድ ግን ነፃ የመውጣታችን ምልክት ሆኖ ይታያል፡፡

# መስቀል፣ ተቀባይነትን ማጣትና እርቅ

በክርስቲያኖች መረዳት መሰረት የሰው ልጆች ትልቁ ችግር ኃጢኣት ነው፡፡ ኃጢኣት ደግሞ የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን እንዲያጡና እርስበርሳቸው እንዳይቀባበሉ አድርጓል፡፡ ይሄ ባይተዋርነት ውጤቱ ደግሞ መገለልን አስከትሏል፡፡ አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመተላለፋቸው ከኤደን ገነት ተባረዋል፡፡ ስለሆነም ከእግዚአብሔር መገኘት የተገለሉ እንዲሆኑ ሆኗል፡፡ በመውደቃቸው የተነሳ ደግሞ የተረገሙ ሆነዋል፡፡

የእስራኤልን ታሪክ በምንመለከትበት ጊዜ እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ከእርሱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዲኖራቸው ቃልኪዳን ገብቶላቸዋል፡፡ የእስራኤል ህዝብ ግን ይሄንን ሐሳብ አልተቀበሉም፡፡ ይልቁንም በራሳቸው መንገድ ተጉዘው ፍርድን በራሳቸው ላይ አምጥተዋል፡፡

በሰው ላይ የመጣውን ፍርድና ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማጣትን ሊያሸንፍ የቻለው ቁልፍ ነገር መስቀል ነው፡፡ ኢየሱስ ተቀባይነትን እስከማጣት ደርሶ ራሱን ዝቅ ቢያደርግም የመስቀሉ

---

9 David Skidmore . 'Heart speaks to heart during Archbishop of Canterbury 's visit to Chicago.' http://www.wfn. org /1996/06/ msg 00144.htm.

ኃይል ግን በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን ግድግዳም ጭምር ማሸነፍ ችሏል፡፡ ኢየሱስ ለዓለም ኃጢአት ሲል ሰዎች የጎዱትን ጉዳት ከምንም ሳይቆጥር ነፍሱን አሳልፎ በመስጠት ለሁላችንም መስዋእት ሆኗል፡፡ በዚህ ምክንያት የሰው ልጆችን የተጣሉ እንዲሆኑ ያደረገው ኃይል መስዋእት በተከፈለበት ፍቅር ተሸናፊ ሆኗል፡፡ይሄኛው ኢየሱስ በመስቀል ላይ ያሳየው ፍቅር ማንው የሌለውና እግዚአብሔር ለዓለም ሁሉ የሰጠው ስጦታ ነው፡፡

> በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ አለሙን እንዲሁ ወዷልና፡፡(ዮሐ 3፡16)

የሰው ልጆች እግዚአብሔርን በመበደላቸው ምክንያት ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት ሊቀበሉት የተገባቸውን ቅጣት እርሱ እንዲቀበለው ሆኗል፡፡ ይሄ የሰው ልጆች ሁሉ የተገባቸው ቅጣት ደግሞ ሞት ነው፡፡ ስለሆነም በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ የኃጢአትን ይቅርታ ያገኛሉ፡፡ እንደዚሁም የዘላለም ህይወት ወራሽ ይሆናል፡፡ በዚህም መንገድ ኢየሱስ ተቀባይነት ማጣትን በተቀጣው ቅጣት እግዚእብሔርን በማስደሰት ማሸነፍ ችሏል፡፡

በሙሴ መጻሕፍት የመስዋእት ማቅረብን ምሳሌ በምንመለከትበት ጊዜ የሚፈሰው ደም ኀጢአትን ያስተሰርይ ነበር፡፡ ክርስቲያኖች ደግሞ ይሄንን ሀሳብ የሚተረጉሙት የኢየሱስ ክርስቶስን በመስቀል ላይ መሞት አስፈላጊነት ነው፡፡ በነብዩ ኢሳይያስ የባርያውን ሥቃይን አስመልክቶ የተነገረው ሐሳቡን ግልጽ ያደርገዋል፡፡

> እኛ ግን በእግዚአብሔር እንደ ተመታ ፣ እንደ ተቀሰፈ፣ እንደ ተሰቃየም ቆጠርነው፡፡ ነገር ግን እርሱ ስለ

> መተላለፋችን ተወጋ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ በእርሱ ላይ የወደቀው ቅጣት ለእኛ ሰላም አመጣልን፤ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን፡፡ መድቀቁና መሰቃየቱ ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር፤ እግዚአብሔር ነፍሱን የኀጢአት መስዋእት ቢያደርገውም እንኳ፣ ዘሩን ያያል፤ ዕድሜውም ይረዝማል፤ የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእርሱ ይከናወናል፡፡ ስለዚህ ድርሻውን ከታላላቆቹ ጋር እሰጠዋለሁ፤ ምርኮውን ከኀያላን ጋር ይካፈላል፤ እስከ ሞት ድረስ ሕይወቱን አሳልፎ በመስጠቱ፣ (ኢሳ 53፡5፣10፣12)

ሐዋርያው ጳውሎስ ጠንካራ በሆነው የሮሜ መልዕክቱ የኢየሱስ ክርስቶስ መስዋእትነት በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረውን ተቀባይነት ማጣትን በእርቅ ፍጻሜ እንዲኖረው አድርጓል፡፡

> ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኀጢአተኞች ሞቶአልና፡፡ ስለ ጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና፤ ስለ ቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ኀጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቷልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል፡፡ ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቁጣው እንድናለን፤ ይህም ብቻ አይደለም ፣ ነገር ግን አሁን መታረቁን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን፡፡ (ሮሜ 5፡6-11)

ይሄኛው የማስታረቅ ስራ በሦስተኛ አካል ማለትም የሰው ልጆችን ጨምሮ፣ በመላእክት ወይንም በአጋንንቶች የሚነሳ ማንኛውንም ኩነኔ ያሸነፈ ነው፡፡ (ሮሜ 8፡38)

እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል? ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም? እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው የሚኮንንስ ማነው? ከፍታም ቢሆን ዝቅታም ቢሆን ልዩ ፍጥረትም ቢሆንም በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ፡፡ (ሮሜ 8፡31-33፤ 39)

ይሄ ብቻም አይደለም ክርስቲያኖች የማስታረቅን አገልግሎት እንዲያገለግሉ አደራ ተጥሎባቸዋል፡፡ ማለትም ለሌሎች የሚደረግ የማስታረቅ ስራ እንደዚሁም በመስቀሉ የተሰራውን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የማግኘትን መልእክት ማወጅን ያጠቃልላል፡፡

> ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ ፡፡ እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልዕክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን (ሮሜ 2ቆሮ 5፡18-20)

# ትንሳኤና አርነት

## *ትንሳኤ*

*የመሐመድ መገለጥ ምንም ዓይነት የአቋም ለውጥ ሊታይበት ያልቻለው አርነትን አስመልክቶ የሚያንጸባርቀው መሻት ነው፡፡ ይሄንንም ለማሳካት ሲል የእርሱን ጠላቶች ለህጉ እንዲገዙ ያስገድዳቸው ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ ራሳቸውን በእርሱ መመርያና ስልጣን ሥር ያስገዙ ነበር፡፡ ይሄንን ማድረግ ባይችሉ ግን የዲህሚ ህግ ተገዢዎች እንዲሆኑ በኃይል ይገደዳሉ፡፡ ሦስተኛው ምርጫቸው ግን ሞት ነበር፡፡*

*የክርስቶስን አገልግሎት በተመለከተ የክርስቲያኖችን መረዳት በምንመለከትበት ጊዜ አርነት አለ ይሄ አርነት ደግሞ የተገኘው በክርስቶስ የማዳን ሥራ ነው፡፡ የተሰቃየው አገልጋይ ዓላማ ራሱን ማዋረድና በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረውን ተቀባይነት ማጣትን ማስቀረት ነው፡፡*

*አርነት የመጣው በክርስቶስ ትንሳኤና እርገት ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ሞትና ማንኛውም ኃይል የተሸነፈበት ስለሆነ ነው፡፡*

> *ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ አስቀድሞ አይቶ ነፍሱ በሲኦል እንዳልቀረች ሥጋውም መበስበስን እንዳላየ ተናገረ ይሄን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሳው ለዚህም ነገር እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን፤ ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎአልና የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ ይህን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው፡፡ …እንግዲህ ይህን እናንተን የሰቀላችሁትን*

> ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ ፡ ፡ (ሐዋ 2፥31-36)

ሐዋርያው ጳውሎስ በፊሊጲስዩስ መልዕክቱ ታዋቂ በሆነው ምንባብ ላይ ኢየሱስ የቱን ያህል ራሱን እንዳዋረደ፣ በፈቃዱ የባርያን መልክ የራሱ እንዳደረገ እንረዳለን፡ ፡ የታዘዘውም ደግሞ እስከ መስቀል ሞት ድረስ ነው፡ ፡ እግዚአብሔርም ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፡ ፡ በመንፈሳዊ ስልጣናት ሁሉ ላይ የበላይ አደረገው፡ ፡

ይሄ በክርስቶስ የተገኘው ነፃ የማውጣት ድል በእግዚአብሔር ሉአላዊ ፈቃድ ውስጥ አስቀድሞ የነበረና በመስቀሉ የተከናወነ ነው፡ ፡

> እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም ነገር ግን የባርያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳን የታዘዘ ሆነ በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለልክ ከፍ ከፍ አደረገው ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይኸም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ ...(ፊሊ 2፥4-10)

## የመስቀሉ ደቀመዝሙር

ለክርስቲያን ክርስቶስን መከተል ማለት ሞትና ትንሳኤውን ማረጋገጥ ማለት ነው፡፡ ኢየሱስና ተከታዮቹ በተደጋጋሚ ከክርስቶስ ጋር የመሞትን አስፈላጊነት አመላክተዋል፡፡ ያ ማለት ደግሞ ወደ ሞት የሚመራውን አሮጌውን መንገድ መተውና ዳግም በመወለድ በክርስቶስ የፍቅርና የእርቅ አዲስ መንገድ በመነሳት ለራሳችን ሳይሆን ለእግዚአብሔር መኖር ነው፡፡

የክርስቶስን መከራ የተካፈሉ ሰዎች ልምዳቸውን ሲናገሩ በኑሯቸው ያለፈው ፈተና ድልን በሕይወታቸው እንደተቀዳጁ የታየበት፣ ተሸናፊ አለመሆናቸውም የተረጋገጠበት ነው፡፡ በዚህም ታማኝ የሆኑ አማኞችን የጭካኔ ኃይል ካለበት ከዚህ ዓለም እግዚአብሔር ነፃ እንዳወጣ ያሳየ ነው፡፡

> በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ ፡፡ ነፍሱን ሊያደን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና ስለ እኔና ስለ ወንጌል ነፍሱን የሚያጠፉ ሁሉ ግን ያድናታል፡፡ (ማር 8፡34-35 እንደዚሁም (1ኛ ዮሐ 3፡14፣ 16፣ 2ቆሮ 5፡14-15፣ ዕብ 12፡1-2)

# ተቀባይነትን የማጣት ሁለት ወጎች

መሐመድና ኢየሱስ በዓለም ላይ ያሉት የሁለት ታላላቅ ኃይማኖቶች መስራቾች መሆናቸው የታወቀ ነው፡፡ ሁለቱም ጠንካራና ቀጣይነት የነበረው ተቀባይነትን የማጣት ሁኔታ አጋጥሟቸዋል፡፡ ይሄ ተቀባይነትን ማጣት በሁለቱም ላይ የታየው ከልጅነታቸው ጀምሮ ነው፡፡ ተቃውሞ ደግሞ የተነሳባቸው

ከቤተሰብ አባላት ጀምሮ እስከ የኃይማኖት መሪዎች ጭምር ነው፡፡ ሁለቱም እርኩሳን መናፍስቶች ተቆጣጥሯቸዋል ተብለው ተከሰዋል፡፡ ሁለቱም ተፌዞባቸዋል፤ በጥብቅ ተነቅፈዋል፡፡ ሁለቱም በስቃይ ውስጥ አልፈዋል ክህደትም ተፈጽሞባቸዋል፡፡ ሁለቱም በሕይወታቸው ዛቻ ነበረባቸው፡፡

እንደዛም ሆኖ እነዚህ ማንም ሊያውቃቸው የሚችሉ መመሳሰሎች እያሉ እነዚህን ሁለት ትላልቅ ኃይማኖቶች ሊለዩ የሚችሉ ልዩነቶችም አሉ፡፡ የመሐመድን የሕይወት ታሪክ በምንመለከትበት ጊዜ በአብዛኛው ለሰው ልጆች የነበረው ምላሽ አሉታዊ ነበር፡፡ ራስን አለመቀበልና ጸብ አጫሪነት ባህሪያቶቹ ነበሩ ወደ ኢየሱስ በምንመጣበት ጊዜ ግን አቅጣጫው ሙሉ በሙሉ የተለየ ነበር፡፡ አለመቀበልን ያሸነፈው በሌሎች ላይ ጫና በማሳደር አልነበረም፡፡ ይልቁንም ማፈሪያ በሚመስል ሕይወት ውስጥ በማለፍም ጭምር እንጂ፤ እንደ ክርስቲያኖች እምነት ከሆነ ተቀባይነት የማጣትን ኃይል አሸንፏል፡፡ ህመሙንም ፈውሷል፡፡ የመሐመድ ሕይወት በዲህማ ህግ መሠረት ምን ያህል መንፈሳዊ እስራት እንዳለ ወሳኝ ነገሮችን ይዟል፡፡

የክርስቶስን ሕይወት በምንመለከትበት ጊዜ በዲህማ ህግ የሚሰቃዩትን ክርስቲያኖች ሁለንተና ነፃ የሚያወጣ ነው፡፡

# መንፈሳዊ ንጽረተ ዓለም

እዚህ ጋር ልንጠቅሰው የተገባው ንጽረተ ዓለም የተቃኘው በአዲስ ኪዳን ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆላስይስ አማኞች በጻፈው መልዕክቱ በጸሎቱ እንደሚያስባቸው ይነግራቸዋል፡፡

> እያደጋችሁ ከደስታም ጋር በሁሉ ለመጽናትና ለመታገስ እንደ ክብሩ ጉልበት መጠን በኃይል ሁሉ እየበረታችሁ በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገናችሁ በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን፡፡ እርሱ ከጨላማ ሥልጣን አዳነን ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግስት አፈለሰን፡፡ (ቆላ 1፡12-14)

እንደ ጳውሎስ አመለካከት ከሆነ ሰዎች በባህሪያቸው በሰይጣንና በአጋንንቶች ኃይል ስር ናቸው፡፡ ነገር ግን በክርስቶስ ባላቸው እምነት ምክንያት ከእርኩሳን መናፍስት ተፅዕኖ ነፃ ወጥተዋል፡፡ ጄ.ኤች ሀውልደን የተባሉ በኦክስፎርድ የትሪኒቲ ኮሌጅ የነገረ መለኮት ምሑር የጳውሎስን የስነ መለኮት ንጽረተ ዓለምን አስመልክቶ ያላቸውን አመለካከት እንደዚህ ጽፈዋል፡

> … ስለ ሰው ማንነት የውስጥ መረዳት አለው፡፡ ሰው በአቋሙ በመጽናትና ኃጢአት በማድረግ ብቻ ከእግዚአብሔር ሐሳብ የወጣ አልነበረም፡፡ ይሄ አጽናፈ ዓለም በዲያቢሎስ ኃይላት ተፅዕኖ ስር ከመሆኑ የተነሳ እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ይልቅ ለዲያቢሎስ አምባገነናዊ አስተዳደር መገዛት ችሏል፡፡ የሰው ከእግዚአብሔር ሐሳብ ማፈንገጥ በሰው ልጆች ሁሉ ፊት የሚስተዋል የጋራ ባህሪ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ ለአይሁዳውያንም ሆነ ለአሕዛብ የሚሰራ እውነት ነው፡፡ ምክንያቱም የሰው ልጆች ሁሉ የአዳም ልጆች ናቸውና፡፡ (Paul's Letters from Prison, P 18)

ሀውልደን ሐሳባቸውን ለማብራራት እንደሞከሩት የጳውሎስ ንጽረተ ዓለም የሚያሳየው የሰው ልጆች ከሰይጣን እስራት ነፃ መሆን እንዳለባቸው ነው፡፡ “(አጋንንታዊ ኃይላትን በተመለከተ የሰው ልጆች ከነሱ ተፅዕኖ ነፃ መውጣት አለባቸው” ገጽ 18)፡፡ ይሄንን ቁልፍ ሚና ኢየሱስ የወሰደው ደግሞ በሞትና በትንሳኤው ነው፡፡ ይሄ እውነት ደግሞ በኃጢአት ላይና የሰው ልጆችን በባርነት ተፅዕኖ ስር እንዲሆኑ ባደረጉት የዲያቢሎስ ኃይላት ላይ ድልን እንድንቀዳጅ አድርጓል፡፡

ሐዋርያው ዮሐንስ በመጀመርያው መልዕክቱ እንደጻፈው

> ከእግዚአብሔር እንደ ሆንን ዓለምም በሞላው በክፉው እንደ ተያዘ እናውቃለን፡፡ (1ኛ ዮሐ 5፡19)

ጳውሎስ እንዳለው ዓለም ሁሉ በጨለማው ስልጣን (ሰይጣን) ቁጥጥር ውስጥ ከሆነ (ቆላ 1፡13) እንደ ምሳሌ አድርገን ብንወስድ ሙስሊሞች ለክፍለ ዘመናት ተነግሮ የማያልቅን መከራ በማኅበረሰብ ላይ አድርገዋል፡፡ ይሄ ደግሞ መታየት ያለበት ከፖለቲካና ከማኅበራዊ አንፃር ብቻ አይደለም በመንፈሳዊም ጎኑም ጭምር ሊታይ ይገባል፡፡ በመንፈሳዊው ዓለም ያለው አምባገነናዊ የክፉ አሰራር በሰዎች ክልልም እንደሚሰራ የሚያመለክት ነው፡፡

ማንኛውም ሰው ሊገነዘበው የሚገባው ነገር ቢኖር የተቋም መልክ ያላት ቤተክርስቲያን (በክርስቶስ ትምህርት የማትኖረዋ ቤተ ክርስቲያን) ከክፉ ኃይላት ተፅዕኖ ራሷን የመከላከል ብቃት ያላት አለመሆኗን ነው፡፡ ፀረ-ሴማዊነት፣ ዘረኝነት እና ሴቶችን ማግለል በውስጧ ከታዩ የማግለል ምልክቶች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡

# የክፋትን ኃይል ማሸነፍ

ለክርስቲያኖች ጎጂ ውጤት ካለው፣ መንፈሳዊ ተፅዕኖ ከሚያመጣው የዲህሚ ሕግ ነፃ መውጣት፣ የሰይጣንን ኃይል መቋቋም እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በዚህ ዓለም ላይ ያለውን ተቀባይነት ማጣትን በመንፈሳዊ ኃይል በዋናነት የሚያቀነባብረው ሰይጣን ነው፡፡

እንደ ወንጌልና የአዲስ ኪዳን መልዕክቶች ከሆነ ሰይጣን ዓለምን የሚገዛበት ኃይል አለው፡፡ እርሱ “የዚህ ዓለም ንጉስ” ነው (ዮሐ 12፡31)፡፡ “የዚህ ዓለም አምላክ” (2ቆሮ 4፡4) እንደዚሁም “የአየር አለቃ መንፈስ” (ኤፌ 2፡2) መንግስቱ ደግሞ “የጨለማ ሥልጣን” ይሄ ደግሞ “በማይታዘዙት ላይ የሚሰራ መንፈስ” ነው፡፡

ኢየሱስ ለጳውሎስ በራዕይ በተገለጠለት ጊዜና ወደ አሕዛብ እንዲሄድ በጠራው ጊዜ ሐዋርያው የተነገረው ነገር ቢኖር ሰዎችን “ከጨለማ ወደ ብርሀን ከ ሰይጣን ኃይል ወደ እግዚአብሔር” ይመልሳል ተብሎ ነው፡፡ (ሐዋ 26፡ 18) ይሄ ሐሳብ የሚያመለክተው ሰዎች በክርስቶስ አምነው ከመዳነቸው በፊት በሰይጣን ቁጥጥር ውስጥ ነበሩ፡፡ ነገር ግን በክርስቶስ በኩል በመዋጀት ከጨላማ ኃይል ወደ እግዚአብሔር መንግስት ተሻግረዋል፡፡

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ መንፈሳዊ ጦርነት በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል ይቀጥላል፡፡ ሰይጣን ደግሞ ዓለምን ለአመጽ የዳረገ ነው፡፡ (ማር 1፡15 ሉቃ 10፡18፤ ኤፌ 6፡12) ይሄ በሁለት መንግስታት መካከል ያለ ግጭት ነው፡፡ ውግያው ደግሞ የተገለጸና ሊሰወር የማይችል ነው፡፡ ክርስቲያኖች ደግሞ ወደየትኛው ካምፕ መቀላቀል እንዳለባቸው መወሰን አለባቸው፡፡ ጦርነቱ ደግሞ አንድ

ጊዜ በመስቀል አማካይነት አሸናፊውን ጎራ ለይቷል፡፡ ስለሆነም የፍጻሜው አሸናፊ ያለምንም ጥርጥር ክርስቶስ ሆኗል፡፡

ክርስቲያኖች እንደ ክርስቶስ ወኪል፣ እንደ ክርስቶስ ተወካዮች በየእለቱ ከጨለማ ኃይላት ጋር ሁልጊዜ ጦርነት ይገጥማሉ፡፡ የክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ የነፍሳችን ባለስልጣን በጨላማ ኃይላት ላይ ኃይለኞች ሆነን እንድንገለጥ መሠረት ሆኖናል፡፡ የዚህ መንፈሳዊ ውግያ ግዛት ደግሞ የሚያጠቃልለው ሕዝብን፣ ኅብረተሰብን፣ ማኅበረሰብናና ብሔርን ነው፡፡

የተቋም መልክ ያላት ቤተክርስቲያን በጦር ሜዳ ትመሰላለች፤ ያላት ኃይሏ ደግሞ መፈንዳት የሚጀምረው በክፉ ዓላማ ላይ ነው፡፡

ለማንኛውም እዚህ ጋር ትኩረት መስጠት የምንፈልገው ለእስልምና ነው፡፡ ቁልፉ ነገር ደግሞ መገዳደርን የሚጠይቀው መንፈሳዊና ግዛታዊ አካሄድ የሆነውን የዲህሚ ሕግና የሸሀዳ ትንታኔ ነው፡፡ በሌላው መልኩ ሙስሊሞችን የበላይና የተማሩ አድርጎ በማቅረብ ሌሎቹን ባርያ በማድረግ መጨቆን፣ በሌላ መልኩ ክርስቲያኖችንም ባርያ ማድረግና ሌሎች ሙስሊሞች ያልሆኑት ሕዝቦች ዝቅ ብለው እንዲገዙ ማድረግ፤ የሀሰት ምስጋና በመስጠት ዝም ብለው እንዲገዙ በማድረግ በሞት እርግማን ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋሉ፡፡ (ኤፌ 6፡11-17)

ሐዋርያው ጳውሎስ ስላገኘነው ድል አስረግጦ ሲናገር የዚህ ዓለም ገዢ የሆኑት የጨለማ ኃይላት ትጥቃቸው ተፈትቷል፣ አቅማቸው ተወስዷል፡፡ ተሸናፊዎችም ሆነዋል፡፡ ይሄ ደግሞ ሊሆን የቻለው በመስቀሉ በተሰራው የኃጢአት ይቅርታ ነው፡፡

እናንተም በበደላችሁና ሥጋችሁን ባለ መገረዝ ሙታን በሆናችሁ ጊዜ ከእርሱ ጋር ሕይወትን ሰጣችሁ፡፡ በደላችሁንም ሁሉ ይቅር አላችሁ፡፡ በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽህፈት ደመሰሰው፡፡ እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል፡፡ አለቅነትና ሥልጣናትን ገፎ ድል በመንሳት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው፡፡ (ቆላ 2፡13-15)

ዲህማና ሽሀዳ የተጻፉ መለያዎች ሆነው የሰው ልጆችን ስብእናን በመቃወምም ጭምር ያገለግላሉ፡፡ የመንፈሳዊው ኃይል መለያዎች የሆኑት ሰዎችን የሚቀወሙትና የሚጨቁኑት ዲህማና ሽሀዳ በመስቀሉ ኃይል በሚስማር ሊጠረቅባቸው ችሏል፡፡ ይሄ ደግሞ በአደባባይ የሚያሳዩትና እን ሦስተኛው ምርጫ ብዬ ያልኩትንም ጭምር የሚያጠቃልል ነው፡፡

የዲህማ ሕግ ቁልፍ የሆነው አካሄዱ ኢስላም ያልሆኑትን በዝምታ ማስጨነቅ ላይ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ነገር ግን በመስቀሉ በመጠረቁ ትጥቁ ተገፎ ጥርስ እንደሌለው አንበሳ ሆኗል፡፡ ከዚህም የተነሳ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ኃይላትና ሥልጣናት ላይ ድልን እንደተቀዳጁ ሁሉ በዲህሚ ህግ ላይም አሸናፊዎች ናቸው፡፡

## ሕጋዊ መብቶች

መንፈሳዊ ነፃነትን የምንቀዳጅበት አንደኛው ደረጃ ሰይጣን በኛ ላይ ያወጀብንን አዋጅ በመንፈሳዊ ሥልጣን በመቃወም ነው፡፡ መንፈሳዊ መሰጠት በቀደመው ትውልድ ሲኖር፣ ደግሞም በክርስቶስ የተሰራውን ሥራ በእምነት መቀበል ሲቻል ቀጣዩ ተውልድ በነፃነት እንዲመላለስ ሁኔታዎች ይመቻቹለታል፡፡ እውነቱን በምንመለከትበት ጊዜ ሰይጣን በክርስቲያኖች ላይ ቀጣይነት ያለው

*መንፈሳዊ ውግያ ለመክፈት ኪዳን እንደገባ ከስራው መረዳት እንችላለን ፡፡*

**ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚያስተምረው ከሆነ ቁጣን ደብቆ በመያዝና በማሰላሰል ለዲያቢሎስ ዕድል ፈንታን መስጠት ይቻላል፡፡**

> **ተቆጡ ኃጢአትንም አታድርጉ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ ለዲያቢሎስም ፈንታ አትስጡት** (ኤፌ 4፡ 26)

**እዚህ ላይ "ፈንታ" የሚለው ቃል የተተረጎመው *ቶፖስ* ከሚለው የግሪክ ቃል ነው፡፡ ትርጓሜው ደግሞ በአንድ አካባቢ መሆን ወይንም የተያዘ ቦታ ማለት ነው፡፡ "ቦታ መስጠት" የሚለው ሐሳብ ደግሞ "እድል ፈንታን" አሳልፎ መስጠት እንደ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ እያለ ያለው አንድ ሰው ለኃጢአቱ ይቅርታን ከመጠየቅ ይልቅ በመቆጣት ሽምቀቆ ውስጥ ራሱን ቢያስገባ ለክፉ ሐሳብ ዓላማ መጠቀምያ ለመሆን መሠረትን ያመቻቻል ማለት ነው፡፡**

**በዮሐ** 14 30 **ኢየሱስ ክፉው በእርሱ ላይ እድል ፈንታ እንደሌለው መናገሩ ትክክለኛ መሠረት ነበረው፡፡**

> **ከእንግዲህ ወዲህ ከእናንተ ጋር ብዙ አልናገርም የዚህ ዓለም ገዥ ይመጣልና፤ በእኔ ላይም አንዳች የለውም፤ ነገር ግን አብን እንድወድ ዓለም ሊያውቅ አብም እንዳዘዘኝ እንዲሁ አደርጋለሁ፡፡ ተነሡ፤ ከዚህ እንሂድ፡፡** (ዮሐ 14፡ 30-31)

**ሊቀ ጳጳስ ጄ. ኤች በማብራርያ መጽሐፋቸው እንዳስቀመጡት ኢየሱስ እየተናገረ ያለው "ብታሰር እንኳን ሰይጣን በማንነቴ ላይ ምንም ማድረግ አይችልም" የሚል *ነው፡፡* ***(A critical and Exegetical*

*Commentary on the Gospel According to John, Vol 2, P. 256).* ይሄኛው ፈሊጣዊ አነጋገር በእርግጥ ተገቢ መሆኑ በካርሰንም ማብራርያ ተሰጥቶበታል፡

> በእኔ ላይ አንዳች የለውም የሚለው አባባል "በእኔ ላይ ምንም ማድረግ አይችልም" የእብራውያንን አነጋገር በምንመለከትበት ጊዜ "በእኔ ላይ ምንም መናገር አይችልም" 'ሊነቅፍብኝ የሚችለው ምንም ነገር የለውም' የሚል ነው፡፡ ዲያቢሎስ በኢየሱስ ላይ አንዳች ነገር ሊያደርግ የሚችለው እሱን ሊከስበት የሚችል ነገር ማግኘት ሲችል ብቻ ነው፡፡ (The Gospel According to John PP.508-9)

ምንም ዓይነት ኃጢአት ያልተገኘበት ኢየሱስ አባቴ ያዘዘኝን አደርጋለሁ ብሏል፡፡ ለዚህም ነው ሰይጣን በሱ ላይ አንዳች ለማድረግ ምንም ሕጋዊ መሠረት ሊያገኝ ያልቻለው፡፡ ይሄ ደግሞ የመስቀሉን ሚስጥር እንድንረዳ ትልቅ አቅም ይሆነናል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የኢየሱስ ሞት ሰይጣን ሕጋዊ ቀጪ እንዳይሆን መሠረቱ ሁሉ እንዲፈራርስበት አድርጓልና፡፡

ጌታ የሆነው መሲህ መሞቱ በሌሎች ምትክ የተደረገ ንጹህ መስዋእት ነው፡፡ ሰይጣን በኢየሱስ ላይ ያደረገው ቅጣት ተደርጎም መቆጠር የለበትም፡፡ ኢየሱስ የሚነቀፍበት ነገር ከሰይጣን ዘንድ ተገኝቶበት ቢኖር ኖሮ የተሰቀለው ስለ እርሱ ኃጢአት በሆነ ነበር ነገር ግን ንጹህ ከመሆኑ የተነሳ የዓለምን ሁሉ ኃጢአት ለማስወገድ መስዋዕት ሆኗል፡፡

## የመግቢያ ቀዳዳዎችን መድፈን

ስለ መንፈሳዊ ነፃነት በምንነጋገርበት ጊዜ አስፈላጊና ስሜትን የሚነካ ጉዳይ ስለሆነ ስልታዊ በሆነ መንገድ ሊታይ ይገባዋል፡፡ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ማንኛውንም ለዲያቢሎስ እድልፈንታ የሚሰጥን ነገር ማስወገድና በሮችን ሁሉ መዝጋት እጅግ ወሳኝ ነገር ነው፡፡ ወደ በሩ መቅረብ ማለት ደግሞ አንድ ሰው ለሰራው በደሉና ለተናገራቸው ከንቱ ንግግሮች ንስሀ በመግባት ሰይጣን በሕይወታቸው የፈቀደውን እንዲያደርግ መብት ከሰጡት ማንኛውም ነገር መላቀቅን የሚያሳይ ነው፡፡

መስቀሉ ለማንኛውም መንፈሳዊ ጥያቄ መፍትሔ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው ክርስቶስን እንደ አዳኝ አድርጎ በመቀበል፤ በግሉ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ማግኘት ይችላል፡፡ ከክርስቶስ ጋር በመቀበር ከእርሱ ጋር የታወቀ ይሆናል፡፡ ከዚህም የተነሳ የሰይጣን ሕጋዊ የሆነ ክስ ማቅረብ አይችልም፡፡ይሄ ማለት ደግሞ በክርስቶስ ከመሆኑ የተነሳ አንዳች ነቀፌታ ሊያገኝበት አይችልም፡፡ ነቀፌታው በመስቀሉ ተወስዷልና፡፡

አንድ ሰው የማያቋርጥ የመዋሸት ሕይወት በሚኖረው ጊዜ ሰውየው መዋሸቱ በእግዚእብሔር ፊት ስህተት እንደ ሆነ ያውቃል፡፡ ስለዚህም ይሄንን በመናዘዝ፣ ንስሃ በመግባት በክርስቶስ በኩል የኃጢአትን ይቅርታ ያገኛል፡፡

## ትውልድ ተሻጋሪ መንገድ

በአንዳንድ ቤተሰቦች ከሚያነሷቸው ርዕሰ ጉዳዮች አንዱ አንድ ስህተት ከትውልድ ወደ ትውልድ በመተላለፍ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል

የሚል እምነት ነው፡፡ አብዛኞቹ የሚስማሙበት ነገር ቢኖር ከዘር የሚወረስ ወይንም ከማኅበረሰቡ የሚወረስ ነገር በመልካምም ሆነ በመጥፎ ሁኔታ በቤተሰብ ላይ ተፅዕኖ ሊያመጣ ይችላል የሚል ነው፡፡ መጠየቅ የሚገባው ጥያቄ ግን በእርግጥም ቤተሰብ መንፈሳዊ ነገርን ለትውልዱ ማስተላለፍ ይችላልን? የሚል ነው፡፡ ማስተላለፍ የሚችሉ ይመስላል  አንዳንድ ተፅዕኖዎች ደግሞ ከትውልድ ትውልድ የሚሸጋገሩ ናቸው፡፡ መንፈሳዊ ተፅዕኖ እጅግ ብዙ ትውልድን የመጉዳት አቅም አለው፡፡

አንዳንድ ክርስቲያኖች ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ መንፈሳዊ ቀንበር አለ በሚለው አስተሳሰብ አይስማሙም፡፡ ሊቀበሉትም አይፈልጉም፡፡ ምክንያታዊም አይደለም ሲሉ ይሞግታሉ፡፡ ምናልባት በቤተሰብ ላይ ያለ ባህሪ ወደ ልጆች ሊተላለፍ ይችላል ብለው ግን ያምናሉ፡፡ እንደ ምሳሌ አድርገን ብንወስድ ወላጆች ውሸታም ከሆኑ ልጆች ይሄንን እኩይ ባህሪ መቅዳት ይችላሉ፡፡ከዚህም የተነሳ ውሸታም መሆንን ይማራሉ፡፡ ወይንም እናት ልጇን የምትጋገም ከሆነ ልጁ ማንነቱን በተመለከተ ደካማ አመለካከት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

አጠቃላዩን የመጽሐፍ ቅዱስ ንጽረተ ዓለም ከቃልኪዳን፣ እርግማንና በረከት አንጻር በምንመለከትበት ጊዜ በእነዚህ አመለካከቶች የተቃኘ ነው፡፡ የሙሴ መጽሐፍ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ስለገባው ኪዳን ይናገራል፡፡ በነሱና በትውልዳቸው መካከል ሊተላለፍ ስላለው በረከትና መርገም የሚናገር ነው፡፡ በረከቱም ለሺህ ትውልድ ሲሆን እርግማኑ ደግሞ ለሦስትና አራት ትውልድ ነው፡፡ (ዘጸ 20፡5፤ 34፡7)

በተጨማሪም ትውልዱ ከአባቶቻቸው በደል ነፃ ይሆን ዘንድ የእነሱንና የአባቶቻቸውን በደል የግድ መናዘዝ አለባቸው፡፡ (ዘሌ 26፡40)

ስለዚህም እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል፡፡ "ለአባቶቻቸው የገባውን ኪዳን ያስታውሳል ፡፡ ምድራቸውንም ይፈውሳል"፡፡

# ሸሀዳን ለመተው የሚደረግ ምስክርነት

## *"እስልምናን ካደው!"*

ክርስትናን ያጥላላ የነበረ የቀድሞ ሙስሊም ምስክርነት

"ተወልጄ ያደግኩት በምዕራቡ ዓለም ከሚኖሩ የሙስሊም ቤተሰብ ነው፡፡ መስኪዶች በመሄድ ኃይማኖታዊ ሥርአት ከመፈጸሜም በተጨማሪ ጸሎትን በአረብኛ እንድንጸልይ ትምህርት ይሰጠን ነበር፡፡ በእርግጥ ይሄ ነው የሚባል አክራሪ ኃይማኖተኛም አልነበርኩም፡፡  ነገር ግን ወደ ዩኒቨርሲቲ ከገባሁ በኋላ ግን ባለጠበቅኩት ሁኔታ ነገሮች መቀየር ጀመሩ፡፡ በዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ  ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ማን እንደሆነ እንደሚገባ ተረዳሁ፡፡ በእርሱም አምኜ ነፍሴን አዳናት፡፡

በትምህርት ላይም ሳለሁ በክርስቲያኖች ቡድን ውስጥ ታቅፌ መንፈሳዊ መርሐ ግብሮችን መሳተፍ ጀመርኩ፡፡ በየሳምንቱ የተለያዩ ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ያካፍሉናል፡፡ በክርስቶስ አምኜ ዓመት እንኳን ሳይሞላኝ መልዕክት እንዳካፍል ተጠየቅኩ፡፡ መልዕክት በማካፍልበት አንድ ምሽት ላይ ለመጸለይ በዩኒቨርሲቲው አንደኛው ቤተመጻሕፍት ለመጸለይ ሄድኩ፡፡ መልዕክቴ

ደግሞ "ኢየሱስ ለኔ ሞቷል እኔስ ለኢየሱስ እሞታለሁ?" የሚል ነው፡፡

ታድያ መጸለይ በጀመርኩ ጊዜ አንድ ያልተጠበቀ ነገር ሆነ በጉሮሮዬ አካባቢ የአየር እጥረት እንዳጋጠመው ዓይነት ስሜት ተሰማኝ ፡፡ የሆነ ለየት ያለ ነገር ሁለንተናዬን ሲቆጣጠር ይታወቀኛል ፡፡ ከዚያም አንድ ድምጽ "እስልምናን ካድ እስልምናን ካድ" ብሎ ሲናገረኝ ሰማሁ፡፡ ጌታ እንደሆነ አመንኩ፡፡ እኔም "ጌታ ሆይ እኔ እኮ በእርግጥም ኢስላም አይደለሁም በልምምዱ ውስጥም የለሁም" አልኩ፡፡

ቢሆንም በአየሩ ላይ የከበደ ነገር አሁንም አለ፡፡ "እስልምናን ክጄአለሁ" ይሄ ሁሉ ነገር የሆነው በዝግታ መንፈስ ውስጥ ሆኜ በቤተመጻሕፍት ውስጥ ሆኜ ነበር፡፡ ወዲያውኑ ጉሮሮዬ ውሰጥ የነበረው ነገር ለቀቀኝ፡፡ ለየት ያለ የእረፍት ስሜት ተሰማኝ፡፡ ወደ ጸሎትና ዝግጅት ከሄድኩ በኋላ ወደ ስብሰባችን ስፍራ አመራሁ፡፡ በስብሰባችን ጌታ በኃይል ተገለጠ አስታውሳለሁ ተማሪዎች በጉልበታቸው ተንበርክከው እያለቀሱ ራሳቸውን ለጌታ ይሰጡ ነበር፡፡

## አዲስ አማኞችን ደቀ መዛሙርት ማድረግ

በሰሜን አሜሪካ የሚገኝ አንድ አገልግሎት ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉትን ከእስልምና ወደ ክርስትና ለተለወጡ ሰዎች የማይቆም ስልጠና ይሰጣል፡፡ የስልጠናው

አስተባባሪ አንድ የተረዳው ነገር ቢኖር ተሳታፊዎቹ ጽኑ የሆኑ ደቀመዛሙርት የመሆን ችግር ነበረባቸው፡፡

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሰው ሸሀዳን መተው አስመልክቶ ስለሚናገረው ጸሎት እውቀቱ አላቸው፡፡ የስልጠናው ተሳታፊዎች ሁሉ በአንድ ላይ በመሰብሰብ እስልምናን ሙሉ በሙሉ ከሕይወታቸው እንዲያስወጡ ጸልየዋል፡፡ የተሳታፊዎቹ ምላሽ የሚያመለክተውም ታላቅ ዕረፊትና ደስታ እንደተሰማቸው ነው፡፡ "እልምናን ሙሉ በሙሉ ማስወጣት እንዳለብን ለምንድን ነው ማንም ግልጽ አድርጎ የማይነግረን ይሄንን ደግሞ ከረዥም ጊዜ ማድረግ ነበረብን" ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡ እስልምናን በአደባባይ መካድ የስልጠናው አስፈላጊ ክፍል ነው፡፡

# ዲህማን በመካድ ስለመጣ ለውጥ የተሰጠ ምስክርነት

## *ትውልድ ተሻጋሪ ፍርሃት*

በዘመኗ ሁሉ በታላቅ ፍርሃት ውስጥ ለነበረች ሴት የመጸለይ እድል ገጥሞኝ ነበር፡፡ ዘሮቿ በደማስቆ ሶርያ ከአንድ መቶ ዓመት በፊት በዲህማ ተፅዕኖ ስር ሆነው ይኖሩ ነበር፡፡ የታወቀው ክርስቲያኖችን በጅምላ እንዲጨፈጨፉ በተደረገበት በ1860 ዓ.ም ማለት ነው፡፡ በዲህማ ተፅዕኖ ስር ላሉት አሰራሩን በመካድ በምንጸልይ ጊዜ የፍርኃት መንፈስ ተሰበረ፡፡ ከዚህም የተነሳ ለዘመናት ከእርስዋ ጋርየነበረው ፍርሃት ተነስቶ እረፍትን አገኘች፡፡

## ከዘር ማጥፋት ውርስ ነፃ መውጣት

ከአርሜንያን ቤተሰቦች የተወለደ ሰው ዘሮቹ የግሪክ ስም ስነበራቸው ብቻ በጅምላ ግድያ ውስጥ ማለፍ ግድ ሆኖባቸዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ የተረፉት ቅሬታዎች በሰምሪኒያ አድርገው ወደ ግብጽ መጥተዋል፡፡ ከአንድ ክፍለዘመን በኋላ ይሄ ልጅ በየእለቱ በእንደዚህ ዓይነቱ ፍርሃት ውስጥ ያልፍ ነበር፡፡ የቤቱን በሮችን መስኮቶች መዝጋቱን እርግጠኛ እስካልሆነ ድረስ ከጭንቀት ነፃ አይሆንም ነበር፡፡ እንደዛም ሆኖ ከትውልድ ትውልድ እተላለፈ የመጣውን የፍርሃት መንፈስ በካደና አብረን በጸለይን ጊዜ ለየት ያለ ነፃ መውጣትና መንፈሳዊ ፈውስ በሕይወቱ ተከናወነ፡፡

## ከፍርሃት ወደ ድፍረት - ወንጌልን የማድረስ ሥልጠና

አረብኛ ተናጋሪ የሆኑ ክርስቲያኖች በቡድን ሆነው ይጸልዩ ነበር፡፡ የሚጸልዩትም ወደ አውሮፓ ሀገራት ቱሪስት ሆነው ለጉብኝት ለሚመጡት ሙስሊሞች ወንጌልን ለመስበክ ነው፡፡ የቱንም ያህል የወንጌል ቡድኑ ያለው ነፃነት ባለበት ምድርም ቢሆን እምነታቸውን በድፍረት ለመናገር ፈርተው ነበር፤ ከዚህም የተነሳ ከፍርሃት ቀንበር ወጥተው ውስጣቸው እንዲፈወስ ግልጽ ውይይት ማድረግ ነበረባቸው፡፡ ከዚህም በኋላ በመካከላቸው የነበረ አንድ መሪ ገላጻውን እንዲህ ሲል አሰማ "በውስጣችሁ ታላቅ ፍርሃት ሊፈጠር የቻለው በናንተ ፈንታ ተገብቶ የነበረ ኪዳን ስላለ ነው"፡፡ በንግግሩ ላይ ከተወያዩ በኋላ ከዚህ በፊት በማስገደድ ተገብቶ የነበረውን ቃል ኪዳን አስመልክቶ ብርቱ ጸሎት በማድረግና ሥራውን በመካድ ነፃ መሆን ተችሏል፡፡

ውጤቶቹ እጅግ አስገራሚ ነበሩ ፡፡ ያለምንም ልዩነት የዚህ ጸሎት ተሳታፊዎች ሐሳባቸውን በኃይል ለመግለጽ እንደሞከሩት በስልጠና ውሥጥ እንደዚህ ዓይነቱ ርዕሰ ጉዳይ የግድ መካተት አለበት፡፡ ለጥልቅ በረከትና እውነተኛ ነፃነት በተለይም ደግሞ እያንዳንዱ ሰው በዲህማ የተገባን ቃልኪዳን በመካድ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ያገኙትን ኪዳን አውጀዋል፡፡ ከዚህ ተፅዕኖ ነፃነት ስላለ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡ በደሙ ኃይል በጸሎት ነፃ መውጣት ችለዋልና፡፡

# የኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ተከታይ የሆነች ሴት ሙስሊሞችን በወንጌል ለመድረስ እንዴት ኃይል እንዳገኘች የሰጠችው ምስክርነት

በሙስሊም ሀገር ለአራት ዓመት ተምሬ በሕግ የመጀመርያ ዲግሪዬን ስሰራ ሼሪያን የትምህርቱ እንደዋና ክፍል ተቆጥሮ የማጥናት እድል አግኝቼ ነበር፡፡ በሼሪያ ሕግ መሰረት ክርስቲያኖችን እንዴት ዝቅ ማድረግ እንደሚቻል በጥልቀት አጥንቻለሁ፡፡ የዲህማ ሕግንም ጭምር ማለት ነው፡፡ ነገር ግን አንድ ነገር እንደዚህ ዓይነቱ አስተምህሮ በኔ ባህሪ ላይ የሚያመጣውን ተፅዕኖ በተመለከተ በነበረኝ መረዳት ላይ ያጋጠመኝ እንቅፋት ነበር፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን የምወድ የተሰጠሁ ክርስቲያን ነበርኩኝ፡፡ ነገር ግን ስሜቶታቸውን እንዳልጎዳ በማሰብ ጌታዬን በሙስሊም ወዳጆቼ ፊት የመመስከር አቅም አጣሁ፡፡ የዲህማ አካሄድን አስመልክቶ የተዘጋጀን ጥናት በተካፈልኩ ጊዜ ያለሁበት መንፈሳዊ ሁኔታ ወደ ብርሃን መውጣት ጀመረ፡፡ ከነፍሴ ውስጥም ትልቅ ተስፋ መቁረጥ ፈንቅሎ ወጣ፡፡ ያባቶቼን ምድር ድል ባደረጉባቸው ቦታዎች ላይ ሙስሊሞች የበላይ ሆነው መግዛታቸውን በደስተ የተቀበልኩባቸውንና እንዲያውም ስለ ትክክለኛነቱ የተሟገትኩባቸውን ጊዜያት አስታውሳለሁ፡፡ ለረዥም

አመታት የዲሚን ሕግ ተቀብዬ ተረግጬ የኖርኩ መሆኔን ልክድ አልችልም፡፡ የጸሎትን ኃይል ተመልክቻለሁ፡፡ በክርስቶስ ያገኘሁትንም አርነት መለማመድ ችያለሁ፡፡

በተመሳሳይ ምሽት ተመልሼ ወደ ቤቴ ሄድኩና የቅርብ ወዳጄ የሆነችን አንዲት ሙስሊም ጠራሁ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚወዳትና በመስቀል ላይ እንደሞተላት ነገርኳት፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለሙስሊሞች የምሰጠው አገልግሎት እጅግ ውጤታማ ሆነ፡፡ ብዙዎቹ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታና አዳኝ ሲያውጁት ማየት ችያለሁ፡፡

# የደም ቃልኪዳንና ልምምዱን በይፋ መካድ

ከላይ ለመመልከት እንደሞከርነው ሌላው ቁልፍ የሆነ ፅንሰ ሐሳብ ቢኖር ዲህማ ማለት 'የደም ቃልኪዳን' መሆኑን ነው፡፡ በእብራውያን ቅዱሳን መጻሕፍት ደረጃውን የጠበቀ ቃልኪዳን የሚገባውና አንድ ሰው በዚህ ቃልኪዳን የሚታሰረው የደም መስዋዕት በማቅረብ ነው፡፡ በዘፍ 15 ላይ እግዚአብሔር በጣም ታዋቂ የሆነውን ኪዳን ለአብርሃም ሲገባ መስዋእት በመጠየቅ ነው፡፡ አብርሃም እንስሳውን አዘጋጀ፡፡ እንስሳውን አረደና የሥጋውን ብልቶች ቆራርጦ መሬት ላይ አስቀመጠ፡፡ ከዚያም የእግዚአብሔርን መገኘትና ተሳታፊ መሆን የሚያመለክት የሚጨስ ነበልባል በሥጋው መካከል አለፈ፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ልምምድ እርግማንን ይቀሰቅሳል፡፡ የዚህ ቃል ኪዳን መልዕክት በግልፅ ቢነገርም ባይነገርም ባለ ቃልኪዳኑ የሚናገረው ንግግር፡ 'ቃል ኪዳኑን ካፈረስኩ እኔም እንደ እንስሳው ይሁንብኝ' ማለት ነው፡፡ ይሄ ማለት ደግሞ መገደልና መቆራረጥ ማለት ነው፡፡

ይህ ነገር እግዚአብሔር በነብዩ ኤርሚያስ በኩል በተናገረው ነገር ውስጥ ተንጸባርቋል፡

> **ቃል ኪዳኔንም የተላለፉትን ሰዎች፥ እንቦሳውንም ቈርጠው በቍራጩ መካከል ባለፉ ጊዜ በፊቴ ያደረጉትን የቃል ኪዳንን ቃል ያልፈጸሙትን፥** የይሁዳን አለቆችና የኢየሩሳሌምን አለቆች ጃንደረቦችን ካህናትንም በእንቦሳም ቍራጭ መካከል ያለፉትን የአገሩን ሕዝብ ሁሉ፥ ለጠላቶቻቸው እጅ ነፍሳቸውንም ለሚሹአት እጅ አሳልፌ እሰጣለሁ ሬሳቸውም ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት መብል ይሆናል። ኤር 34፡18-20

ጠንቋዮች የሚለማመዷቸው በባዕድ አምልኮ ውስጥ የሚገኙ ልምምዶች የደም መስዋዕትን በመጠቀም ሰዎችን በቃል ኪዳን የማሰር ተግባርን ሊያካትት ይችላል፡፡ በሌሎች የባዕድ አምልኮ ቡድኖች ውስጥ ደግሞ ሞትን በራስ ላይ መጥራት፣ ለምሳሌ ያህል ራስን በመርገም፣ የሞት ምልክት የሆውን ሽምቀቆ አንገት ላይ በማሰር፣ ሞትን የሚያመለክቱ ነገሮችን በማድረግ ለምሳሌ ያህል በሬሳ ሳጥን ውስጥ በመግባት፣ ጦርን ልብ ላይ በማድረግ ቃል ኪዳን ሊፈጸም ይችላል፡፡ ባሕላዊ በሆነው የእስልምና የጂዝያ አከፋፈል ጊዜ የሚደረገው ሙስሊም ያልሆነውን ሰው አንገት የመቅላት ምልክት የደም መስዋዕት ምልክት ነው፡፡ ይህ ስርኣት ዲህሚው በራሱና በሕብረተሰቡ ላይ የሚያመጣውን አንገት መቀላት የሚያመለክት ነው፡፡ እርሱም በመንፈሳዊው ዓለም እንዲህ እንደማለት ነው፡ “የዚህን ውል አንዱንም አንቀጽ ብተላለፍ አንገታችን እንዲህ ይቀላ”፡፡

ግልፅ እና ስውር የሆኑ የደም ቃልኪዳን እርግማኖች አደገኛ ናቸው ምክንያቱም መንፈሳዊ ባርነትን ሊያስከትሉ ይችላሉና፡፡ በመጀመርያ ደረጃ ሰውየውን በውሉ የታሰረ እንዲሆን ያደርጉታል በመቀጠልም በውሉ ላይ በሰፈረው እርግማን መሰረት ሰውየው በአዕምሮም ሆነ በመንፈስ የተጨቆነ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

የነዚህ እስራቶች መገለጫዎች በጣም አስደናቂ ናቸው፡፡ አንዲት የዲህሚ ታሪክ የነበራት ሴት የሞቱ ዘመዶችዋ ወደ ሙታን ምድር ትመጣ ዘንድ በህልሟ ያባርሯት ነበር፡፡ ያለ ምንም ምክንያት ደግሞ ራሷን ለመግደል ትፈልግ ነበር፡፡ እየጸለይንና እያወራን በመጣን ቁጥር ቤተሰቦችዋም በተመሳሳይ ሁኔታ በቅዠት ይሰቃዩ እንደነበር ተረዳን፡፡ ዘሮችዋ ለረጅም ዘመናት በዲህማ ውስጥ ይኖሩ ስለነበር የሞት ፍርሃት እያስጨነቃት መሆኑን ተረዳሁ፡፡ ዘሮችዋ በዓመታዊ የጂዝያ ክፍያ ስርኣት ውስጥ በመሳተፋቸው ምክንያት የመጣውን የሞትን ኃይል እየገሰፅን እና እያንዳንዱን የሞት እርግማን እየሰበርን መጸለይ ጀመርን፡፡ ከዚህ ጸሎት በኋላ ያቺ ሴት ከቅዠት እና ከሞት ፍርሃት ነፃ ወጣች፡፡

# በእስራት ውስጥ ያሉትን የመፍታት ስልጣን

አርነት መውጣትን የሚከለክል ተቃውሞ በሚመጣበት ጊዜ ሊወሰድ የሚገባው እርምጃ ቢኖር እግዚአብሔራዊ ያልሆነን ማንኛውንም አካሄድ ለመቃወም ፈጣን እርምጃ መውሰድ ነው፡፡ ብሉይ ኪዳንን በምንመለከትበት ጊዜ ጣዖታትና የሚመለኩባቸው ስፍራዎች ሙሉ በሙሉ ወድመው ነበር፡፡ ይሄ ደግሞ የሚያሳየው ጣዖታት ምንያህል በመንፈሳዊው ስፍራ ግዛት እንደነበራቸው ነው፡፡ (ዘዳ 12፡1-3) ከፍተኛ ቦታዎች፣ የጣዖት ልምምድ የሚደረግባቸው ስፍራዎች፣

ለጣዖት የሚሰዋባቸው እቃዎች እና መስዋእታቸው ሙሉ በሙሉ ጣዖታቱንም ጨምሮ እንዲወገዱ ተደርጓል፡፡

አንድን ስምምነት ለማድረግ በሚታሰብበት ጊዜ እያንዳንዱ ነገር በጥንቃቄ መታየት አለበት፡፡ ሊታይ የሚገባው ደግሞ ሁኔታውና ሊያስከትል የሚችለው ውጤት መሆን አለበት፡፡ ይሄ ደግሞ የሚኖረው ጠቀሜታ ምንድን ነው ካልን አንድን ኃጢአት በደንብ አውቆ ለመናዘዝና ንስሃ ለመግባት ስለሚጠቅም ነው፡፡ መንፈሳዊ ነፃነትን ለማወጅም ይጠቅማል፡፡ ይሄ ደግሞ ማንም በየትኛውም ይቅርታ በሚያስፈልገው የሕይወቱ ክፍል የእግዚአብሔር የእውነት ብርሃን እንዲያንጸባርቅበት ያደርጋል፡፡

እግዚአብሔራዊ ያልሆኑ ቃልኪዳኖች በሚደረጉ ጊዜ ተመሳሳይ የሆነ መርህ መተግበር አለበት፡፡ ለምሳሌ ያህል አንድ ሰው ዝም ለማለት የደም ቃል ኪዳን ቢገባ ይህንን የደም ቃል ኪዳን ለመስበር ንስሃ መግባት እና የዚህን ቃል ኪዳን ተሳትፎ መካድ ያስፈልገዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ "እኔ ይህንንና ያንን ጉዳይ በሕይወት ዘመኔ ሁሉ ይቅር አልልም" በማለት ከመናገራቸው የተነሳ ይቅርታ ካለማደረግ መንፈስ ጋር የሚታገሉ ሰዎች ይህንን መሃላ በመካድ እና በእግዚአብሔር ፊት ንስሃ በመግባት እርግማኑን ሊሰብሩት ይገባል፡፡ ዖታዊ ጥቃት ደርሶባቸው በሞት ስለተስፈራሩ የደረሰባቸውን በደል ላለመናገር ቃል የገቡ ሰዎች "የደረሰብኝን ነገር ላለመናገር የገባሁትን የዝምታ ቃል ክጄ ስለመብቴ እሟገታለሁ" በማለት መሃላውን መስበር ያስፈልጋቸዋል፡፡ ከዲህማዊነት መንፈስ ነፃ ለመውጣት የመፈልግ ሰው የጂዝን ክፍያ እና አንገት ላይ የሚደረገውን የእርድ ምልክት መካድ ግድ ይለዋል፡፡

ኢየሱስም ለደቀመዛሙርቱ በሰማይና በምድር የማሰርና የመፍታት ስልጣን እንዳላቸው ነግሯቸዋል፡፡ ህም ማለት በመንፈሳዊው ዓለም እና በቁሳዊው ዓለም ማለት ነው፡፡

> እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል (ማቴ 18፡18፤ 16፡19)፡፡

ክርስቲያኖች እግዚአብሔራዊ ያልሆኑ ውሎችንና ስግደቶችን የማፍረስ ስልጣን እንዳላቸው ማወቁ አስገራሚ መጽናኛ ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ ደም የተደረገው ቃል ኪዳን ማንኛውንም በክፉ ሐሳብ የተሰራን ውልና ኪዳን ስለሚያፈርስ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ መሲሁን አስመልክቶ በዘካርያስ መጽሐፍ የተጻፈው ነው፡፡

> ለአንቺም ደግሞ ስለ ቃል ኪዳንሽ ደም እስሮችሽን ውኃ ከሌለበት ጉድጓድ አውጥቻሁ (ዘካ 9፡11)

በመስቀሉ አማካይነት በአለቆችና በጨለማ በስልጣነት ላይ ድል እንዳለ እግዚአብሔር አስቀድሞ አሳውቆናል (ቆላ 2፡13-15)፡፡ ይሄኛው ድል የክፉት ኃይላት የሚገዙበትን ሰዎች በፈቃዳቸውም ይሁን ያለፈቃዳቸው አውቀውም ይሁን ሳያውቁ በነሱ ቅጥጥር ስር እንዲሆኑ ያደረጉበትን ኃይላቸውን ማሳጣት ችሏል፡፡

## ምዕራፍ 7

# ዲህማን እንዴት መካድ ይቻላል?

በዚህ ምዕራፍ  ከዲህማ የጭቆና አገዛዝ ነፃ ስለሚወጣበት መንገድ ስለሚናገረው የክርስቲያኖች ጸሎት ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

የመሐመድን ሕይወት በጥልቀት በምንመለከትበት ጊዜ ሌሎችን በመጉዳት ልምምድ ውስጥ ያለፈ ነው፡፡ በሚያቆስል፣ ሌሎች ላይ የኃይል ጥቃት በመፈጸም፣ የአዕምሮ ጉዳት ሰለባ በሚያደርግ መንፈስ በመመራት ሌሎችን በኃይል መቆጣጠር ችሏል፡፡ በሌሎች ላይ ጂሃድ በማወጅም ጭምር በጭቆና ውስጥ እንዲገቡና ዝቅተኛ ሆነው እንዲታዩ አድርጓል፡፡

በተቃራኒው ደግሞ ክርስቶስ በሰዎች የተወገዘ ሲሆን ጥቃትን ለመፈጸም ፈቃደኛ አልነበረም፡፡ ሌሎችንም የበታች አድርጎ

አላየም፡፡ ሰዎችን የሚያቆስለውን መንፈስ ተቃውሟል፡፡ መስቀሉና ትንሳኤው ተቀባይነት ማጣትንና የጨለማ ኃይላትን አሸንፏል፡፡

# ጸሎት ለምን አስፈለገ?

እነዚህን ጸሎቶች ለተለያዩ ምክንያቶች የመጸለይ ፍላጎት ሊኖርህ ይችላል፡፡

- አንተ ወይንም ዘሮችህ በእስልምና አስተዳደር ስር ሙስሊም እንዳልሆኑ ሰዎች በመኖር የዲህሚን ውል ተቀብላችሁት ሊሆን ይችላል ወይንም ደግሞ የጂሃድ እና የዲህሚ መርሆች ተፅዕኖ ባለበት ሁኔታ ውስጥ ኖራችሁ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ያህል የጂሃድ እና የአሸባሪዎችን ጥቃት ትፈራ ይሆናል፡፡
- ያንተና የቤተሰቦችህ ታሪክ ሽብርን በመሳሰሉ ከጂሃድ ጋር በተያያዙ በዲህማ ስር በሚከሰቱ ጥቃቶች ተፅዕኖ የደረሰበት ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነት ክስተቶች ስለመከሰታቸው ሰምተህ አታውቅ ይሆናል ነገር ግን የቤተሰብህ ታሪክ አካል ስለመሆኑ ጥርጣሬ ሊኖርህ ይችላል፡፡
- አንተ ወይንም ዘሮችህ በእስላማዊ ጂሃድ ማስፈራርያ ደርሶባችሁ ሊሆን ይችላል፡፡ ምናልባትም ደግሞ በእስልምና ስር የኖርክበት አጋጣሚ ባይኖርም ነገር ግን ከፍርሃት እና ከስጋት ነፃ መሆን ትፈልግ ይሆናል፡፡
- አንተ ወይንም ዘሮችህ እንደ ሙስሊሞች ኖራችሁ ሊሆን ይችላል ስለዚህ የዲህማ ውል እና ተያያዥ የሆኑ ነገሮች አካል መሆንህንም መካድ ትፈልግ ይሆናል፡፡

እነዚህ ጸሎቶች በህይወትህ ላይ ዳግመኛ ተፅዕኖ እንዳይኖረው የዲህማን ውል ከነትርጉሞቹ ለመሰረዝ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ በእስልምና ግዛት ውስጥ እንደ ዲህሚ በመኖራችሁ ምክንያት ባንተና በዘሮችህ ላይ የተደረጉትን እርግማኖች ሁሉ ለመስበር የተዘጋጁ ናቸው፡፡

ባለፉት ዘመናት ዕውቀት በማጣትህ ምክንያት እየተጸጸትክ እና ከንግዲህ በኋላ እንደ እግዚአብሔር ቃል ለመኖር እየወሰንክ ይህንን ጸሎት ልትጸልይ ትችላለህ፡፡ እነዚህ ጸሎቶች የሚከተሉትን የመሳሰሉ የዲህሚ አሉታዊ መንፈሳዊ ተፅዕኖዎችን ለመቀልበስ የተዘጋጁ ናቸው፡

- ውስጣዊ ጉዳት
- ፍርሃት
- እፍረት
- ማስፈራራት
- የህሊና ክስ
- የበታችነት ስሜት
- ራስን መጥላት እና ራስን አለመቀበል
- ሌሎችን መጥላት
- ድብርት
- ማታለል
- ውርደት
- መገለል እና ብቸኝነት
- ዝምታ

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች

ለነዚህ ጸሎቶች ራስን ለማዘጋጀት የመጀመርያው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማንበብ ነው፡፡ ይህም ለዚህ ጸሎት መሰረት የሆኑትን

እውነቶች ለማረጋገጥ ነው፡፡ እነዚህን ጸሎቶች መጸለይህን መመስከር ከሚችል አንድ ሰው ጋር ብትጸልይ ይመከራል፡፡

የእግዚአብሔር ፍቅር መገለልን ያሸንፋል

"እኛም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር አውቀናል አምነንማል። እግዚአብሔር ፍቅር ነው፥ በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል።" (1ዮሃ 4፡16)

"[ኢየሱስም አለ] በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" (ዮሃ 3፡16)

እድል ፈንታችን ፍርሃት አይደለም፤ በእግዚአብሔር ነው

"እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና።" (2ጢሞ 1፡7)

"አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና። አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል።" (ሮሜ 8፡15-16)

በነፃነት እንድንኖር ተጠርተናል

"[ኢየሱስም አለ] እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል።" (ዮሃ 8፡32)

"በነፃነት ልንኖር ክርስቶስ ነፃነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ።" (ገላ 5፡1)

ሰውነታችን የእግዚአብሔር እንጂ የጭቆና አይደለም፡ የደማችን ዋጋ ተከፍሏል

"ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።" (1ቆሮ 6፡19-20)

"እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት..." (ራዕ 12፡11)

ወንዶችና ሴቶች በእግዚአብሔር ፊት እኩል ናቸው፣ አንዱ ቡድን በሌላው ላይ የበላይ አይደለም

"አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና።" (ገላ 3፡28)

ልዩ መለያችን ውርደት እና የበታችነት አይደለም ነገር ግን የክርስቶስ ድል፣ በክርስቶስ ያለው የአንድነት ፍቅር እና የክርስቶስ መስቀል ናቸው

"ነገር ግን በክርስቶስ ሁልጊዜ ድል በመንሣቱ ለሚያዞረን በእኛም በየስፍራው ሁሉ የእውቀቱን ሽታ ለሚገልጥ ለአምላክ ምስጋና ይሁን" (2ቆሮ 2፡14)

"በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ፥ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ፤ እንዲሁም ዓለም አንተ እንደ ላክኸኝ በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደ ወደድሃቸው ያውቃል።" (ዮሃ 17፡23)

"ለሁሉም እንዲህ አላቸው፡- በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ።" (ሉቃ 9፡23)

እውነትን የሚገልጥልን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አለን

"እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ።" (ዮሃ 16፡7-8)

"ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ ዓይነገርምና፤ የሚመጣውንም ይነግራችኋል።"

እፍረትን ለማሸነፍ በክርስቶስ ስልጣን ተሰቶናል

"የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን

ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና። ” (ዕብ 12፡2)

ራሳችንንና ልጆቻችንን መንፈሳዊ ነገሮችን የማስተማር መብት አለን፤ ኃላፊነትም አለብን

“እግዚአብሔር፡- ሕዝቡን ወደ እኔ ሰብስብ፥ በምድርም በሕይወት በሚኖሩበት ዘመን ሁሉ እኔን መፍራት ይማሩ ዘንድ፥ ልጆቻቸውንም ያስተምሩ ዘንድ ቃሌን አሰማቸዋለሁ ብሎ በተናገረኝ ጊዜ፥ በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት በኮሬብ በቆምህበት ቀን ዓይኖችህ ያዩትን ነገር እንዳትረሳ፥ በሕይወትህም ዘመን ሁሉ ከልብህ እንዳይወድቅ ተጠንቀቅ፥ ነፍስህንም በትጋት ጠብቅ ለልጆችህም ለልጅ ልጆችህም አስታውቀው። ” (ዘጸ 4፡9)

እውነትን በፍቅር በድፍረት ለመናገር በክርስቶስ ስልጣን አለን

ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ናቸው የሚወድዱአትም ፍሬዋን ይበላሉ። ” (ምሳ 18፡21)

“አሁንም፥ ጌታ ሆይ፥ ወደ ዛቻቸው ተመልከት፤ ለመፈወስም እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ ብላቴናህም በኢየሱስ ስም ምልክትና ድንቅ ሲደረግ፥ ባሪያዎችህ በፍጹም ግልጥነት ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው። ” (ሐዋ 4፡29)

“ፍቅር ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም” (1ቆሮ 13፡6)

"ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ በሚታመን ሁሉ እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል እርሱም በእግዚአብሔር ይኖራል።" (1ዮሃ 4፡15)

"እንግዲህ ታላቅ ብድራት ያለውን ድፍረታችሁን አትጣሉ።" (ዕብ 10፡35)

በእውነት ቃል መተማመን አለን

"የሰውን ምስክር ብንቀበል የእግዚአብሔር ምስክር ከእርሱ ይልቅ ይበልጣል፤ ስለ ልጁ የመሰከረው የእግዚአብሔር ምስክር ይህ ነውና።" (1ዮሃ 5፡9)

"እነርሱም...ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት" (ራዕ 12፡11)

እኛ መከላከያ የሌለን ወይንም መሳርያ የሌለን አይደለንም ነገር ግን በመንፈስ የታጠቅን ነን

"በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ። የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።" (ኤፌ 6፡10)

"በሰው ልማድ ምንም እንኳ የምንመላለስ ብንሆን፥ እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም፤ የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፥ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤ የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም ዕውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን፥ መታዘዛችሁም በተፈጸመች

ጊዜ አለመታዘዝን ሁሉ ልንበቀል ተዘጋጅተናል።” (2ቆሮ 10፡3-4)

**በክርስቶስ ስም መከራ መቀበልን እንደ ደስታ ልንቆጥር ይገባናል**

“ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት” (ያዕ 1፡2)

**መስቀሉ የዲህማን ውል ያፈርሳል ኃይሉንም ይደመስሳል**

“እናንተም በበደላችሁና ሥጋችሁን ባለመገረዝ ሙታን በሆናችሁ ጊዜ፥ ከእርሱ ጋር ሕይወትን ሰጣችሁ። በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ። በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው። እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል። አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ፥ ድል በመንሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው።” (ቆላ 2፡13)

ስትጸልይ ሳለ ያንተ ጸሎት እና እወጃ ኃይል ያላቸውና ውጤታማ እንደሆኑ ተረዳ፡፡ እግዚአብሔር አንተን ወደ ሙሉ አርነት ሊያመጣህ ፍቃዱ ስለሆነ ከርሱ ጋር ተስማማ፡፡ ክርስቶስ እንደተቀበለህ እና ከየትኛውም የክፉ ወጥመድ ሊያላቅቅህ እንደሚፈልግ በመንፈስህ ውስጥ ተቀበል፡፡ የዲህማ ውል ሙስሊም ባልሆኑ ሰዎች ላይ የጫነውን ውሸት ለመጣል ወስን፡፡

# ጸሎቶች እና እወጃዎች

## *የንዛዜ ጸሎት*

*አፍቃሪ እግዚአብሔር ሆይ ኃጢአትን በመስራት ካንተ ዘወር ማለቴን እናዘዛለሁ፡፡ ሌሎች ሰዎችን ያስፈራራሁበትን እና በሰዎች ላይ የበታችነትን እንዲሁም ውርደትን የጫንኩበትን በደሌን ይቅር በለኝ፡፡ ስለ ትዕቢቴ ይቅር በለኝ፡፡ ሌሎችን የጎዳሁበትን እና የጨቆንኩበትን በደሌን ይቅር በለኝ፡፡ እነዚህን ሁሉ ነገሮች በኢየሱስ ስም ክጄያቸዋለሁ፡፡*

*የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሔር ሆይ በክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለተገኘው የይቅርታ ስጦታ አመሰግንሃለሁ፡፡ አንተ እንደተቀበልከኝ ዕውቅና እሰጣለሁ፡፡ በመስቀል በኩል ካንተ ጋር እና ከሌሎች ጋር መታረቅ ስለሆነልን አመሰግንሃለሁ፡፡ ልጅህ መሆኔን እና የእግዚአብሔር መንግስት ወራሽ መሆኔን ዛሬ አውጃለሁ፡፡*

## *እወጃዎችና ክህደቶች*

*አባት ሆይ የፍርሃት ተገዢ አለመሆኔን ነገር ግን የፍቅርህ ልጅ መሆኔን ካንተ ጋር እስማማለሁ፡፡ መሐመድ ያስተማረውን የእስልምና ፍላጎቶች ሁሉ እቃወማለሁ እክዳለሁ፡፡ በማንኛውም መንገድ ለቁርአኑ አላህ የሚሆነውን መገዛትን እክዳለሁ፡፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ የሆነውን እርሱን ብቻ እንደማመልክ አውጃለሁ፡፡*

*ለዲህማ ውል እና መርሆች ለመገዛት በመስማማት አባቶቻችን ለሰሩት ኃጢአት ንስሃ እንገባለን የኃጢአታቸውንም ይቅርታ እንጠይቅሃለን፡፡*

አርነት በምርኮ ውስጥ ላሉት

*ለእስልምና ማህበረሰብ እና መርሆች ለመገዛት በኔም ሆነ በዘሮቼ የተደረጉትን ውሎች ሁሉ እክዳለሁ፡፡*

*ዲህማንና አኳሆኖቹን ሁሉ ሙሉ በሙሉ እቃወማለሁ፡፡ በጂዝያ ክፍያ ጊዜ አንገት ላይ የሚደረገውን ምልክት ከነትርጉሙ እክዳለሁ፡፡ በተለይ በዚህ ስርአት የተመሰለውን የእርድ እና የሞት እርግማን እክዳለሁ፡፡*

*የዲህማ ውል በክርስቶስ መስቀል ላይ መቸንከሩን አውጃለሁ፡፡ ዲህማ በአደባባይ ስለተዋረደ በኔ ላይ ስልጣን የለውም፡፡ የዲህማ ውል መንፈሳዊ መርሆች በክርስቶስ መስቀል መጋለጡን፣ እርቃኑን መቅረቱን እና መዋረዱን አውጃለሁ፡፡*

*ለእስልምና ያለኝን የውሸት ክብር ስሜት እክዳለሁ፡፡*

*የውሸት የህሊና ክስን እክዳለሁ፡፡*

*በክርስቶስ ያለኝን እምነት ላለመናገር የገባሁትን ውል ሁሉ እክዳለሁ፡፡*

*ስለ ዲህማ ወይንም ኢስላም ላለመናገር የገባሁትን ውል ሁሉ እክዳለሁ፡፡*

*እናገራለሁ ዝምም አልልም፡፡*

*እውነት አርነት እንደሚያወጣኝ አውጃለሁ (ዮሃ 8፡32) በክርስቶስ ኢየሱስ ነፃ እንደወጣ ሰው መኖር ምርጫዬ ነው፡፡*

*በኢስላም ስም በኔና በቤተሰቦቼ ላይ የተነገሩትን እርግማኖች ሁሉ እክዳለሁ አመክናለሁ፡፡ በዘሮቼ ላይ የተነገሩትን እርግማኖች ሁሉ እክዳለሁ አመክናለሁ፡፡*

*በተለይ የሞትን እርግማን እሰብራለሁ፡፡ ሞት ሆይ በኔ ላይ ስልጣን የለህም!*

*እነዚህ እርማኖች በኔ ላይ ስልጣን እንደሌላቸው አውጃለሁ፡፡*

*የክርስቶስን በረከቶች እንደመንፈሳዊ ውርሶቼ አድርጌ አውጃለሁ፡፡*

*ፍርሃትን እክዳለሁ፡፡ በክርስቶስ ደፋር መሆን ምርጫዬ ነው፡፡*

*የሰዎች መጠቀሚያ መሆንንና በቁጥጥራቸው ስር መሆንን እክዳለሁ፡፡*

*ጭቆናና የኃይል ጥቃትን እክዳለሁ፡፡*

*ፍርሃትን እክዳለሁ፡፡ በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት የማጣት ፍርሃትን እክዳለሁ፡፡ የድህነትን ፍርሃት እክዳለሁ፡፡ ባርያ የመሆን ፍርሃትን እክዳለሁ፡፡ ተገዶ የመደፈርን ፍርሃት እክዳለሁ፡፡ ብቸኛ የመሆንን ፍርሃት እክዳለሁ፡፡ ቤተሰቦቼን የማጣት ፍርሃትን እክዳለሁ፡፡ የመገደልን እና የሞትን ፍርሃት እክዳለሁ፡፡*

*እስልምናን መፍራትን እክዳለሁ፡፡ ሙስሊሞችን መፍራትን እክዳለሁ፡፡*

*በሕዝባዊ ወይንም ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የመሳተፍ ፍርሃትን እክዳለሁ፡፡*

*ኢየሱስ ክርስቶስ የሁሉ ጌታ መሆኑን አውጃለሁ፡፡*

*ኢየሱስን በሁሉም የህይወቴ ክፍሎች ላይ ጌታ አድርጌ ራሴን እሰጠዋለሁ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የቤቴ ጌታ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የሃገሬ ጌታ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህች ሃገር ውስጥ ባሉ ሰዎች*

*ሁሉ ላይ ጌታ ነው፡፡ ኢየሱስን እንደ ጌታዬ አድርጌ ራሴን እሰጠዋለሁ፡፡*

*ውርደትን እክዳለሁ፡፡ ክርስቶስ እንደተቀበለኝ አውጃለሁ፡፡ እርሱንና እርሱን ብቻ አገለግላለሁ፡፡*

*እፍረትን እክዳለሁ፡፡ በመስቀሉ በኩል ከሁሉም ኃጢአት መንጻቴን አውጃለሁ፡፡ እፍረት በኔ ላይ መብት የለውም፡፡ ከክርስቶስ ጋር በክብር እነግሳለሁ፡፡*

*ጌታ ሆይ ሙስሊሞችን ስለመጥላታችን እኔንና ዘሮቼን ሁሉ ይቅር በለን፡፡ ሙስሊሞችንና ሌሎችን መጥላትን እክዳለሁ፡፡ የክርስቶስን ፍቅር በዚህ ምድር ላይ ላሉ ሰዎች ሁሉ አውጃለሁ፡፡*

*ስለቤተ ክርስቲያን ኃጢአትና መሪዎች በተሳሳተ መንገድ ስለመገዛታቸው ንስሃ እገባለሁ፡፡*

*ማግለልን እክዳለሁ፡፡ በክርስቶስ በኩል ይቅርታን ማግኘቴን እና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቴን አውጃለሁ፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ታርቄአለሁ፡፡ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት በሰማይም ሆነ በምድር ውስጥ ያለ ኃይል ለውጥ ሊያደርግብኝ አይችልም፡፡*

*ምስጋናዬን ወደ አባታችን እግዚአብሔር፣ ብቸኛ አዳኜ ወደሆነው ወደ ክርስቶስ፣ ብቻውን ህይወትን ወደሚሰጠኝ ወደ መንፈስ ቅዱስ ከፍ አድርጌ አነሳለሁ፡፡*

*ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታ መሆኑን ህያው ምስክር ለመሆን ራሴን አሳልፌ እሰጠዋለሁ፡፡ በመስቀሉ አላፍርም፡፡ በትንሳኤው አላፍርም፡፡*

*የአብርሃም የይስሃቅ የያዕቆብ አምላክ በሆነው የህያው እግዚአብሔር ልጅ መሆኔን አውጃለሁ፡፡*

*የእግዚአብሔርንና የመሲሁን ድል አውጃለሁ፡፡ ጉልበት ሁሉ እንደሚንበረከክ እና ምላስም ሁሉ ኢየሱስ ጌታ መሆኑን ለእግዚአብሔር ክብር እንደሚመሰክር አውጃለሁ፡፡*

*በዲህሚ ስርአት ውስጥ በመሳተፋቸው ለሙስሊሞች ይቅርታን አውጃለሁ፡፡*

*አባቴ እግዚአብሔር ሆይ እባክህን ከዲህማ፤ ከዲህሚ መንፈስ እና እግዚአብሔራዊ ካልሆነ ከዲህማ ጋር ከተያያዘ መርህ ሁሉ ነፃ አውጣኝ፡፡*

*አሁን በቅዱስ መንፈስህ እንድትሞላኝ እና የኢየሱስ ክርስቶስን መንግስት በረከቶች ሁሉ በኔ ላይ ታፈስ ዘንድ እጠይቅሃለሁ፡፡ የቃልህን እውነት አጥርቼ መረዳት እችል ዘንድ እና በእያንዳንዱ የህይወቴ ገጽታ ላይ ተግባራዊ ማድረግ እችል ዘንድ ጸጋህን ስጠኝ፡፡ የህይወትንና የተስፋን ቃሎች አደርጋለሁ ብለህ ቃል በገባኸው መሰረት ትሰጠኝ ዘንድ እና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በስልጣንና በኃይል መናገር እችል ዘንድ ከናፍርቴን ትባርክ ዘንድ እለምንሃለሁ፡፡ ለክርስቶስ ታማኝ ምስክር እሆን ዘንድ ድፍረትን ስጠኝ፡፡ ለሙስሊሞች ጥልቅ ፍቅርንና የክርስቶስን ፍቅር ከነርሱ ጋር መካፈል እችል ዘንድ ሸክምን እንድትሰጠኝ እለምንሃለሁ፡፡*

*እነዚህን ነገሮች አዳኝና ጌታ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አውጃለሁ እጠይቃለሁ፡፡ አሜን፡፡*

## ምዕራፍ 8

# ሽሃዳን እንዴት መካድ እንደምንችል

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኙት ጸሎቶች በአራት የተከፈሉ ናቸው፡-

- ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል መወሰን
- ሽሃዳና የመሐመድ ምሳሌነት
- ማታለል እና
- የበላይነት

## ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል የሚጸለይ የውሳኔ ጸሎት

*ፈጣሪ በሆነው ሁሉን ቻይ አንድ አምላክ አምናለሁ፡፡*

*ሌሎች አማልክትን ሁሉ እክዳለሁ፡፡*

*እግዚአብሔርንና ሰዎችን መበደሌን እናዘዛለሁ፡፡ ይህንንም በማድረጌ በእግዚአብሔርና በሕግጋቱ ላይ አመፅን ፈፅሜያለሁ፡፡*

*ራሴን ከኃጢአት ማዳን አይቻለኝም፡፡*

*ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑንና ሞትን ድል አድርጎ የተነሳ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አምናለሁ፡፡ በመስቀል ላይ በኔ ፋንታ ሞቶ የኃጢአት ቅጣቴን ከፍሎልኛል፡፡ ስለ እኔም ከሙታን ተነስቷል፡፡*

*ከኃጢአቴ እመለሳለሁ፡፡*

*በመስቀል ላይ የተገኘውን የክርስቶስን ይቅርታ እለምናለሁ፡፡ ይህንንም የይቅርታ ስጦታ አሁን ተቀብያለሁ፡፡*

*እግዚአብሔር አባቴ መሆኑን ተቀብዬ የእርሱ መሆንን እሻለሁ፡፡*

*የዘላለምን ሕይወት እፈልጋለሁ፡፡*

*ሕይወቴን በሞላ ለክርስቶስ ሰጥቴ ከዛሬ ጀምሮ እርሱ ይመራኝ ዘንድ እገዛለታለሁ፡፡*

*ሌሎች መንፈሳዊ ቃል ኪዳኖችን በሙሉ ክጃለሁ፡፡ ሸሃዳንና በኔ ላይ ያለውን ቁጥጥር በሙሉ እክዳለሁ፡፡*

*ሰይጣንንና ክፋትን ሁሉ እክዳለሁ፡፡ ከክፉ መንፈሳውያን ሥልጣናት ጋር ያደረኳቸውን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ያልሆኑ ስምምነቶችን በሙሉ እክዳለሁ፡፡*

*ከእግዚአብሔር ያልሆነ ሥልጣን በኔ ላይ ይኖራቸው ዘንድ ከሌሎች ጋር የገባኋቸውን ስምምነቶች ሁሉ አፍርሻለሁ፡፡*

*በማንኛውም ሁኔታ በኔ ላይ ተፅዕኖ እያደረገ የሚገኝ ዘር ማንዘሮቼ የገቡትን ቃል ኪዳን በሙሉ አፍርሻለሁ፡፡*

*በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ያልመጣ ማንኛውንም ስነ ልቦናዊ ወይም መንፈሳዊ ኃይል ሁሉ እክዳለሁ፡፡*

*የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ይሰጠኝ ዘንድ እለምናለሁ፡፡*

*አባቴ እግዚአብሔር ሆይ ላንተና ላንተ ብቻ ክብርን ማምጣት እችል ዘንድ አቤቱ አርነትን ስጠኝ፡፡*

*አንተን እንዳከብርና ሌሎችን እንድወድ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችን በውስጤ አኑር፡፡*

*ራሴን ለእግዚአብሔር አምላኬ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል መቀደሴን በሰዎችና በመንፈሳውያን ኃይላት ሁሉ ፊት አውጃለሁ፡፡*

*የሰማይ ዜጋ መሆኔን አውጃለሁ፡፡ እግዚብሔር ጠባቂዬ ነው፡፡ በዘመኔ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ እንደ ጌታዬ ለመከተል በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ምርጫዬ አድርጌያለሁ፡፡*

# ከሸሀዳና ከመሐመድ ምሳሌዎች አርነት መውጣት

ሙስሊሞች ሸሀዳን በሚያነበንቡበት ጊዜ መሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ነው ይላሉ ቁርአንንም እንደ አላህ ቃል አድርገው ይወስዳሉ፡፡ ይሄ ማለት ደግሞ ቁርአን ስለመሐመድ የተናገረውን ሁሉ ይቀበላሉ ማለት ነው፡፡ የግድ ሊከተሏቸው የሚገቡ ምሳሌዎቹንም ጭምር ማለት ነው፡፡ መሐመድን ሊከተሉ የማይወዱ የሚያጋጥማቸውን ሥቃይና እርግማንም ይጠብቃሉ፡፡ በመሐመድ የማያምኑና የማይከተሉትን መዋጋት ሥራቸው እንደሆነም ያምናሉ፡፡

አሉታዊ የሆኑት አንዳንድ የመሐመድ ምሳሌዎች የሚከተሉትን ይይዛል፡፡

- የኃይል ጥቃትና ጦርነት
- ነፍሰ ገዳይነት
- ሌሎችን ባርያ ማድረግ
- መበቀልና መቅጣት
- ሴቶችን መጥላት
- አይሁዶችን መጥላት
- ስድብ
- ማፈርና ሌሎችን ማሳፈር
- ሌሎችን መናቅ
- ማታለል
- ለማጥቃት መነሳት
- ራስን ማጽደቅ/ ለሰሩት ጥፋት ኃላፊነት አለመውሰድ
- የበላይነት ስሜት
- የእግዚአብሔርን ባህርያት አዛብቶ መተርጎም
- ሌሎችን ለመጨቆን መፍቀድ እና
- አስገድዶ መድፈር

ሸሀዳን በማነብነብ ሙስሊሞች ቁርአን እና በሱና ስለ ክርስቶስና እና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገሯቸውን ነገሮች መቀበላቸውን ያረጋግጣሉ፡፡ እነዚህ ደግሞ የሚያጠቃልሉት፡

- የክርስቶስን በመስቀል ላይ መሞት መካድ
- መስቀልን መጥላት
- ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ የሚለውን መካድ( ይሄንን የሚያምኑም ሰዎችን መርገም)
- አይሁዶችና ክርስቲያኖች ቅዱሳን መጻሕፍትን በርዘዋል ብሎ ማመን
- ኢየሱስ ዳግመኛ ተመልሶ የሚመጣው ክርስትናን ለማጥፋትና ዓለም ሁሉ ለመሐመድ ሸሪአ እንዲገዛ ለማስገደድ ነው ብሎ ማመን

አንድ ሰው እስልምናን በሚተውበት ጊዜ በሸሀዳ ላይ የተጠቀሱትን ማለትም መሐመድን እንደ ነብይ መቀበልን መተውና መካድን ያጠቃልላል፡፡ ይሄ ማለት ደግሞ ቁርአን የእግዚአብሔር ቃል ነው ብሎ አለመቀበል ማለት ነው፡፡

መሐመድ እንደ መልዕክተኛ ያለው ቦታ በግልጽ ካልተካደ በቁርአን ውስጥ የሚገኙት እርግማኖች እና ማፈራርያዎች እንዲሁም መሐመድ ለክርስቶስ ሞት እና ለክርስቶስ ጌትነት የነበረው ተቃውሞ መንፈሳዊ መዋዠቅን ሊያስከትል ችላል፡፡ ይህም አንድን ሰው በቀላሉ የወረደ ማንነት እንዲኖረው ሊያደርግ ይችላል፡፡ ከዚህም የተነሳ በቀላሉ ሊጎዳ ስለሚችል እንደ ክርስቶስ ተካታይ በእምነት የመከተል ችግር ያጋጥመዋል፡፡

# ጸሎቶች

*በመሐመድ ሕይወት የተገለጡትን ትምህርቶችና የሐሰት መገዛት እክዳለሁ፡፡*

*መሐመድ የአምላክ መልዕክተኛ ነው የሚለውን የውሸት እምነት አልቀበልም፡፡ እክደዋለሁም፡፡*

*ቁርአን የእግዚአብሔር ቃል ነው የሚለውን አነጋገር እክዳለሁ፡፡*

*ማንኛውንም ሸሀዳን ማነብነብ አግባብ ነው ብዬ አልቀበልም፡፡ እክደዋለሁም ፡፡*

*አል ፋቲሃ አይሁዶች ከእግዚአብሔር ቁጣ በታች ናቸው፣ ክርስቲያኖችም ከሀዲዎች ናቸው የሚለውን አስተምህሮ እክዳለሁ፡፡*

*አይሁዶችን መጥላትን እክዳለሁ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በርዘውታል የሚባለውን አባባል አልቀበልም፡፡*

*እግዚአብሔር ኤሁዳውያንን ጥሏቸዋል የሚለውን አመለካከት እክዳለሁ፡፡*

*ቁርአንን ማነብነብና በሕይወቴ ላይ ስልጣን አለው የሚለውን አባባል እክዳለሁ፡፡*

*መሐመድን እንደ ምሳሌ በመቁጠር የሚደረግ ማንኛውንም የሐሰት አምልኮ እክዳለሁ፡፡*

*መሐመድ እግዚአብሔርን አስመልክቶ ያመጣውን የሐሰት ትምህርቶች እክዳለሁ፡፡ በቁራኑ ላይ የተገለጠውን አላህ እግዚአብሔር ነው የሚለውን አባባል እክዳለሁ፡፡*

*በተወለድኩ ጊዜ ለእስልምናና ለዘር ዘሮቼ የተሰጠሁበትን መሰጠት እክዳለሁ፡፡*

*የመሐመድን ምሳሌዎች ተከተል የሚለውን አስተሳሰብ እክዳለሁ፡፡*

*የኃይል ጥቃትን ፣ሌሎችን ዝቅ አድርጎ ማየትን፣ ጥላቻን፣ በሴቶች ያለአግባብ መጠቀምን፣ ሌብነትን፣ መሐመድ የፈጸማቸውን ሁሉንም ኃጢአቶች እቃወማለሁ፡፡ እክዳለሁ፡፡*

*በክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑቱ ከኩነኔ ነፃ መሆናቸውን፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከማንኛውም አሳፋሪ በደል ነፃ ስላወጣኝ ማንኛውንም አሳፋሪ ነገርን አልቀበልም፡፡ ደግሞም እክደዋለሁ፡፡*

*በሙስሊሞች የሚነገር ማንኛውንም የፍርሃት ንግግር አልቀበልም ደግሞም እክደዋለሁ፡፡ በሙስሊሞች ዛቻ የተነሳ በፍርሃት ውስጥ ለወደቁት እግዚአብሔር ይቅርታ እንዲያደርግላቸው፣ በሁሉም ነገራቸው በእግዚአብሔር መታመንን ምርጫቸው እንዲያደርጉ እጸልይላቸዋለሁ፡፡*

*እግዚአብሔራዊ ባልሆነው ማንኛውም ድርጊቴ ይቅርታ እንዲያደርግልኝ ፣ መሐመድንም የአላህ መልዕክተኛ ነው ብዬ በመከተሌ እግዚአብሔርን ምህረት እጠይቃለሁ፡፡*

*ኢየሱስ ዳግመኛ ወደ ምድር በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ የሚኖሩ ሁሉም ሕዝቦች የመሐመድን ሸሪአ እንዲቀበሉ ያስገድዳቸዋል የሚለውን የስድብ ንግግር እቃወማለሁ ፡፡ ደግሞም እክዳለሁ፡፡*

*ኢየሱስን ብቻ ለመከተል ምርጫዬ አድርጌአለሁ፡፡*

*ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን፤ ለኃጢአቴ በመስቀል ላይ መሞቱን፤ ለኔ ደህንነት ሲል ከሞት መነሳቱን አምናለሁ፡፡ ስለ ክርስቶስ መስቀል እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡ የኔን መስቀል ወስዶ እንድከተለው ስላደረገኝ፤*

*ክርስቶስ የሁሉም ጌታ መሆኑን አምናለሁ፡፡ በሰማይና በምድር ላይ ገዢ ነው፡፡ የሕይወቴ ጌታ ነው፡፡ በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ ዳግመኛ እንደሚመጣ አምናለሁ፡፡ እንድንበት ዘንድ ከሰማይ በታች የተሰጠ ከኢየሱስ ሌላ ስም እንደሌለ አምናለሁ፡፡*

*አባቴ እግዚአብሔር አዲስን ልብ እንዲሰጠኝ ወደ ሕይወቴ እጋብዘዋለሁ፡፡ እርሱም የክርስቶስ ልብ ነው፡፡ በምናገረውና በማደርገው ሁሉ ይመራኝ ዘንድ፤*

*ሁሉንም የሐሰተኛ አምልኮዎች እቃወማለሁ፡፡ ህያው አምላክን ለማምለክ ማንነቴን አሰጣለሁ፡፡ አብ፤ ወልድና መንፈስቅዱስን፡፡*

# ከመታለል አርነት መውጣት

በኢስላሚክ ጅሃድ ላይ በመቃወም ተናግረዋል ተብለው በኢንዶኔዢያ ወህኒ ቤት በሐሰተኛ ክስ ታስረው የነበሩት መጋቢ ዳምኒክ ስለ እውነት እንዲህ ብለዋል፡፡

*…የቱንም ያህል እውነትን ማግኘት አስቸጋሪና ውድ ቢሆንም ሌላ ምርጫ የለንም፡፡ እውነትን ፍለጋ ሊከፈል የተገባውን ውድ ዋጋ ሁሉ እንከፍላለን፡፡ ሊኖረን የሚገባ ምርጫ ካለ ደህና ሁኝ እውነት የሚል ይሆናል፡፡ የእውነት ወዳጆች እንደ ብረት የጠነከረ ነገር ሊኖራቸው እንደዚሁም ንጹህና ግልጽ የሆነ ልብ ያላቸው ናቸው (እንደ ብርጭቆ)፡፡ እንደሚታወቀው የብረት ምሰሶ ጠንካራ ነገር ነው፡፡ ሊታጠፍ የሚችልም አይደለም፡፡ የሚጸናና የማይለወጥም ነው፡፡*

*… እንደ ብርጭቆ የሆነ ልብ ከተደበቀ ማንነት የጸዳና ንጹህ ማንነት ያለው ነው፡፡ በብርጭቆው እንደሚታየው እውነት ወዳጆች ስሜታዊ ናቸው፡፡ በዓለም ላይ ስላለው የፍትህ መዛባትና የሐሰት መንገስ በቀላሉ ሊሰበሩ የሚችሉ ናቸው፡፡ የልብ መሰበር የድካም ምልክት ተደርጎ መቆጠር የለበትም፡፡ ነገር ግን የጥንካሬና የኃይል ምልክት ነው፡፡ ጠንካራ ፈቃድ ያለውና የተሳለ አንደበት ያለው ነው፡፡ በውሸተኞች መካከልና በዙርያው ባሉት ሁሉ ላይ በግልጽና በድፍረት መናገር ይችላል፡፡ ልቡ ዝም ሊል አይችልም፡፡ ፍትህ በሚጣመምበት ጊዜ መታገስ ስለማይችል ፊት ለፊት ይጋፈጣል፡፡*

እግዚአብሔር እውነት የመሆኑ እውነታ ከእርሱ ጋር ወደ ሕብረት ለመግባት ለኛ መሰረታዊ ነገር ነው፡፡

እግዚአብሔር በሕብረት ያምናል፡፡ ከሰው ልጆች ጋር ግንኙነትን እንዲኖረው መስመሩንም ዘርግቷል፡፡

## አብርሃም፡

“ቃል ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል ከአንተም በኋላ ከዘርህ ጋር በትውልዳቸው ለዘላለም ኪዳን አቆማለሁ፡፡ ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ አምልክ እሆን ዘንድ ፡፡ በእንግድነት የምትኖርባትን ምድር የከንዓን ምድር ሁሉ ለዘላለም ግዛት ይሆንህ ዘንድ ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ እሰጣለሁ፤ አምላክም እሆናቸዋለሁ፡፡” (ዘፍ 17፡ 7-8)

## ዳዊት

ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ ለባርያዬም ለዳዊት ዘርህን ለዘላለም አዘጋጃለሁ፡፡ ዙፋንህንም ለልጅ ልጅ እመሰርታለሁ፡፡ (መዝ 89፡3-4)

እግዚአብሔር በግንኙነቱ የማይለወጥና ታማኝ ነው፡፡ ሁልጊዜ ቃሉን ይጠብቃል፡፡

“ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም እርሱ ያለውን አያደርገውምን? የተናገረውንስ አይፈጽመውምን?” (ዘኁ 23፡19)

“እግዚአብሔርን አመስግኑ ቸር ነውና ምህረቱ ለዘላለም ነውና” መዝ (136፡1)

[ስለ እስራኤላውያን ሲናገር] “...በምርጫ በኩል ግን ስለ አባቶች ተወዳጆች ናቸው፤ እግዚአብሔር በጸጋው ስጦታና በመጥራቱ አይጸጸትምና” (ሮሜ 11፡28-29)

> “...ለተመረጡት እምነት እንዲሆንላቸው በዘላለምም ሕይወት ተስፋ እንደ አምልኮት ያለውን እውነት የማይዋሽ እግዚአብሔር ከዘላለም ዘመናት በፊት ተስፋ ሰጠ፡ ፡” (ቲቶ 1፡2)

> “ስለዚህም እግዚአብሔር የተስፋውን ቃል ለሚወርሱ ፈቃዱ እንደማይለወጥ አብልጦ ሊያሳያቸው ስለ ፈቀደ እግዚአብሔር ሊዋሽ በማይቻል በሁለት በማይለወጥ ነገር በፊታችን ያለውን ተስፋ ለመያዝ ለሸሸን ለእኛ ብርቱ መጽናናት ይሆንልን ዘንድ በመሐላ በመካከል ገባ፤ ይህም ተስፋ እንደ ነፍስ መልሕቅ አለን እርሱም እርግጥና ጽኑ የሆነ ወደ መጋረጃውም ውስጥ የገባ ነው፡ ፡ (ዕብ 6፡ 17-19) እግዚአብሔር ግን የታመነ ነው፡ ፡ ለእናንተም የሚነገረው ቃላችን አዎንና አይደለም አይሆንም፡ ፡ በእኛ ማለት በእኔና በሰልዋኖስ በጢሞቴዎስም በመካከላችሁ የተሰበከ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ አዎንና አይደለም አልነበረም ነገር ግን በእርሱ አዎን ሆኗል፡ ፡ እግዚአብሔር ለሰጠው የተስፋ ቃል ሁሉ  አዎን ማለት በእርሱ ነውና ስለዚህ እግዚአብሔር ስለክብሩ በእኛ የሚነገረው አሜን በእርሱ ደግሞ ነው፡ ፡” (2ቆሮ 1፡18-20)

በቁርአን ግን ይሄ የአላህ ስብእና አይደለም፡ ፡

> ከመልክተኛ ማንኛውንም ለነርሱ ያብራራላቸው ዘንድ በሌላ አልላክንም አላህም የሚሻውን ያጠማል፤ የሚሳንም ያቀናል፤ እርሱም አሸናፊው ጥበብ ነው፡ ፡ (14፡4)

እውነተኛው የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር እርሱን እንድንመስለው ይፈልጋል፡፡

> "እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው። ለእስራኤል ልጆች ማኅበር ሁሉ እንዲህ በላቸው፡- እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ።" (ሌዋ 19፡1-2)

የእግዚአብሔርን ቅድስና ከምንገልጥባቸው መንገዶች መካከል አንዱ እውነተኛ በመሆን እና በእውነት በመኖር ነው ምክንያቱም እግዚአብሔር እውነት ነውና፡፡ ሰይጣን ውሸትን በልባችን ውስጥ መጨመር ያስደስተዋል፡፡ የእግዚአብሔር እውነት ግን ይጠብቀናል፡፡

> "ምሕረትህ በዓይኔ ፊት ነውና፥ በእውነትህም ተመላለስሁ።" (መዝ 26፡3)

> "በእጅህ ነፍሴን እሰጣለሁ የእውነት አምላክ አቤቱ፥ ተቤዠኸኝ።" (መዝ 31፡5)

> "አቤቱ፥ አንተ ምሕረትህን ከእኔ አታርቅ ቸርነትህና እውነትህ ዘወትር ይጠብቁኝ።" (መዝ 40፡11)

እውነት ያነፃናል

> "እነሆ፥ በዓመፃ ተፀነስሁ፥ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ።

እነሆ፥ እውነትን ወደድህ የማይታይ ስውር ጥበብን አስታወቅኸኝ። በሂሶጵ እርጨኝ፥ እነፃማለሁ እጠበኝ፥ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ።" (51፡5-7)

**ኢየሱስ በእውነት የተሞላ ነው**

"ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን።" (ዮሃ 1፡14)

**በእውነት እንድንሄድና እንድንኖር ተጠርተናል**

"እውነትን የሚያደርግ ግን ሥራው በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደ ሆነ ይገለጥ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል።" (ዮሃ 3፡21)

በወንጌላት ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ 78 ጊዜ እውነት እላችኋለሁ በማለት ተናግሯል፡፡ በእውነት ብቻ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንደምንችል ነግሮናል፡፡

"እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።" (ዮሃ 4፡24)

"ኢየሱስም፡- እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" (ዮሃ 14፡6)

ጳውሎስም ውሸት በመናገርና ክርስቶስን በመከተል መካከል ስላለው አለመጣጣም ይናገራል

"ይኸውም፥ ለበደለኞችና ለማይታዘዙ፥ ለዓመጸኞችና ለኃጢአተኞች፥ ቅድስና ለሌላቸውና ለርኵሳን፥ አባትና እናትን ለሚገድሉ፥ ለነፍሰ ገዳዮችና ለሴሰኞች፥ ከወንድ ጋርም ለሚተኙ፥ በሰዎችም ለሚነግዱ፥ ለውሸተኞችም በውሸትም ለሚምሉ፥ የብሩክ እግዚአብሔርንም ክብር እንደሚገልጥ ለእኔ አደራ እንደ ተሰጠኝ ወንጌል የሆነውን ደኅና ትምህርት ለሚቃወም ለሌላ ነገር ሁሉ ሕግ እንደ ተሰራ እንጂ ለጻድቅ እንዳልተሰራ ሲያውቅ ነው።"

# የባሕል ጉዳይ

እንደ እስልምና ከሆነ ውሸት በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ ተፈቅዷል፡፡ በቁርአን ውስጥ አምላክ ሰዎችን ያታልላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ውሸት ግዴታ ይሆናል፡፡ (ማታለልና ታቅያ በሚል ርዕስ ላይ የተደረገውን ትንተና The Third Choice በሚለው መጽሐፍ ላይ ከገጽ 56 ጀምሮ ይመልከቱ)፡፡

የሸሪአ ህግ የሚደነግጋቸው የውሸት ዓይነቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡ በጦርነት ጊዜ መዋሸት፣ ባል ሚስቱን መዋሸት፣ ራስን ለመጠበቅ መዋሸት፣ ኡማውን ለመጠበቅ መዋሸት፣ ሙስሊሞች በአደጋ ውስጥ እንዳሉ ካመኑ ራስን የመጠበቅ ውሸት (ታቅያ)፡፡

በእስልምና ኃይማኖታችሁን መካድ የተፈቀደ ነው፡፡ ነገር ግን ክርስቲያን በንዲህ ዓይነት መንገድ መኖር አይችልም፡

"ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤ በሰው

> **ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ።"** (**ማቴ** 10፡28-33)

**ኢየሱስ ንግግራችሁ አዎን ከሆነ "አዎን" በሉ ንግግራችሁ ደግሞ አይደለም ከሆነ "አይደለም" በሉ ብሏል፡፡**

# ጸሎቶችና አዋጆች

*አባት ሆይ አንድ ነገር አውቃለሁ አንተ የእውነት አምላክ ነህ፡፡ በጨለማው ምሽት ላይ ብርሃንህን አብርተሃል፡፡ ዛሬ በጨለማ ውስጥ ሳይሆን በብርሃንህ ውስጥ ለማደር መርጫለሁ፡፡*

*እባክህን የዋሸኋቸውን ውሸቶች ሁሉ ይቅር ትል ዘንድ እማጸንሀለሁ፡፡ ምቾት ያለበትንና ቀላሉን መንገድ መርጫለሁ ትክክለኛውን ግን አይደለም፡፡ በከናፍርቶቼ የበደልትን በደል ሁሉ ይቅርበለኝ፡፡ በእውነትህ የምደሰትበትን ልብ ስጠኝ፡፡ እውነትን ለሌሎች የሚናገር አንደብትንም ስጠኝ፡፡*

*ውሸትን የማስወግድበትና በእውነት የምጽናናበትን ብርታት ስጠኝ፡፡*

*በእየለቱ ኑሮዬ የምዋሸውን ውሸት ዛሬ አስወግዳለሁ ድግሞም እክደዋለሁ፡፡*

*ውሸትን የሚያበረታታውን የሙስሊሞችን አስተምህሮ አስወግዳለሁ **ታቂያንም** ጨምሮ፡፡ ከማንኛውም ውሸትና ማታላል ራሴን ዞር አደርጋለሁ በእውነት ለመኖር መርጫለሁ፡፡*

*ዋስትናዬ ያለው ባንተ መሆኑን አውጃለሁ እውነትም አርነት ያወጣኛል፡፡*

*የሰማይ አባት ሆይ በእውነትህ ብርሃን እንዴት መመላለስ እንዳለብኝ አሳየኝ፡፡ የምናገራቸውንም ቃሎች ስጠኝ በእውነትህ ላይ እንድራመድም መንገዱን አሳየኝ፡፡*

# ከየበላይነት አስተሳሰብ አርነት መውጣትና መብት መስጠት

በእስልምና የበላይ በመሆን "የተሻለው ማነው" በሚለው ላይ ላይ ልዩ አጽንዖት ይሰጠል፡፡ ፡፡ ቁርአን ሙስሊሞች ሙስሊም ካልሆኑት የተሻሉ ናቸው ብሎ ያስተምራል፡፡

> "ለሰዎች ከተገለጸች ሕዝብ ሁሉ በላጭ ኾናችሁ በጽድቅ ነገር ታዛላችሁ፤ ከመጥፎም ነገር ታዛላችሁ፤ በአላህም (አንድነት) ታምናላችሁ፡፡ የመጽሐፉም ሰዎች ባመኑ ኖሮ ለነርሱ የተሻለ በኾነ ነበር፡፡ ከነርሱ አማኞች አሉ፡፡ አብዛኞቻቸው ግን አመጸኞች ናቸው፡፡" (3፡10)

እስልምና በሌሎች ኃማኖቶች ሁሉ ላይ የበላይ ሆኖ መግዛት ይፈልጋል፡

> "እርሱ ያ መልክተኛውን በመሪ መጽሐፍና በእውነተኛ ኃይማኖት በኃይማኖት ሁሉ ላይ ሊያልቀው የላከ ነው፡፡ መስካሪም በአላህ በቃ፡፡" (48፡28)

በመሐመድ ብዙ ሀዲሶችም  የበላይ ስለመሆን ታላቅ አጽንዖት ተሰጥቷል፡፡

የእስልምና ኃይማኖት በአረብ ባህል ውስጥ ትልቅ ተፅዕኖ ፈጥሯል፡፡ ይሄም ከ1000 ዓመት በላይ ቅርጽ ይዞ እንዲሄድ አድርጓል፡፡ በአረብ ባህል "ክብር"ና "ሀፍረት" በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ ሰዎች የበታች ሆኖ መታየት እጅግ ያሳፍራቸዋል፡፡ አንድ ግጭት በሚኖርበት ጊዜ ሌላውን ዝቅ አድርጎ በማየት ሌሎችን በማጥቃት እርካታ የማግኘት አዝማምያ ይታያል፡፡

አንድ ሰው እስልምናን ትቶ በመውጣት ክርስቶስን ለመከተል የሚወስን ከሆነ ሰዎች በሌሎች ላይ የበላይ በመሆን በዚም እርካታን ለማግኘት ጥረት የሚያደርጉበትን የስሜታዊነት ንጽረተ ዓለም መካድ ይገባቸዋል፡፡

ከዚህ ጨቋኝ ከሆነ ንጽረተ ዓለም ነፃ የመውጫው መንገድ የክርስቶስ ምሳሌነት ነው፡፡ ጳውሎስ ለፊልጵሲዩስ ሰዎች በላከው ሁለተኛ መልዕክት ላይ ይህ ውብ በሆነ ሁኔታ ተገለጾዋል፡

> በክርስቶስም አንዳች ምክር ቢሆን፥ የፍቅር መጽናናት ቢሆን፥ የመንፈስ ኅብረት ቢሆን፥ ምሕረትና ርኅራኄ ቢሆኑ፥ ደስታዬን ፈጽሙልኝ፤ በአንድ አሳብ ተስማሙ፥ አንድ ፍቅር አንድም ልብ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ፤ ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር፤ እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፥ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ። በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን። እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም፥ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም

ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ። በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው። (ፊል 2)

ከመካከላቸው ማን የተሸለ እንደሆነ በኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መካከል በተለያዩ ጊዜያት ጥያቄ ይነሳ ነበር፡ ፡ በኢየሱስ መንግስት ውስጥ የክብር ስፍራ ሊኖረው የሚችለው ማን እንደሆነ ማወቅ ይፈልጉ ነበር፡ ፡

“የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስም ወደ እርሱ ቀርበው። መምህር ሆይ፥ የምንለምንህን ሁሉ እንድታደርግልን እንወዳለን አሉት። እርሱም፦ ምን ላደርግላችሁ ትወዳላችሁ? አላቸው። እርሱም፦ በክብርህ ጊዜ አንዳችን በቀኝ አንዳችንም በግራህ መቀመጥን ስጠን አሉት። ኢየሱስ ግን፦ የምትለምኑትን አታውቁም። እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ፥ እኔ የምጠመቀውንስ ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን? አላቸው። እርሱም፦ እንችላለን አሉት። ኢየሱስም፦ እኔ የምጠጣውን ጽዋ ትጠጣላችሁ፥ እኔ የምጠመቀውንም ጥምቀት ትጠመቃላችሁ፤ በቀኝና በግራ መቀመጥ ግን ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ የምሰጥ እኔ አይደለሁም አላቸው። አሥሩም ሰምተው በያዕቆብና በዮሐንስ ይቈጡ ጀመር። ኢየሱስም ወደ እርሱ ጠርቶ

> እንዲህ አላቸው፡- የአሕዛብ አለቆች ተብሎ የምታስቡት እንዲገዙአቸው ታላላቆቻቸውም በላያቸው እንዲሠለጥኑ ታውቃላችሁ። በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፥ ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የሁሉ ባሪያ ይሁን፤ እንዲሁ የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።" (ማር 10፥35-45)

ኢየሱስ እዚህ ቦታ ላይ አሕዛብ ብሎ የሚጠራው ሁሉንም ሕዝቦች ነው፡፡ የተፈላጊነት ስሜት እንዲሰማን መሻት ዓለም አቀፋዊ የሆነ የሰዎች ሁሉ አባዜ ነው፡፡ ልክ እንደ ያዕቆብና ዮሃንስ በመላው ዓለም ላይ የሚገኙ ሰዎች የተሻለውን መቀመጫ ወይንም ደግሞ የተሻለውን ክብር ይፈልጋሉ፡፡ ኢየሱስ ለዚህ መሻት መልስን የሰጠው ደቀ መዛሙርቱ በእውነት ሊከተሉት የሚፈልጉ ከሆነ ሌሎችን እንዴት ማገልገል እንደሚችሉ ማወቅ እንደሚያሻቸው በመንገር ነበር፡፡ በአንድ ልዩ መንገድ ኢየሱስ ይህ ተግባራዊ ሊሆን እንዴት እንደሚችል አሳይቷል፡፡ በዝያን ዘመን በነበሩ ሕዝቦች ዘንድ እንደ አሳፋሪ አሟሟት ለሚቆጠረው የመስቀል ሞት ራሱን አሳልፎ እስኪሰጥ ድረስ "ራሱን ባዶ አደረገ" (ፊል 2፥7)፡፡

በሌሎች ላይ የመሰልጠን ፍላጎት የሰው ልጆች ትልቅ ወጥመድ ነው፡፡ በኤደን ገነት እባብ ሄዋንን የፈተናት እንደዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ይዞ ነው፡፡ "እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ" በማለት (ዘፍ 3፥4) በዚህ መሰረት ሄዋን እባቡ ያላትን መሆን ፈለገች፡፡ ከዚህም የተነሳ በዓለም ላይ ከፍተኛ የሆነ ችግርና ስቃይ እንዲፈጠር ምክንያት ሆነ፡፡ ይሄ ደግሞ የሆነበት ምክንያቱ በሌሎች ላይ የበላይ ለመሆን ካለ ጥልቅ ፍላጎት የተነሳ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር የኢየሱስ አስተሳሰብ በእጅጉ የተለየ ነው፡፡ አገልጋይ መሆንን መረጠ፡፡ የበላይ መሆንን ግን አይደለም፡፡ ማንንም አልገደለም፡፡ ይልቁንም ለሌሎች ቤዛ በመሆን መስዋእት ሆነ እንጂ፡፡ እውነተኛ የክርስቶስ ተከታይም ማድረግ የሚገባው ተመሳሳይ ነገር ነው፡፡ ማንም ሰው በሌሎች ላይ የበላይ ሆኖ በመታየት ሊያገኝ የሚችለው አንዳች ደስታ የለም፡፡ እውነተኛ የክርስቶስ ተከታዮች ሌሎች በሚያስቡት ነገር ፍራቻም ሆነ ሀፍረት አይሰማቸውም፡፡

በሌሎች ላይ የበላይ የመሆን ፍላጎት አደገኛ ገጽታ እንዳለው የምንማረው በሉቃስ 15፡11-32 ላይ ከተጠቀሰው የአባካኙ ልጅ ታሪክ ነው፡፡ 'መልካም' ልጅ የተባለው የበላይነት ስሜት ስለተሰማው አባቱ ጠፍቶ ለተገኘው ልጅ ባዘጋጀው የደስታ ግብዣ ላይ ለመገኘት ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ በዚህም ምክንያት በአባቱ ተገስጾ ነበር፡፡ ወደ እውነተኛ ስኬት የሚወስደው መንገድ በእግዚአብሔር እይታ በሌሎች ላይ ጌታ መሆን ሳይሆን ሌሎችን ዝቅ ብሎ ማገልገል ነው፡፡

# ጸሎቶችና አዋጆች

*አባት ሆይ ድንቅ አድርገህ ስለፈጠርከኝ አመሰግንሀለሁ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የፈጠርከኝ አንተ ስለሆንክ ነው፡፡*

*ስለወደድከኝና የአንተ ስላደረግከኝ አመሰግንሀለሁ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን የምከተልበትን እድል ስለሰጠኸኝ አመሰግንሀለሁ፡፡*

*የበላይ የመሆንን ፍላጎት በማስተናገዴ ምህረትን አድርግልኝ፡፡ ከሌሎች የተሻለ ሆኖ ለመገኘት ፍላጎቴ በመገዛቴም ይቅር በለኝ፤*

*እንደ ማንኛውም ሰው ኃጢአተኛ መሆኔን አውቃለሁ፡፡ ያለ አንተም አንዳች ማድረግ አልችልም፡፡*

*የኋላ ታሪኬን በምመለከትበት ጊዜም ሆነ አሁን ባለሁበት ሁኔታ በቡድን ውስጥም ባለኝ ግንኙነት የበላይ ለመሆን ለነበረኝ ፍላጎት ይቅር በለኝ፤ እኔም እክደዋለሁ፡፡ ሁሉም ሰዎች በአንተ ፊት እኩል መሆናቸውን አምናለሁ፡፡*

*ሌሎችን ዝቅ የሚያደርግ ንግግርን በመናገሬ ይቅርታ አድርግልኝ፡፡ ለነዚህ ቃላቶቼ ምህረትን እጠይቃለሁ፡፡*

*በዘራቸው፣ በፆታቸው፣ በሀብታቸውና በትምህርታቸው ምክንያት ሌሎችን ዝቅ አድርጎ ማየትን እቃወማለሁ፡፡*

*በፊትህ መገኘት የቻልኩት በጸጋህ ብቻ መሆኑን አውቃለሁ፡፡ በሰው ልጆች ላይ ሊደረግ ካለሁ ከማንኛውም ፍርድ እራሴን እለያለሁ፡፡ ያዳንከኝን አንተን ብቻ እመለከታለሁ፡፡*

*ጻድቆች የበላይ ናቸው የሚለውን የሙስሊሞች አስተምህሮ እክዳለሁ፡፡ ሙስሊም መሆን ስኬታማ ያደርጋል፣ ሙስሎሞች የበላይ ሕዝቦች ናቸው የሚለውን እክዳለሁ፡፡*

*ወንዶች ከሴቶች የበላይ ናቸው የሚለውን አስተሳሰብ አልቀበልም፡፡ ደግሞም እክዳለሁ፡፡*

*የሰማዩ አባት እግዚአብሔር ሆይ ከነበረኝ ማንኛውም የበላይ የመሆን አስተሳሰብ እመለሳለሁ፡፡ አንተንም ለማገልገል መርጫለሁ፡፡*

*ጌታ ሆይ በሌሎች ስኬት ለመደሰት መርጫለሁ፡፡ በሌሎች ላይ መቅናትና ጥላቻን አልቀበልም ደግሞም እክደወለሁ፡፡*

*ጌታ ሆይ በፊትህ ምን ዓይነት ሰው ስለመሆኔ ጤናማና ትክክለኛውን ፍርድ ስጠኝ፤ እንዴት እንደምታየኝ እውነቱን አስተምህረኝ፡፡ አንተ የምትፈልገው ዓይነት ሰው እንድሆንልህ እርዳኝ፡፡*

# ዋቢ መጻሕፍት/ Bibliography

Bernard, J.H. 1928. A critical and exegetical on the Gospel according to John. 2 vols. Edinburgh: T&T Clark.

Carson, D.A. 1991. The Gospel according to John. Leicester, England: Inter-Varsity press.

Gibson, Noel and Phyl. 1987. Evicting demonic squatters and breaking bondages. Drummoyne, NSW: Freedom in Christ Ministries Trust. (An earlier edition of Evicting demonic intruders.)

Houlden, J.H. 1970. Paul's letters from prison: Philipians, Colossians, Philemon and Ephesians. Harmondsworth, Middlesex: Penguin.

Kreider, Alan. 1995. Worship and Evangelism in pre-Chrestendom. Alcuin/GROW Joint Liturgical Studies, 32. Cambridge: Grove Books Ltd.

Muir, William. 1861. The life of Mahomet. London: Smith, Elder and Co.